የኦክላንድ ተቋም እና ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ



## በአፍሪካ የሚደረገውን የመሬት ይዞታ ውል አስመልክቶ

# በኢንቨስትመንት ስም የሚፈጸም የመሬት ነጠቃ፤ በኢትዮጵያ

የኦክላንድ ተቋም እና ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

## በአፍሪካ የሚደረገውን የመሬት ይዞታ ወረራ አስመልክቶ

# በኢንቨስትመንት ስም የሚፈጸም የመሬት ነጠቃ፤ በኢትዮጵያ



## ጥቂት ስለ ዘገባው

ይህ ዘገባ በሰባት የአፍሪካ አገሮች (ኢትዮጵያ፣ ማሊ፣ ሞዛምቢክ፣ ሴራሊዮን፣ ሱዳን፣ ታንዛኒያ እና ዛምቢያ) የሚደረገው የመሬት ኢንቨስትመንት ውሎች ሁኔታ ምን ይመስላል? የሚለውን ለመመርመርና በማስረጃነት ለመጠቀም የኦክላንድ ተቋም (OI) ካካሄደው አንዱ ሲሆን የመሬት ሽያጭ ውሉ በተለይ በታዳጊ አገሮች ሊያስከትል የሚችለውን የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ተጽዕኖ የሚገመግም ነው።

ዘገባው የኦክላንድ ተቋምና ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) በጣምራነት ያዘጋጁት ነው። የዘገባው ጥናትም የተካሄደው ከጥቅምት 2003ዓም - ጥር 2003 ባሉት ጊዜያት ሲሆን ጥናቱንም ለማከናወን በቤንሻንጉል፣ በጋምቤላ እና ኦሮሚያ ክልሎች በቦታዎቹ ላይ በአካል በመገኘት የመስክ ምርምር ተካሂዷል።

የጥናት ቡድኑ እያንዳንዱን የመሬት ስምምነትና የመሬቱን አሸናሸን በተመለከተ ውሎቹ በጥልቅ በመመርመር ጥናቱን አድርጓል። የመስክ ጥናቱን ከተለያየ አቅጣጫ በማድረግ በርካታ ሰነዶችን በማሰባሰብ፣ በቦታው ላይ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦችን ቃለመጠይቅ በማድረግ፣ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚሰጡ የተፈጥሮ መሬቶች የሚኖራቸውን የማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሕጋዊ ተጽዕኖ መርምሯል። ቡድኑ ከመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ከሲቪል ማኅበረሰቦች፣ ከባለሃብቶች እና የመሬቱ ውል በኑሯቸው ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ካስከተለባቸው የአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ተገናኝቷል። በሪፖርቱ የግለሰቦች ታሪክ በተለያዩ ቦታዎች ተጠቅሷል፤ ሆኖም ግን መንግሥት ባሁኑ ጊዜ በሚያደርገው ክትትልና ፖሊሲው የሚቃወሙ ላይ ባለው ትዕግሥት አልባነት ምክንያት የሰዎቹ ማንነት እንዲሁም የሚኖሩበት ሥፍራ ሆን ተብሎ በሪፖርቱ እንዳይካተት ተደርጓል።

## የተርጓሚው ማስታወሻ

የእንግሊዝኛው ጽሁፍ የተዘጋጀው በኦክላንድ ተቋም (Oakland Institute) እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር በ2011ዓም ሲሆን የአማርኛው ትርጉም በወቅቱ እንዲወጣ የተደረጉ ሙከራዎች በተለያዩ አጋጣሚዎችና ከፍተኛ የሥራ መደራረብ እንዲሁም ቅድሚያ የሚሹ ጉዳዮች በመካከል እየገቡ የጊዜ ማስተጓጎል በመፍጠሩ እስካሁን ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ የአማርኛው ትርጉም በወቅቱ ሊወጣ ባለመቻሉ ምክንያት በተፈጠረ የጊዜ ክፍተት ሳቢያ የሚታዩ የመረጃ ማዛባቶችና ግድፈቶች ምክንያታቸው ይኸው መሆኑ እንዲታወቅ ያሻል፡፡

ከዚህ አኳያ በዚህ ጽሁፍ ወስጥ "በሚቀጥለው ዓመት" ተብሎ የተጠቀሰው ዓርፍተነገር ከእንግሊዝኛው በቀጥታ የተተረጎመ በመሆኑና ይህንንም ቀይሮ ማብራሪያ በየቦታው መስጠት ከአስፈላጊነቱ ይልቅ የጽሁፉን ወጥነት የሚያዛባ በመሆኑ እንዳለ ተትቷል፡፡

ሌላው የዶላር ምንዛሪ ተመን እና የብር ዋጋ ጽሁፉ በወጣበት ጊዜ ከነበረው ጋር እንጂ ተተርጉሞ ከታተመበት የጊዜ አንጻር የተሻሻለ አለመሆኑን አንባቢው አስተውሎ በዚሁ ግንዛቤ ጽሁፉ እንዲነበብ ማስገንዘብ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ከዚህ ወጪ በእንግሊዝኛውና በአማርኛው ጽሁፍ መካከል ለሚገኝ የሃሳብም ሆነ የቃላት ልዩነት የተርጓሚው መሆኑ እንዲታወቅና ኃላፊነቱም ሆነ ተጠያቂነቱ የተርጓሚው ስለሆነ ለማንኛውም ጉዳይ ተርጓሚውን የዚህ ጽሁፍ ባለቤት በሆነው ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የሕዝብ ግንኙነት ግብረኃይል በኩል በዚህ አድራሻ media@solidaritymovement.org ማግኘት ይቻላል፡፡

ተርጓሚው
መጋቢት 10፤ 2005ዓም/March 19, 2013

# ምስጋና

የዚህ ሪፖርት ተመራማሪ ጸሐፊ ፊሊክስ ሆርን ሲሆኑ ፕሮጀክቱ በኃላፊት የመሩት ፍሬዲሪክ ሞሳው ናቸው፡፡

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) ዋና ኃላፊ የሆኑትን አባንግ ሜቶን እንዲሁም የኦክላንድ ተቋም ኃላፊ የሆኑትን አኑራድሃ ሚታልን ላደረጉት ድጋፍና ትብብር ምስጋናችን ይድረሳቸው፡፡ ከተቋሙ የምርምርና የአርትዖት ድጋፍ የሰጡትንም ሼፐርድ ዳንኤልን ለማመስገን እንወዳለን፡፡

የራሳቸውን ሕይወት አደጋ ላይ በመጣል እንዲሁም ሊመጣባቸው የሚችለውን መከራ ሳይፈሩ አስፈላጊ የሆነው መረጃ በሙሉ ለሰጡን ጀግኖች በሙሉ የተለየ ምስጋና ልናቀርብላቸው እንወዳለን፡፡ ለደኅንነታቸው ሲባል ስማቸው በዚህ ሪፖርት ላይ ሳይቀርብ ቢቀርም በተለይ ግን ለዚህ ፕሮጀክት መሳካት በዋናነት የሚጠቀስ ተግባር ለፈጸሙት አቶ አኮክ አጁሉ ከፍ ያለው ምስጋና ይድረሳቸው፡

በዚህ ሪፖርት ላይ የተንጸባረቁት ሃሳቦች በሙሉ የኦክላንድ ተቋም ናቸው እንጂ ይህንን ፕሮጀክት ያገዙና የደገፉ ድርጅቶችም ሆኑ ግለሰቦች አቋም እንዳልሆነ እንዲታወቅልን ይሁን፡፡

የእንግሊዝኛውን ዘገባ ዲዛይን ያደረገው ኤሚሚዶ ግራፊክ ዲዛይን፣ አርታኢዎች፡ ፍሬድሪክ ሞሳው እና ግራኔት ሶስኖፍ ሲሆኑ ከእንግሊዝኛው ዘገባ የተወሰዱትን ፎቶዎች ያነሳው፡ ፊሊክስ ሆርን ነው፤ ከዚያ ወጪ ያሉት የአኢጋን ናቸው፡
የሽፋን ፎቶ፡ የካራቱሪ ከባንያ ትራክተር በምንጣሮና ጽዳት ተግባር ላይ፡፡

ይህ የአማርኛ ትርጉም ዲዛይን የተደረገው፣ የታረመውና ተቀናብሮ በዚህ መልኩ የተዘጋጀው በተርጓሚው ነው፡፡ ተርጓሚውን በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የሕዝብ ግንኙነት ግብረኃይል አድራሻ (media@solidaritymovement.org) በኩል ማግኘት ይቻላል፡፡

የእንግሊዝኛው አሳታሚ የኦክላንድ ተቋም በተለያዩ ማለትም በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ የሕዝብ ተሳትፎ እንዲኖርና ክርክሮች እንዲካሄዱ በሚደረግ ሥራ ላይ የተጠመደ የፖሊሲ ሃሳብ አመንጪ (ቲንክ–ታንክ) ተቋም ነው፡
የአማርኛው አሳታሚ አሰራጭ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) ነው፡፡ ይህ ድርጅት የተለያዩ ኢትዮጵያውያንን በአንድ ጥላ ሥር በማምጣት አሁን በሥልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ ለሚያደረሰው ስፍር ቁጥር የሌለው የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተጠያቂ እንዲሆን የሚታገል ለማኅበራዊ ፍትሕ ማስፈን የቆመ ነው፡

Copyright © 2011 by The Oakland Institute
የአማርኛው ትርጉም Copyright © 2013 by The Solidarity Movement for a New Ethiopia

ይህንን ሪፖርትና በወስጡ ያሉትን መረጃዎች (ፎቶዎች፣ ሠንጠረዦች፣ ሳጥኖች፣ ወዘተ) በከፊልም ሆነ በሙሉ ለማስተማሪያነት፣ ለማስተባበሪያነት፣ ለጥናትና ምርምር ሁለቱን ተቋማት እንደምንጭ በመጥቀስ ያለክፍያ ማጠቀም ይቻላል፡፡ ወደፊት ለሚደረጉ ተግባሮች ይረዳ ዘንድ የኮፒራይት ባለቤቶቹ

ከላይ ለተጠቀሱት ጉዳዮች የሚጠቀመው አካል እንዲመዘገብ ይሻሉ፡፡ ሆኖ ግን በሌላ ሚዲያ ኮፒ ለማድረግ፣ በሌሎች ኅትመቶች እንደገና ለማጠቀም፣ በተዛማጅ ወይም በቀጥታ ለመተርጎም ከተቋሞቹ ፍቃድ ማግኘት የግድ ነው፡፡ ይህንንም በሚከተለው አድራሻ ማመልከት ይቻላል፡፡ ለእንግሊዝኛው ዘገባ – info@oaklandinstitute.org ለአማርኛው ዘገባ media@solidaritymovement.org


**የኦክላንድ ተቋም**

**The Oakland Institute**

PO Box 18978

Oakland, CA 94619, USA

info@oaklandinstitute.org

www.oaklandinstitute.org

**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ**

**The Solidarity Movement for a New Ethiopia**

PO Box 857

Stillwater, MN 55082, USA

media@solidaritymovement.org

www.solidaritymovement.org


# ማውጫ


የአፈጻጸም ማጠቃለያ .......... 10

መግቢያ .......... 5

1. አገራዊ ዓውድ .......... 7

1.1 ማኅበረሰባዊ ዓውድ .......... 7
1.2 ፖለቲካዊ ዓውድ .......... 8
1.3 የልዕለምጣኔሃብት (ማክሮኢኮኖሚክስ) ዓውድ .......... 12
1.4 የምግብ ዋስትና ዓውድ .......... 17

1.5 የሜት ይዞታ .......... 19
1.6 የሜት ኢንቨስትሜትን በተመለከተ የሕግ አስተያየት .......... 24
1.7 የኢንቨስትሜት (የመዋዕለንዋይ) ዓወድ .......... 26

2. የሜት ይዞታ ኢንቨስትሜት ጥናት .......... 30

2.1 አጠቃላይ ወቅታዊ የኢንቨስትሜት ገጽታ .......... 30
2.2 የሜት ኢንቨስትሜት መሠረታዊ መርህ .......... 34
2.3 ምን ያህል ሜት ነው የተዘጋጀ ነው? .......... 35
2.4 ባለሃብቱ ማነው? .......... 37
2.5 ሜት ለኢንቨስትሜት እንዴት እንደሚዘዋወር? .......... 42
2.6 የሜት ኢንቨስትሜት ሂደት .......... 45
2.7 የስምምነቱ ይዘት .......... 46
2.8 ምክክርና ግልጽነት .......... 52
2.9 ሕግ ማስከበርና ክትትል .......... 52

3. ጥቅማጥቅምና ተጽዕኖ .......... 53

3.1 ጥቅማጥቅም .......... 54
3.2 በምግብ ዋስትና ላይ ያለው ተፅዕኖ .......... 57
3.3 የማኅበራዊ፣ ምጣኔሃብታዊ እና ባሕላዊ ተጽኖዎች .......... 59
3.4 ንብረት ማጣትና መፈናቀል .......... 69
3.5 የአካባቢ ተጽዕኖ .......... 71
3.6 የውሃ አጠቃቀምና አስተዳደር .......... 74
3.7 የሜት ይዞታ ባለቤትነት ሠርቲፊኬት፡ - ምን ጥቅም ይኖረው ይሆን? .......... 78
3.8 የግንዛቤ ደረጃ .......... 79
3.9 የዓለም ባንክ መሜያዎች .......... 79
3.10 ወደፊት ተጨማሪ ጥናት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች .......... 82

ተቀጽላ ሀ .......... 86

ተቀጽላ ለ .......... 86

# ምህጻረ ቃላት

ADLI — Agricultural Development Led Industrialization
ልማት መር የግብርና ኢንዱስትሪ

AGOA — Africa Growth and Opportunities Act
የአፍሪካ ዕድገትና ዕድል ሕግ

AISD — Agriculture Investment Support Directorate
እርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

COMESA — Common Market for Eastern and Southern Africa
ኢትዮጵያ የምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (ኮሜሳ)

EBA — “Everything But Arms” Initiative
“ከጦር መሣሪያ በስተቀር” ስምምነት

EIA — Environmental Impact Assessment
የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ

EWCA — Ethiopian Wildlife Conservation Authority
የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን (ኢዱልጥባ)

FAO — United Nations Food and Agriculture Organization
የተባበሩት መንግሥታት የምግብና የእርሻ ድርጅት (ፋኦ)

FDI — Foreign Direct Investment
ከውጪ የሚመጣ መዋዕለ ንዋይ

GSP — Generalized System of Preference
አጠቃላይ የምርጫ አሠራር

HRW — Human Rights Watch
የሰብዓዊ መብት ጥበቃ

ICERD — International Convention on the Elimination of all Forms of Racial Discrimination
የዓለም አቀፍ የዘር መድልዎ አስወጋጅ ጉባዔ

| | | |
|---|---|---|
| ICSID | International Center for the Settlement of Investment Disputes<br>ዓለምአቀፍ ክርክር የማላገያ ስምምነት ማዕከል |
| ILC | International Land Coalition<br>ዓለምአቀፍ የመሬት ኅብረት |
| IMF | International Monetary Fund<br>ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት |
| MDG | Millennium Development Goal<br>የሚሊኒየም የልማት ዕቅድ |
| MIGA | Multilateral Investment Guarantee Agency<br>የዓለምአቀፍ የኢንቨስትመንት ዋስትና ኤጀንሲ |
| MoARD | Ministry of Agriculture and Rural Development<br>የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር |
| OI | Oakland Institute<br>የኦክላንድ ተቋም |
| OPEC | Organization of the Petroleum Exporting Countries<br>የነዳጅ ላኪ አገራት ድርጅት (ኦፔክ) |
| PASDEP | Plan for Accelerated Sustained Development and to End Poverty<br>ድህነትን ለማጥፋት ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለው ዕቅድ |
| SIA | Social Impact Assessment<br>የማኅበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ |
| SMNE | Solidarity Movement for a New Ethiopia<br>ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) |
| UNCTAD | United Nations Conference on Trade and Development<br>የተባበሩት መንግሥታት የንግድና የልማት ጉባዔ |
| UNDP | United Nations Development Program<br>የተባበሩት መንግሥታ የልማት ፕሮግራም |
| WFP | United Nations World Food Program<br>የተባበሩት መንግሥታት የዓለም የምግብ ፕሮግራም |

# የሳጥኖች፣ የስዕሎችና የሠንጠረዦች ዝርዝር

ሣጥን ሀ፡ የደቡብ ኦሞ ሸለቆ ታሪክ

ሣጥን ለ፡ ሳዉዲ አረቢያ፣ የከብት ወጪ ንግድና ሞሐመድ አላሙዲ

ሣጥን ሐ፡ የፌደራሉ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ

ሣጥን መ፡ የካሩቱሪ ኩባንያ የመሬት ሊዝ ምስጢር

ሣጥን ሠ፡ የትግራይ የመሬት ኢንቨስትመንት

ሣጥን ረ፡ የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ

ሣጥን ሰ፡ ሳዉዲ ስታርና የፖኬዲ መንደር

ሣጥን ሸ፡ የማጀንጀር ታሪክ

ሣጥን ቀ፡ የሚሉሶ ማከፈር ታሪክ

ሣጥን በ፡ የመሬት ይዞታ በጋምቤላ ለሚገኙት አኙዋኮች ያለው ትርጉም

ሣጥን ተ፡ የኢትዮጵያ የአበባ ኢንዱስትሪ

ሣጥን ቸ፡ መንደር ምስረታና ግዳጅ ሰፈራ

ሣጥን ኀ፡ የአየር ንብረት ለወጥ በኢትዮጵያ

ሣጥን ነ፡ የአካባቢ ጥበቃ ትግበራ መተዳደሪያ

ሣጥን ኘ፡ አባይና የመሬት ኢንቨስትመንት

ሠንጠረዥ 1፡ የኢትዮጵያ የንግድ ሚዛን

ሠንጠረዥ 2፡ የኢትዮጵያ ዓመታዊ የወጪ ቀጥተኛ መዋዕለንዋይ ፍሰት

ሠንጠረዥ 3፡ ቀጥተኛ የወጪ መዋዕለንዋይ የባለሃብት አገሮች ዝርዝር
ሠንጠረዥ 4፡ የሜሬት ኢንቨስትመንት ስታቲስቲክ
ሠንጠረዥ 5፡ ለየሰብል ዓይነቱ የተዘጋጀ ሜሬት (በሺዎች ሔክታር)
ሠንጠረዥ 6፡ በፌደራሉ የሜሬት ባንክ የሚገኝና በአፌደሬ ለግብይት የቀረበ
ሠንጠረዥ 7፡ በሜሬት ይዞታዎች ላይ ሃብታቸውን ያፈሰሱ ሕንዳወያን
ሠንጠረዥ 8፡ የሜሬት ሊዝ ኪራይ በተወሰኑ አገሮች (በዶላር በአንድ ሔክታር በዓመት)

ስዕል 1 በክልል ደረጃ ለምግብ ዕጥረት የተጋለጠው ሕዝብ በመቶ

# የአፈጻጸም ማጠቃለያ

ላለፉት በርካታ ዓስርተ ዓመታት በወጪው ዓለም ዘንድ ኢትዮጵያ የረሃብ፣ የምግብ እጥረት፣ የማያቋርጥ ጤኔ እና የወጪ ዕርዳታ ጥገኛ አገር ሆና ስትታወቅ ቆይታለች፡፡ ምንም እንኳን በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር በዕርዳታ ስትቀበል የኖረች አገር ብትሆንም እስካሁን ኢትዮጵያ ከዓለም ደሃ ከሚባሉት አገሮች አንዷ ነች፡፡ ከ2000ዓም ጀምሮ የኢትዮጵያ መንግሥት በሚሊዮን የሚቆጠር ሄክታር ሜሬት ለአገር ወስጥና ለወጪ ባለሃብቶች የማስጠት ሂደቱ ተያይዞታል፡፡ ይህ የጥናት ዘገባ እንደሚያሳየው፣ ምንም እንኳን ትክክለኛው ቁጥር ከዚህ ሊበልጥ ቢችልም፣ እስካሁን ቢያንስ 3,619,509 ሄክታር ሜሬት ለባለሃብቶች ተሰጥቷል፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ይህንን የሜሬት ይዞታ ኢንቨስትመንት በጣም ተፈላጊነት ያለውን የወጪ ምንዛሪ ወደ አገሪቷ ለማምጣት ዕድል ይከፍታል፤ ከዚያም አልፎ የረጅም ጊዜ የምግብ ዋስትናን በማስጠበቅ የቴክኖሎጂ እሴቶችን ለትናንሽ እርሻዎች በማስተላለፍ እገዛ ያደርጋል ይላል፡፡

ይህ የጥናት ዘገባ በዚህ የሜሬት ሽያጭ ገፈት ቀማሽ የሆኑትን ማኅበረሰቦች፣ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ባለሃብቶች፣ የሲቪክ ማኅበረሰቦችን፣ እና ሌሎችን ቃለማጠይቅ በማድረግ የተዘጋጀ ከመሆን ባሻገር ከተለምዶና ከፕሮፓጋንዳ ባለፈ ሜልኩ "በቦታው ላይ" የሚደረገውን አስሜልክቶ ሚጃ በማቅረብ ይህ የሜሬት ኢንቨስትመንት በነዋሪወና በሜሬቱ ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ይተነትናል፡፡ የጥናቱ አጠቃላይ ወጤት የሚከተሉትን ግኝቶች ያካተተ ነው፡ –

**የንግድ ኢንቨስትመንት በአቅራቢያ በሚገኙ የሜሬት ኢንቨስትመንቶች ላይ የምግብ እጥረት እንዲኖር ሜድረጉ፤** ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በረሃና በምግብ እጥረት የታወቀች አገር ብትሆንም፣ ይህ የሜሬት ኢንቨስትመንት በምግብ ራሷን እንድትችል ከማድረግ አኳያ የሚሰጠው ምንም ዓይነት ዋስትና የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በእነዚህ የሜሬት ይዞታዎች ላይ የሚሚተው ሰብል የወጪ ምንዛሪ ለማስገኘት ሲባል የአገር ወስጥ አቅርቦትን ወደጎን በማለት ወደወጪ እንዲላክ የሚያደፋፍሩ ብዙ ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸው በምግብ ራስን ለመቻል በቂ ዕገዛ እንደሚያደርግ ያሳያል፡፡ በሜጨረሻም የኢትዮጵያ መንግሥት ከዚህ የሜሬት ኢንቨስትመንት የቴክኖሎጂ ልወወጥ በከፍተኛ ሁኔታ ሊካሄድ ይችላል ቢልም፣ እንዲህ ዓይነቱ ልወወጥ እንዲካሄድ ያማቻቸው ምንም ዓይነት ዘዴ ለሜኖሩ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

**በሕግ፣ በፖሊሲና በመሜሪያ ሜልክ የሚወጣው እንዲሁም ለሕዝብ በይፋ የሚነገረው በተግባር እየተፈጸመ ካለው ጋር ከፍተኛ ልዩነት ያለው መሆኑ፤** የኢትዮጵያ መንግሥት የሜሬትን ጉዳይ በተማለከተ ሁሉም ነገር

በምክክር የሚደረግ መሆኑን፣ ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ገበሬዎች አለመኖራቸውን እንዲሁም እየተሰጠ ያለው መሬት "ጥቅም ላይ ያለዋለ" ነው ቢልም የኦክላንድ ተቋም ቡድን ጥናት ባደረገባቸው አካባቢዎች በሙሉ መንግሥት አንድ ጊዜ እንኳን ከኅብረተሰቡ ጋር ምንም ዓይነት ምክክር እንዳላደረገ ደርሶበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የጥናት ቡድኑ በጎበኛቸው ቦታዎች በሙሉ ትናንሽ የእርሻ ቦታዎች እየጠፉ መሆናቸውን፣ በመንግሥት በኩል "ጥቅም ላይ ያለዋለ" የተባለው መሬት ለኢንቨስትመንት ከማስጠቱ በፊት በነዋሪዎቹ ዘንድ የተለያዩ የማኅበራዊ/ባሕላዊ እንዲሁም ሥነምህዳራዊ እሴቶች ጋር የተያያዙ ተግባራት አስቀድሞ ሲፈጸሙባቸው የቆዩ እንደነበሩ ለመመስከር ችሏል፡ ፡

**የውሃ አጠቃቀም ገደብ አለመኖር፤ የአካባቢያዊ ተጽዕኖ ግምገማ (EIA) እንዲሁም የአካባቢያዊ ቁጥጥር አለመኖር፤** ኢትዮጵያ ከአባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ ካለችበት ወሳኝ ሁኔታ እንዲሁም ውሃ በአገሪቷ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑ አኳያ ባለሃብቶች ውሃ ያለአንዳች ገደብ እንደፈለጉ እንዲጠቀሙ ሚፈቀዱ አስደንጋጭ የሆነ ክስተት ነው፡ ፡ እንዲያውም እነዚሁ ባለሃብቶች መሬት በገዙበት አካባቢ በሚገኝ ወንዝ ላይ ግድብ ለመሥራት ያላቸውን ዕቅድ ይህም ድርጊት ባካባቢው ላይ ከሚያመጣው ዕክል አኳያ በመንግሥት በኩል ያለው ቁጥጥር የላላ መሆኑን ባለሃብቶቹ ራሳቸው ለጥናት ቡድኑ በግልጽ ተናግረዋል፡፡ ምንም እንኳን የአካባቢያዊ ተጽዕኖ ግምገማ ተካሂዷል እየተባለ ሲነገር የቆየ ቢሆንም፤ አንድም የመንግሥት ባለሥልጣን የተሟላ የአካባቢያዊ ተጽዕኖ ግምገማ ለማቅረብ አለመቻሉን፤ ማንኛውም ባለሃብት ይህንኑ ግምገማ አሟልቶ አለማቅረቡን፤ እንዲሁም የየትኛውም አካባቢ ነዋሪ የተሟላ የግምገማ ሪፖርት አለማየቱን የጥናት ቡድኑ ተገንዝቧል፡፡

**ነዋሪው ኅብረተሰብ ከእርሻ መሬቱ ሚፈናቀሉ በግልጽ እየተካሄደ ያለ ተግባር መሆኑና በርካታ በየአካባቢው የሚኖሩ ምንም ዓይነት ካሣ አለመቀበላቸው፤** አብዛኛዎቹ ኢንቨስትመንቶች የሚካሄዱት በቆላማ አካባቢዎች (ከአንዱ ክልል በስተቀር) ከመሆኑ ባሻገር ባካባቢዎቹ ምንም ዓይነት የመሬት ሰርቲፊኬት የማስጠት ሂደት ሲፈጸም አይስተዋልም፡፡ የጥናት ቡድኑ ተዘዋውሮ በተመለከተባቸው ቦታዎች በሙሉ ያካባቢው ነዋሪ ከእርሻ መሬቱና ከሚኖርበት መንደር እየተፈናቀለ እንደሚገኝ ለማንዘብ ችሏል፡፡ መንግሥት በኅብረት ጥቅም ላይ ስለዋሉ የእርሻ ቦታዎች፣ እርሻን ወደሌላ ቦታ ስለማዘዋወርና ስለ አርብቶአደር የሚሰጠው አትኩሮት በጣም ትንሽ በመሆኑ እነዚህን ቦታዎች በሙሉ በጥቅሉ "ጥቅም ላይ ያለዋሉ" እያለ ሲሰይማቸው ይስተዋላል፡፡ በመሆኑም ከቦታቸው የሚፈናቀሉ ገበሬዎች ሌላ ቦታ የእርሻ መሬት እንዲፈልጉ ይገደዳሉ፤ ይህም በመሆኑ የተፈጥሮ ሃብትንና መሬትን በመሻማት ረገድ ከሌሎች ገበሬዎች ጋር ለወጥረት በሚዳርግ ከፍተኛ ፉክክር ውስጥ እንዲገቡ ይገደዳሉ፡፡

**ምንም ዓይነት የቅድመ ፕሮጀክት ግምገማ አለመኖር፤ እንዲሁም ለመሬት ኢንቨስትመንት ሲባል ለአካባቢያዊ ጥቅማጥቅሞች ትኩረት አለማስጠት፤** ደን ይመነጠራል፤ ብዝሃ ሕይወት ይጠፋል፤ የመኖር ዋስትና ይወድማል፤ ይህ ሁሉ የሚሆነው የመሬት ኢንቨስትመንትን ለመተግበር ሲሆን ተገቢ የመሬት አጠቃቀምን ተግባራዊ ከሚድረግ አኳያ የተመጣጠነ እና ሁሉንዓቀፍ የሆነ ተግባር ሲፈጸም አይስተዋልም፡፡ ከዚህ ይልቅ ግን ባለሃብቱ በፈለገው መሠረት ለፈለገው ተግባር የማዋል መብት ተሰጥቶታል፡፡ የአካባቢው ነዋሪ ከእነዚህ የንግድ ኢንቨስትመንቶች ጥቅም እንዲያገኝ የተቀየሰ ምንም ዓይነት ዕቅድ የለም፡፡ እንዲያውም የአካባቢው ነዋሪዎች በእነዚህ ኢንቨስትመንቶች ምክንያት ለሚፈጠረው ማንኛውም ችግር ገፈት ቀማሽና የበዪ ተመልካች ከመሆን በስተቀር የተረፈው አንዳችም ጥቅም የለም፡፡ አብዛኛዎቹ ኢንቨስትመንት የሚካሄድባቸው ቦታዎች የሚገኙት የየአካባቢው ነዋሪዎች ለዘመናት ሥር በሰደደ የምግብ ዕጥረት አዙሪት ውስጥ የሚኖሩ በመሆናቸው ይህንን የመሬት ኢንቨስትመንት እነርሱን ለሚጨቁን የሚገበር አዲስ መንገድ እንደሆነ አድርገው ነው የሚቆጥሩት፡፡

**የውጪ የመሬት ኢንቨስትመንቶች የመናኛ አውታሮችን አትኩሮት የሳቡ ቢሆንም ለአብዛኛዎቹ በአገር ውስጥና በውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሚከቡትን ትናንሽ ሚት በቅጡ ለሚልማት በቂ የግብርና እውቀት**

**አለመኖሩ፤** እያንዳንዱ ባለሃብት ለልማት ሲሰሚሩ ያቀደወን ተግባር በተገቢው ሁኔታ ለሚፈጸም የሚያስችለው በቂ የገንዘብ አቅም እንዳለው ይጠየቃል፡፡ ሆኖም ግን ያው ባለሃብት የእርሻ ተግባራትን ለሚፈጸም የሚያስችለው የትምህርትና የቴክኒክ ዕወቀት እንዳለው አይጠየቅም፡፡ ይህ የጥናት ቡድን በየማከሉ ተዘዋወሮ በተማከታቸው ቦታዎች ሁሉ በርካታ ባለሃብቶች የግብርና ነክ ዕወቀትና ልምድ እንደሚካላቸው ለሚዳት ችሏል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ሁሉ ሁኔታ ለኢትዮጵያ አዲስ ክስተት ነው፡፡ ባለሃብቶች ስለወሰዱት ሜሬት እና ስለአካባቢው በቂ ግንዘቤ እንደሌላቸው በአንጻሩ ደግሞ የየአካባቢው ነዋሪ የመኖሪያ ቦታው በቡልዶዘር ሲማጠር የሚማከት እንደሆነ የጥናት ቡድኑ ለማታዘብ ችሏል፡፡ ባለሃብቶች የኢትዮጵያን ሜሬት እያስማጠሩ ሲወስዱ የአካባቢው ነዋሪ ዘንድ ንዴትና ተስፋመቁረጥ እየጎላ እንዲሁም በአካባቢው የአየርንብረትና የምግብ ዋስትና በእጅጉ እየከፋ ይገኛል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን በየቦታው በአካል ተገኝቶ የታዘበው አሉታዊ ተጽዕኖ ከኢትዮጵያ መንግሥት ዘንድ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት እርምጃ ካልተወሰደና የሚከናወኑት የሜሬት ኢንቨስትመንት ወሎች በሙሉ የየአካባቢወን ነዋሪና በአጠቃላይ ደግሞ አገሪቷን እንዲጠቅሙ ሆነው የሚከናወኑ መሆናቸወን ካልተረጋገጠ በስተቀር ሁኔታዎች እየከፉ ሜሄዳቸው አይቀሬ ነው፡፡




**የአማራ ክልል**

በተለያዩ የዜና ማከራጫዎች እንደተዘገበው ከ175ሺህ ሐክታር በላይ ሜሬት ለኢንቨስትመንት ተመድቧል፡፡

**የአፋር ክልል**

በክልሉ 409ሺህ 678ሐክታር ሜሬት በኢትዮጵያ የፌደራል ሜሬት ባንክ አማካኝነት ለባለሃብቶች ተመድቧል፡፡

**የግብጽ ብሔራዊ ባንክ**

22ሺህ ሐክታር ለስንዴና የዘይት ዘር

**የኦሮሚያ ክልል**

**የጅቡቲ ማንግሥት**

3ሺህ ሐክታር ላይ ጥራጥሬዎች

**ኢምሚ ባዮቴክ (የሕንድ)**

100ሺህ ሐክታር የጃትሮፋና የምግብ ዘይት ዘር

**አልሜዳዛ (የሕንድ)**

28ሺህ ሐክታር የሸንኮራ አገዳ

**ሮምቶን አግሪ ኩባንያ (የሕንድ)**

10ሺህ ሐክታር ቲማቲም

**የጋምቤላ ክልል**

ከክልሉ 829ሺህ 199 ሐክታር (32በመቶ የሚሆነው የክልሉ ሜሬት) በኢትዮጵያ የፌደራል ሜሬት ባንም አማካኝነት ለባለሃብቶች የተዘጋጀ ነው፡፡

**ካራቱሪ (የሕንድ)**

300 ሺህ ሐክታር
ሩዝ፣ ከዘንባባ የሚገኝ ዘይት፣ በቆሎ፣ ሸንኮራ አገዳ ያመርታል

**ሩቺ ሶያ (የሕንድ)**

25ሺህ ሐክታር፤ አኩሪአተር

**ሳዑዲ ስታር ኩባንያ (የሳዑዲ አረቢያ)**

10ሺህ ሐክታር፤ ሩዝ

**ቢ ኤች አ (የሕንድ)**

27ሺህ ሐክታር ለነዳጅ የሚውል ዘይት

**ሶናቲ ግሮ ፋርም (የሕንድ)**

10ሺህ ሐክታር፤ ሩዝ፣ የባቄላ ዓይነቶችን እና ጥራጥሬ ያመርታል፡፡

**የደቡብ ክልል**

የኢትዮጵያ የሜሬት ገበያ በአብዛኛው ያተኮረው በዚህ ክልል ነው፡፡

ከየካቲት 2001ዓም ጀምሮ 200ሺህ ሐክታር የሚያካልል 16 የኢንቨስትመንት ስምምነት ተደርጓል፡፡ እያንዳንዱ ኢንቨስትመንት ከ5ሺህ ሐክታር በላይ ሲሆን እያንዳንዱም የተሰጠው ለወጪ ባለሃብት ነው፡፡

# መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ዙሪያ ለም የሆነ ሜሬት በረጅም ጊዜ ሊዝ ወይም የነጻ ያህል በሚቆጠር ዋጋ ለባለሃብቶች እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ይህ አካሄድ "የሜሬት ነጠቃ" ተብሎ የሚጠቀስ ሲሆን በተለይ በ2000 ዓም አካባቢ ከተከሰተው የምግብ ቀውስ ወዲህ የብዙዎችን አትኩሮት የሳበ ጉዳይ ሆኗል፡፡[1] በዚህም ምክንያት ኮርፖሬሽኖች፣ ባለሃብቶች፣ መንግሥታት፣ ወዘተ በምግብ አቅርቦት ራሳቸውን ለመቻል በሌሎች አገራት ታላላቅ የእርሻ ሜሬቶች የሚገኙበትን መንገድ ሲሰልሉ ሌሎቹ ደግሞ ወደፊት የገንዘብ ምንጭ ሊያስገኝ ይችላል በሚል ሲገዙ ቆይተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ከምንጊዜውም ይልቅ ባለሃብቶች የእርሻ ሜሬቶች ላይ መዋዕለንዋያቸውን ሜፍሰስ አስተማማኝና ትርፋማ እንደሆነ እየተረዱ መጥተዋል፡፡ በእስያና በመካከለኛው ምስራቅ የሚገኙ አንዳንድ አገሮች ለሰብል ምርት እያጋጠማቸው የመጣውን የሜሬትና የውሃ ሃብት ዕጥረት ለመመጣትና የምግብ ዋስትናቸውን ለሚጋገጥ ዓይናቸውን ወደባሕር ማዶ አገሮች በተለይም ወደ አፍሪካ እያዞሩ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአወሮፓ ሕብረትና በአሜሪካ እየተገበረ ያለው የሰብልነዳጅ ኮታ ኮርፖሬሽኖችን ወደነዳጅ የሚቀየሩ ሰብሎችን ለማምረት የሚያስችሉ ታላላቅ የሜሬትና የውሃ ሃብቶች ላይ ዓይናቸውን እንዲያዞሩና የሚገኙትንም እንዲቀራመቱ በዓለም ዙሪያ እንዲሯሯጡ እያደረጋቸው ይገኛል፡፡

በ2001 አካባቢ እንዲህ ዓይነቱ የኢንቨስትመንት ስምምነት በዓለም ዙሪያ 56 ሚሊዮን ሄክታር የእርሻ ሜሬት የሚካ ነበር፡፡[2] የተባበሩት መንግሥታት የምግብና የእርሻ ድርጅት (FAO) እንደሚለው ከሆነ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሁሉንም "ወገን የሚጠቅም"[3] ከመሆኑም ባሻገር የዓለም ባንክም ይህንኑ የሚደግፍ "ተገቢ የአግሮ-ኢንቨስትመንት" ዝርዝር መሜያ በማውጣት ከንደፊሃሳብ ባለፈ ሜኩ ሊከናወን ስለመቻሉ ያትታል፡፡[4]

ይህንን ጉዳይ አስሜልክቶ የሥነዜጋ ማነበረሰቦችና የሰብዓዊ መብት ቡድኖች እንዲሁም አነስተኛ የገበሬዎች ማነበራት እና አያሌ ሳይንቲስቶች ይቃወሙታ፡፡ የተቃወሟቸው መነሻም የሜሬት ነጠቃ ተግባር በምግብ ራስን የመቻልን ሁኔታ እንዲሁም ከምግብና ከሜሬት ጋር በተያያዘ የሰብዓዊ መብትን አደጋ ላይ ይጥላል ይላሉ፡፡ ከዚህ ይልቅ ግን መዋዕለ ንዋዩ ማጠነኛ የሆኑ የእርሻና ሥነምህዳራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የአስተራረስ ዘዴዎችን በሚዳ ሜኩ ቢደረግ ይሻላል ይላሉ፡፡[5] የሜሬትና የውሃ እጥረት ያጠቃቸው ባለሃብቶች በተለይ ሁኔታ በአፍሪካ ላይ ትኩረታቸውን የሚያደርጉ ሲሆን እነዚህም ከአጠቃላዩ የባለሃብቶች ፍላጎት 70 በመቶውን የሚጠቀልል ነው፡፡[6]

እስካሁን ድረስ በእያንዳንዱ አገር ላይ በማስረጃ የተደገፈና ያለውን ነባራዊ እውነት የሚያስረዳና የሜሬትን ወል በተሜከተ ብቃት ያለው ጥናት ተካሂዷል ለሚለት ያስቸግራል፡፡ ስለዚህም ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በኦክላንድ ተቋም አማካኝነት በሌሎች አገሮች ላይ በተደረጉ ጥናቶች ላይ ያለውን የሚጃና የእወቀት ክፍተት ለመሙላትነው፡፡

እንደ ሌሎቹ የአፍሪካ አገሮች ሁሉ ኢትዮጵያም በጣም ለምና ምርታማ የሆነውን የእርሻ ሜሬቷን በረጅም ጊዜ ሊዝ ለወጪ ባለሃብቶች ለማስጠት እየተደራደረች ትገኛለች፡፡ ከወጪ የሚመጣ መዋዕለ ንዋይ (FDI: Foreign Direct Investment) አስፈላጊነት የሚያጠራጥር ቢሆንም እነዚህ የሜሬት መዋዕለንዋዮች የአካባቢውን የማነበራዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ የየቦታውነዋሪ የምግብ ፍላጎትን ባላገናዘበ ሜኩ እየተካሄዱ ያሉ ናቸው የሚል በበርካታ ቦታዎች የሚገር አስተያየት አለ፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በእውነታ ላይ የተመሠረተ ግንዛቤ በሕዝቡ ዘንድ ከመፍጠር አኳያና ለፖሊሲ አውጪዎችም የሚያስተላልፉት ወሳኔ ከዚሁ ጋር የተያያዘና በቦታው ላይ በሚገኙ እውነታዎች ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ ግንዛቤ ለማስጠት ዓላማ ያደረገ ነው፡፡

ስለዚህ የዚህ ጥናት ዋንኛ ግብ በአሁኑ ጊዜ በተፋጠነ ሁኔታ እየተካሄደ ያለው የእርሻ ሜሬቶችን ለባለሃብቶች የማሣጠት ድርጊት

በምግብ ራስን ከመቻል አኳያ በተለይ በነዋሪዎች ላይ፣ በማንነታቸው ዙሪያና በኑሯቸው ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ምን እንደሚሆን ማስረዳት ነው፡፡

ይህ ጥናታዊ ዘገባ ለሦስት የተከፋፈለ ሲሆን የመጀመሪያው ከምጣኔሃብት፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና በምግብ ራስን ከመቻል ዐውዶች አኳያ ስለኢትዮጵያ አጠቃላይ ግንዛቤ ይሰጣል፡፡ ሁለተኛው ክፍል በተለይ ስለ መሬት ኢንቨስትመንት – የት፣ እንዴት እና ለምን እየተካሄደ እንደሆን ማዘርዘር ይሰጣል፡፡ ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የመሬት ኢንቨስትመንት (መዋዕለንዋይ) በኢትዮጵያ የማኅበራዊ፣ አካባቢያዊ፣ ምጣኔሃብታዊና በምግብ ራስን መቻል አስመልክቶ የሚያስከትለዉን ተጽዕኖ የሚዳስስ ይሆናል፡፡

# 1. አገራዊ ዓውድ

በአፍሪካ ካሉት አገራት ኢትዮጵያ በባህል፣ በቋንቋ እና በታሪክ በአያሌው የተለየች አገር ነች፡፡ ባለፈው ዓመት በተደረገው የተባበሩት መንግሥታ የልማት ፕሮግራም (UNDP) የሰብዓዊ ልማት አመልካች (Human Development Index) የደረጃ ምደባ ከ169 አገራት 157ኛውን ሥፍራ በማያዝ “በልማት ወደኋላ የቀሩ” ከሚባሉት አገራት ልትመደብ ችላለች፡፡[7] ከአጠቃላይ ሕዝቧ አብዛኛው በድህነት የሚኖቅቅ ሲሆን 81 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ዕለታዊ ገቢው ከ2 የአሜሪካን ዶላር ያነሰ ነው፡፡ ሥር የሰደደ የምግብ እጥረት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሕጻናትን ዕድገትና የመኖር ኅልውና ላይ አደጋ ጥሏል፤ ከዚህም ባሻገር 13 ሚሊዮን የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ አስከፊ ለሆነ የምግብ ተጋልጠዋል፡፡[8]

## 1.1 ማኅበረሰባዊ ዓውድ

### የሕዝብ ብዛት

በ2003ዓም በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ እንደታወቀው የኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት 85 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን ይህም አሓዝ አገሪቷን በሕዝብ ብዛት ከአፍሪካ ሁለተኛ እንድትሆን አድርጓታል፡፡[9] አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኖረው በገጠር ነው፤ ይህም ደግሞ ከሕዝቡ ብዛት 83 በመቶ የሚሆነውን የሚሆን የሚሆል ነው፡፡ ከሕዝብ አሰፋፈር አኳያ በአንድ ካሬ ኪሎሜትር 66 ሰዎች መኖራቸው በዓለም ሕዝብ ጥቅጥቅ ብሎ ከሰፈረባቸው አገሮች በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት ማካከል ያደርጋታል፡፡ 85 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ በደጋ ሥፍራዎች የሰፈረ ሲሆን አሰፋፈሩም በአንድ ካሬ ኪሎሜትር 150 ሰዎች በማሆን ነው፡፡ አብዛኛው ሕዝብ የዕለት ጉርሱን የሚያገኘውም በአነስተኛ እርሻዎች ላይ በማሳሜራት ነው፡፡

### ብሐረሰብና ቋንቋ

ኢትዮጵያ የተለያዩ ዝርያዎች ኅብር መኖሪያ አገር ነች፡፡ በአገሪቷ ወስጥ አብላጫውን የሚይዘው የኦሮሞ ተወላጅ ሲሆን ይህም ከአጠቃላዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ 34.5 በመቶ ነው፡፡ በመቀጠልም አማራ 26.9 በመቶ፣ ሶማሊ 6.2 በመቶ፣ ትግሬ 6.1 በመቶ በማሆን ቀሪዎቹን ዋንኛ ቡድኖች ይመራሉ፡፡[10] አማርኛ ብሐራዊ ቋንቋ ሲሆን በ27 ሚሊዮን ሰዎች ይናገሩታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በደርዘኖች የሚቆጠሩ የአካባቢ ቋንቋዎችና ዘዬዎችም ይነገራሉ፡፡

### የዜና ማሰራጫ

ኢትዮጵያውያን መረጃ የሚያገኙበት ዋንኛው መንገድ ራዲዮ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የሬዲዮ ጣቢያዎችና ብቸኛው የቴሌቪዥን ማሰራጫ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ናቸው፡፡ የኅትመት (የጋዜጣ) ስርጭት ደግሞ በከተሞች አካባቢ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ በ1999 ዓም አካባቢ የግል ጣቢያዎችን የሚቋቋም አዋጅ የወጣ ቢሆንም በሁሉም ቦታዎች ግለ-ሳንሱር ተግባራዊ ተደርጎ ይስተዋላል፡፡[11] ከአጠቃላይ ሕዝብ 445,000 የሚሆነው ማለትም 0.5 በመቶ የሚሆነው የመረጃ መረብ (የድረገጾች) ተጠቃሚ ነው፤ ይህም አሓዝ ኢትዮጵያን ከሰሃራ በታች ከሚገኙ አገራት የሚጨረሻውን ሥፍራ ላይ የምትገኝ አገር ያደርጋታል፡፡[12] ከዚህ በተጨማሪም በመረጃመረብ ላይ የሚደረገው ሽበባ እጅግ የተስፋፋ ከመሆኑ ባሻገር ነጻ የመረጃ ፍሰት ሕጎች[13] ተግባራዊ ባለመሆናቸው፤ ለሕዝብ ፍጆታ የሚቀርበው መረጃ በጣም ወሱን ነው፡፡ መንግሥትም አፌሴላዊ የሆኑ ጉዳዮችን ሽፋን በተማለከተ ኃላፊነቱን በቁጥጥሩ ሥር ለሚገኘው የዜና ማሰራጫ ብቻ የተፈቀደ እንዲሆን አድርጓል፡፡[14] ጋዜጠኞች እንደ ወንጀለኛ (አሸባሪ) ማካሰሳቸውና

ያለበቂ ምክንያት ማሳሰራቸው ግለ-ሳንሱር እንዲስፋፋ ዓይነተኛ ምክንያት ፈጥሯል፡፡ በመሆኑም በመንግሥትና በጋዜጠኞች መካከል ያለው ግንኙነት በአብዛኛው ውጥረት የተሞላበት ነው፡ ድንበር የለሽ ዘጋቢዎች (Reporters without Borders) የተሰኘው ድርጅት እንደሚለው ከሆነ በግሉ የዜና ማሰራጫ ላይ "የሞቋርጥ ጭቆና" እንደሚደርስበት ይናገራል፡፡[15]

## 1.2 ፖለቲካዊ ዓውድ

የኢትዮጵያ መንግሥታዊ አወቃቀር በዘር ላይ የተመሠረተ ፌደራላዊ ሪፑብሊክ ሲሆን ይህም 9 በዘር (ጎሣ) ላይ የተሚኮዙ ክልሎችን ያካተተ ነው፡ እነዚህ ክልሎች በወስጣቸው ለሚገኙ የተለያዩ የኢትዮጵያ ዘሮች (ጎሣዎች) የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰንን መብት እና የራስ ገዝ መብት እንዲሰጡ ሆነው ነው የተዋቀሩት፡፡

ደርግ በ1983 ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) አማካኝነት አገሪቷን በመቆጣጠር አሜሩሩን እስካሁን ይዞ ይገኛል፡፡[16] በማለስ ዜናዊ የሚሞራው ኢህአዴግ በግንቦት 2002 ዓም ለአራተኛ ጊዜ አሸንፎ ከበፊቱም አብላጫ የነበረውን አሜሩር እጅግ ከፍ አድርጎታል፡፡ በ1997 በተደረገው ምርጫ ኢህአዴግ አሸነፈ ቢባልም በርካታ የተዛቡ የምርጫ ሁኔታዎች፤ በድኅረ-ምርጫ ወቅት የተከሰቱ ግድያዎች እንዲሁም የጋዜጠኞችና የፖለቲካ ፓርቲ ሜዎች ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲታሰሩ ሆነዋል፡፡ እስካሁን በሥልጣን ላይ የሚገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ከደርግ ጋር በተደረገው ሽምቅ ወጊያ ተሳታፊ እንደነበሩ ይወሳል፡፡ (እንደሚታወቀው ደርግ ከ1966 እስከ 1983 ድረስ በሥልጣን ላይ ቆይቷል፡፡)

### ከተቃዋሚ እስከ መንግሥት

በ1997 ከተካሄደው ምርጫ ጊዜ ጀምሮ መንግሥትም ሆነ የሚከተለውን ፖሊሲ በዝምታ የሚያታለፍ ጉዳይ ሆኗል፡፡ መንግሥትን የሚቃወሙ ስለሚደርስባቸው እንግልት፣ ግፍና እስር በዘገባ ሜለክ የተዘጋጁ ብዙ ማስረጃዎች አሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የመንግሥት ተቃዋሚ መሆን የሚያስፈራ ባሕል በመሆን እየዳበረ መጥቷል፡፡ እንዲህ ዓይነት የፍርሃት ድባብ ባጠለበት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ፋይዳ ያለው ለውጥ ማምጣት ካለመቻላቸው አልፎ በወስጣቸው ያለው ሽኩቻ ሥራቸውን በብቃት እንዳይወጡ ዕንቅፋት ሆኖባቸዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ወጪ በርካታ የዳያስፖራው ተቃዋሚ ቡድኖች የመንግሥትን ፖሊሲዎች ሲቃወሙ፥ በኢትዮጵያ ለውጥ እንዲመጣ ሲውተወቱ እንዲሁም ኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶችን በመተለከተ ያለችበት ሁኔታ ምን እንደሚመስል ዓለምአቀፍ ግንዛቤ እንዲኖር እየጎተጎቱ ይገኛሉ፡፡

### የሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ

የ1987ቱ የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት እንዲሁም አሁን በሥራ ላይ ያሉ ሌሎች ድንጋጌዎች የሰብዓዊ መብት አጠባበቅን በተለመከተ ጠንካራ ይዞታ አላቸው፡፡[17] አለመታደል ሆኖ ግን እነዚህ ሁሉ ሕጎች እንደሚገባው አልተተገበሩም፡፡ ተዓሚኒነት ባላቸው ነጻ ድርጅቶች በተከታታይ የተደረጉ ምርሜራዎች በኢትዮጵያ ያለው የሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ከመግለጽ ባሻገር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰበት እንደመጣ ይጠቁማሉ፡፡ በ2000ዓም አካባቢ የወጣው በተባበሩት መንግሥታት የዓለምአቀፍ የዘር መድልዖ አስወጋጅ ጉባዔ (ICERD) የሚቆጣጠረው ኮሚቴ የኢትዮጵያ ወታደሮች "ከዚህ በፊት በተጠና በሚመስል ሜለኩ" የአንድ ብሔረሰብ አባላት ላይ በማነጣጠር ጥቃት ስለሚደረሳቸው ዘግቦ ነበር፡፡ በዘገባው የተጠቀሰው ማስረጃ እንደሚጠቁመው "ጅምላ ጭፍጨፋ፣ በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ግዳጅ ወሲብ፣ ያለፍርድ ማሰር፣ ማሰቃየት፣ ማዋረድ፣ የነዋሪወን ንብረትንና ሰብልን ማውደም" የመሳሰሉ ተግባራት ስለሚፈጸማቸው ማስረጃው ይጠቁማል፡፡[18]

ከዚህ በተጨማሪም በ1997 ዓም የሰብዓዊ መብት ጥበቃ "*በኢትዮጵያ በጋምቤላ ክልል አኙዋኮችን ያነጣጠረ የሰብዓዊ መብት ጥሰትና*

*በሰብዓዊ ፍጡር ላይ የተፈጸመ ወንጀል"* ("Targeting the Anuak: Human Rights Violations and Crimes against Humanity in Ethiopia's Gambella Region,") በሚል ርዕስ ያወጣው ዘገባ በአኙዋኮች ላይ የተፈጸመውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት በስፋት የሚዳስስ ነው፡፡ በተለይም በ1995 የኢህአዴግ የደኅንነት ኃይሎች እና ሌሎች ቡድኖች በጋምቤላ ክልል ለ424 አኙዋኮች መገደል እንደምክንያት ተጠያቂ እንደሚሆኑ በስፋት ያብራራል፡፡ በርካታዎች ታስረዋል፤ አሰብዓዊ ግፍ ተፈጽሞባቸዋል፤ ተደብድበዋል፤ ከ 8ሺህ እስከ 10ሺህ የሚሆኑት ደግሞ ወደጎረቤት አገር ሱዳን ተሰድደዋል፡፡ ይህ እንግዲህ ለረጅም ጊዜ በተከታታይ በአኙዋኮች ላይ ሲደርስ ከነበረው ስደት አንዱ ክፍል ነው፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ስደት ዋንኛ ምክንያት የአኙዋክ ምድር ያለው ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ መሆኑ እንደ ምክንያት ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡ [19]

በተባበሩት መንግሥታት የንዑሳን ጉዳዮች (UN's Independent Expert on Minority Issues) ኤክስፐርት የሆኑት ጌይ ማክዱጋል በ1999 ያወጡት ዘገባ "ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ አናሳ ማኅበረሰቦች በሚሊዮ ማስፈር፣ ከቦታ በሚፈናቀል፣ በግጭት፣ በወህደት፣ በባሕል ወህደት፣ በአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮችና ሜሬት በማጣት ምክንያት ከምድረገጽ ፈጽመው እንደጠፉ" ያትታል፡፡ ወደፊት በዚሁ ሪፖርት ላይ በስፋት የሚዳሰስ ጉዳይ ሲሆን በኢትዮጵያ አብዛኞዎቹ በሊዝ የተሰጡት ሰፋፊ ቦታዎች በተለምዶ በጉምዝ፣ በአኙዋክ፣ በኦሮሞና በሌሎች ሕዝቦች ሰፍረውባቸው ይኖሩ የነበሩ ስፍራዎች ናቸው፡፡ ይህም ሜሬቱ በአሁኑ ወቅት ከሚታየው ወስብስብ ችግር በተጨማሪ የአካባቢውን የማኅበረሰባዊና ፖለቲካዊ ጉዳይ የተባባሰ ደረጃ ላይ እንዲደርስ እያደረገው ይገኛል፡፡ በርካታ በተለያየ ቦታዎች የሚኖሩም ለተመሳሳይ ሁኔታ የመጋለጣቸው ሁኔታ እያሳሰባቸው መጥቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዘገባው እንደሚለው በኦሮሚያ ክልል ወስጥ የሚገኙት የከረዩዎች ዛላኖች (አርብቶአደሮች) በተለምዶ ከሚኖሩበትና የውሃ ምንጫቸው ከሚገኝበት ቦታ እንዲፈናቀሉ መደረጋቸውን ይናገራል፡፡ በኦሞ ሸለቆ ወስጥ በ1.7 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚገነባው የጊቤ ሦስት ግድብ በደቡብ ኦሞ እያስከተለ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን በሚገባ በሚገኝ ተቀምጦ ይገኛል፡፡ ዓለምአቀፍ ተቃውሞ እየደረሰ ቢሆም ኢትዮጵያ ግን በግድቡ ግንባታ ገፍታበታለች፡፡ (ስለ ኦሞ ሸለቆ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሣጥን "ሀ" ይመልከቱ)፡፡ [20]

ከዚህ በተጨማሪም ትርጉማዊ የፖለቲካ ተቃውሞን ወይም የሚቀርቡ ነጻ ትችቶችን አጥብቆ የመቃወም (ያለመቀበል ባሕል) ሁኔታ እያደገና እየጠነከረ መጥቷል፡፡ ከ1997 ምርጫ በኋላ ከተከተሰተው አፈና፣ አመጽና እስር በተጨማሪ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት በየጊዜው መንግሥትን በሚቃቹ ወይም ተቃዋሚ ናቸው ብለው የሚያምኗቸውን ማንገላታት፣ ማሰር፣ ማስቃየትና ግፍ መፈጸማቸውን ቀጥለውበታል፡፡ በርካታ የተቃዋሚ ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞች እና ምሁራን ለእስር ተዳርገዋል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን በጎበኛቸው ማኅበረሰቦች በሙሉ መንግሥትን መቃወም በጣም የሚያስፈራ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የመንግሥትን ፖሊሲዎችንና ራሱን መንግሥትን አለመደገፍ እጅግ የሚያስፈራ ነገር መሆኑን ለማንዘብ ችሏል፡፡ ከመኖሪያ ቦታቸው ከተፈናቀሉ ግለሰቦች መካከል አንዱ አባወራ ለዚህ የጥናት ቡድን በሰጠው መረጃ መሠረት የሚኖርበት ክልል ፕሬዚዳንት ራሳቸው "ወይ መንግሥትን ብትደግፍ ይሻልሃል አለበለዚያ ያለህን ሁሉ ታጣለህ" በማለት በቀጥታ እንዳስጠነቀቁት ተናግሯል፡፡

የሰብዓዊ መብት ጥበቃ Human Rights Watch (HRW) ድርጅት በሶማሊ ክልል በኦጋዴን በሰላማዊ ሰዎች ላይ ለተፈጸመው የጦር ወንጀል በተገቢው መሠረት ሳይጠየቁ የቀሩት አስመልክቶ ለኢትዮጵያ ከፍተኛውን ዕርዳታ የሚሰጡትን አገራት አሜሪካንን፣ የአውሮጳ ኅብረትንና እንግሊዝን አጥብቆ ወቅሷል፡፡ [21]

**ስቃይን የሚቃወመው የተባበሩት መንግሥታት ኮሚቴ (The UN's Committee Against Torture) በህዳር ወር 2003 ዓም ባወጣው ሚኘጃ መሠረት "በአሁኑ ጊዜ የፖለቲካ ተቀናቃኞች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት፣ ተማሪዎች፣ በአሸባሪነት ተጠርጥረው የተወነጀሉ፣ የአርነት ንቅናቄ ቡድኖች ደጋፊዎች ወዘተ በተለያየ ዓይነት፣ ተከታታይነት ባላቸው፣ ተመሳሳይና ቀጣይ በሆኑ መንገዶች በፖሊሶች፣ በእስርቤት ኃላፊዎች እና በደኅንነት ኃይላት እንዲሁም በጦር ሠራዊት መኮንኖች ጭካኔ የተሞላበት ስቃይና መከራ እየደረሰባቸው"[22] መሆኑ እንደሚያሳስበው ገልጾ ነበር፡፡**

በ2000 ዓም የኢትዮጵያ መንግሥት "የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የማኅበራት አዋጅ" ያወጣ ሲሆን ይህም አዋጅ ቁጥር 621/2001[23] ተብሎ የሚጠቀሰው ነጻ የሆኑትን የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችን ተግባራት እንደወንጀል በመቁጠር መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (ማድ) ሥራ ወስጥ ጣልቃ የሚገባና የሚቆጣጠር አዋጅ ነው፡፡ ይህም በማታወጁ ምክንያት በአገር ወስጥ የነበሩ የተለያዩ ማዶች የታገዱ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔና የኢትዮጵያ ሕግ ባለሙያ ሴቶች ማነበር ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## የወጪ ፖሊሲ

ኢትዮጵያ የአሜሪካና የአወሮጳወያን ጠቃሚ ወዳጅ መሆኗ በብዙዎች ዘንድ ይታወቃል፡፡ በአሜሪካና በኢትዮጵያ መካከል ባለው የሁለትዮሽ ግንኙነት መሠረት አሜሪካ ለኢትዮጵያ ሠራዊት የምታደርገወን ዕርዳታ ጨምሮ በየዓመቱ 526 ሚሊዮን ዶላር የምትሰጥ ሲሆን ይህም ከዓለምአቀፉ የድጎማ ማጠን 26.1 በመቶ የሚሸፍን ነው፡፡ (ይህም ከ1995 – 2000 ባሉት ዓመታት የሰጠችው ዕርዳታ አማካይ ተወስዶ ነው) ሌሎች በዋንኛነት የሚጠቀሱ ለጋሾች፡ የዓለም ባንክ (428 ሚሊዮን ዶላር ወይም 21.2 በመቶ)፣ የአወሮጳ ኅብረት (14.2 በመቶ)፣ ታላቋ ብሪታኒያ (9.3 በመቶ)፣ ካናዳ፣ ጀርመን እና ጣሊያን (እያንዳንዳቸው ከ3.6 እስከ 4.8 በመቶ)[24] ናቸው፡፡ በዚህ አለሚጋጋት በሰፈነበት ቀጣና እነዚህ ለጋሽ መንግሥታት ኢትዮጵያን እንደ ዋንኛ ወዳጅ አድርገው የሚቆጥሯት ሲሆን በተለይ አሜሪካ ደግሞ "በአሸባሪነት ላይ በምታደርገው ዓለምአቀፋዊ ጦርነት"[25] ዋንኛ ተባባሪዋ አድርጋ ነው የምትወስዳት፡፡

ኢትዮጵያ አጎራባቾቿ ከሆኑት ኤርትራ፣ ሱማሊያ (በቅርቡ ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጋር ጦርነት ገጥማ እንደነበር ያስታውሷል) እና በማጡ ከኬኒያ ጋር በድንበር ጉዳይ ላይ የተካረረ ሁኔታ ወስጥ ትገኛለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የአባይን ወንዝ አጠቃቀምና በተፋሰስ ከሚያካልላቸው አገራት በተለይ ከግብጽ ጋር በተወሰነ ሜሌኩ ደግሞ ከሱዳን ጋር አስጊ ሁኔታ ወስጥ ገብታለች፡፡ ይህ ጉዳይ በተለይ ግብጽ በአባይ ላይ ያላት ከፍተኛ ጥገኝነት ከሌሎቹ የአባይ ተፋሰስ አገራት ካላቸው ጥቅም ጋር ተዳምሮ በተቃራኒው ደግሞ ኢትዮጵያ አባይን ለማጠቀም ያላት

## ሳጥን ሀ፡ የደቡብ ኦሞ ሸለቆ ታሪክ

በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የሚገኙት አገር በቀል ቡድኖች በአፍሪካ ቀደምት ባሕል ካላቸው ቡድኖች መካከል ዋንኛ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በቦታው አያሌ ትናንሽ የጎሣ ቡድኖች ሲኖሩ እነዚህም በፖለቲካው ወስጥ ወከልና የሌላቸው በጣም የተናቁና የተገለሉ ናቸው፡ አብዛኛዎቹ የኦሞን ወንዝ ተከትለው የሚኖሩና በጎርፍ–ደለል የእርሻ ዘዴ የሚጠቀሙ ዘላኖች (አርብቶአደሮች) ናቸው፡ በኢትዮጵያ ወስጥ ካሉት አገር በቀል ጎሳዎች መካከል የእነርሱ አኗኗር በአደገኛ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡ የማደር ምክረታ፣ የፓርኮች አስተዳደር፣ ማጠ ስፊ የሆነው የጊቤ ሶስት የሃይድሮኤሌክትሪክ ግንባታ፣ የኢሌሚ ትራያንግል (ሦስት ጎን) ክርክር[26] አሁን ደግሞ ንግድ ተኮር የሆነ እርሻን ለማስፋፋት በሚ የሚኬዱት ተግባራት በሙሉ የእነዚህን ጎሣዎች የመኖር ህልወና አደጋ ላይ ጥለውታል፡፡

የጊቤ ሦስት ግድብ ግንባታ በዓለም ዙሪያ የሚዶችንና የወጪ ማግሥታትን ትኩረት የሳበ ጉዳይ ነው፡ ይህ ግድብ ከአፍሪካ ረጅሙ ሲሆን 1870 ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ማምጨት የሚችልና ለአጎራባች አገራት በሽያጭ ሚለክ የሚዳረስ ብቃት ያለው እጅግ ግዙፍ ግድብ ነው፡ የዚህም ግንባታ በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ ያለው ተጽዕኖ በርካታ ነው፡ ከሚኖሪያ ቀዬ ሚናቀል፣ በህይወት ለመኖር ወሳኝ የሆነወን የጎርፍ–ደለል እርሻ እና በኬንያ የሚገኘው የቱርካና ሃይቅ ማጠን መቀነስ ጥቂቶቹ ናቸው፡

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ በአካባቢው አትራፊ ሰብሎች ለማምረት በተያዘው ፕሮግራም መሠረት ሰፋፊ ቦታዎችን በማስኖ ለሚልማ ታቅዷል፡፡ ባሁኑ ወቅት የሚሬት ይዞታን ለባለሃብቶች እየሸነሸነ የሚሠጠው የፌደራሉ የሚሬት ባንክ 180ሺህ ሄክታር ሚሬት ለንግድ እርሻ ሥራ እንዲውል መድቧል፡፡ እነዚህ የሚሬት ይዞታዎች ጥጥ፣ ሰሊጥ፣ የተለያየ ዓይነት ለወዝ፣ ፍራፍሬ፣ አኩሪአተር፣ ሽንኮራአገዳና ከዘንባባ የሚገኝ ዘይት ለማምረት የሚችሉና "ለማስኖ የተዘጋጁ" ናቸው በማለት የፌደራሉ ማግሥት ለሽያጭ እያስተዋወቃቸው ይገኛል፡፡ ይህ የሚሬት ይዞታ እስካሁን ለባለሃብቶች የተሰጠዋ እንዲሁም ክልሎች ባላቸው ሥልጣን መሠረት እስከ 5000 ሄክታር ሚሬት እንዲሰጡ በሕግ የተፈቀደላቸዋ የሚጨምር አይደለም፡ ምንም እንኳን ለጥናት ቡድኑ የቀረበለት ካርታ በግልጽ የሚያሳይ ባይሆንም እነዚህ ለኢንቨስትመንት የተዘጋጁ ቦታዎች ከኦሞ ብሔራዊ ፓርክ እንዲሁም ከሚሰዎችን የአደን ቦታዎች ጋር እንደሚቋራረብ በግልጽ ይታያል፡፡

ይህ እየሆነ ባለበት ወቅት እነዚህ አገር በቀል ጎሣዎች ከትወልድ ሥፍራቸው በማግሥት አስገዳጅነት እየተነሱ በሌሎች ማደሮች እንዲሰፍሩ እየተደረገ ነው፡ ከአካባቢው የሚጣኑ ዘገባዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነ ይህ ድርጊት እየተካሄደ ያለው በሌሎች ቆላማ ክልሎች ሳይሆን በክልሉ በሙሉ በ1997ዓም አካባቢ ዓለምአቀፋዊ ወዝግብ አስንስቶ ነበር፡፡ በዚያን ወቅት የኦሞን ብሔራዊ ፓርክ በተገቢው ሁኔታ ለማስተዳደር በሚል ማግሥት በርካታ አገር በቀል ጎሣዎችን ከትወልድ መኖሪያቸው እንዳፈናቀለ ይታወሳል፡፡ ሆኖም የአለምአቀፍ ኅብረተሰብ ተቃወሞ ባደረሰው ተጽዕኖ ምክንያት ፓርኩን ሊያስተዳድር የነበረው ድርጅት ፓርኩን ትቶ በመውጣቱ ፓርኩ አሁን እንደሚያየው በአብዛኛው ከጥቅም ወጪ ሆኖ (ባክኖ) ቀርቷል፡፡

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባልደረባ የሆኑት አቶ አበራ ደረሳ ". . . ጉዳዩን ጠቅለል አድርገን ስናየው ዘላኖች በየሜዳው ወስጥ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ እንዲኖሩ አንፈልግም፡ አርብቶአደርነት ቀጣይነት ያለው ወይም በራሱ መኖር የሚችል አይደለም፡ . . . ስለዚህም የሥራ ዕድልን ለመፍጠር፣ አካባቢወን ለማለወጥ፣ ግብርናን በዘመናዊ መሣሪያዎች በማገዝ ንግድ ተኮር እንዲሆን ሚድረግ አለብን"[27] በማለት የተናገሩት ማግሥት በጉዳዩ ላይ ያለወን አቋም ጠቅለል አድርጎ የሚያሳይ ነው፡

እንደ እወነቱ ከሆነ እነዚህ አገር በቀል ነዋሪዎች ወደት ሊሄዱ እንደሚችሉ ማመት በጣም አዳጋች ነው፡ በአካባቢው የጎሣ ግጭት ከቁጥጥር ወጪ በሆነ ሚልኩ የተስፋፋ በሙሉ በርካታዎቹ ጎሣዎች ወደ ኬንያና ሱዳን የሚሻሻቸው ሁኔታ አስተማማኝ አይደለም፡ በመሆኑም የመኖር ህልወናቸው እያከተመ

እትብታቸው የተቀበረበት ምድር እየጠፉ በሜዱ የሚሰበት ምንም ሥፍራ የላቸውም፡ አንድ የአገሬው አዛወንት እንዳሉት "ባሕላችንን እያጣን ነው፡

በመሆኑም ለቀጣዩ ትወልድ የምናስተላልፈው ምንም ነገር የለንም፡ ለልጆቻችን የምንናገረው ታሪክ አሁን ካለው ትወልድ የሚያልፍ አይመስለኝም፡"[28]

ፍላጎት ሲደሚርበት ጉዳዩ የሁሉንም ትኩረት የሚስብ ከፍተኛ የወጭ "አባይና የሚሬት ኢንቨስትመንት" በሚል ርዕስ ሳጥን "ኘ" ላይ ፖሊሲ ጉዳይ እንደሚሆን መተንበይ አያዳግትም፡ (ለተጨማሪ ማብራሪያ የተጻፈወን ይመልከቱ፡፡)

## 1.3 የልዕለምጣኔሃብት (ማክሮኢኮኖሚክስ) ዓውድ

ከ1984 ዓም ጀምሮ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ 5.6በመቶ እንዳደገ ይነገራል፡፡ በሚፎዎቹም ዓመታት የኢትዮጵያ የአገር ወስጥ ምርት በከፍተኛ ማጠን እያደገ እንደሚሄደም በሰፊው ይጠበቃል፡፡ መንግሥት በሚያወጣው ስታቲስቲካዊ መረጃ መሠረት ባለፉት አምስት ዓመታት የአገር ወስጥ ምርት የሁለት አኻዝ ዕድገቱን ጠብቆ የቆየ መሆኑን የሚዘግብ ሲሆን ይህም ነዳጅ ከማያመርቱ የአፍሪካ አገራት መካከል ከፍተኛውን ሥፍራ ይዞ ይገኛል፡፡ በከፍተኛ ማጠን እየጨመረ ካለው የሕዝብ ቁጥር ጋር የኢኮኖሚው ዕድገት ሲነጻጸር በ1997ዓም አከባቢ ከነበረው የ146 ዶላር የነፍስወከፍ የአገር ወስጥ ምርት ዕድገት በ2000/2001ዓም ወደ 220 ዶላር ከፍ ማለቱ የኢትዮጵያ ምጣኔሃብት በማጡኑ የሚያስገርም ዕድገት አሳይቷል ሊባል ይችላል፡፡ ሆኖም ግን በሃብታምና ደሃ መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ መምጣት፣[29] የዋጋ ግሽበት ሚጨምር (የዋጋ ግሽበቱ በ2000ዓም 64በመቶ ደርሶ ነበር)፣ እንዲሁም የወጭ ምንዛሪና የምግብ ክምችት በአስደንጋጭ ሁኔታ ማሽቆልቆል (ምንም እንኳን ባለፉት ሁለት ዓመታት መሻሻል ቢያሳይም) እነዚህ ሁሉ እየተከሰቱ ያሉት ኢኮኖሚው እያደገ ነው በሚባልበት ሁኔታ ወስጥ ነው፡፡

### በተለያየ አቅጣጫ የምጣኔሃብት (ኢኮኖሚ) መስፋፋት

የኢትዮጵያ ምጣኔሃብት መሠረት ያደረገው አነስተኛ ማጠን ባላቸው የግብርና ተግባራት ነው፡፡ ሆኖም ባለፉት አምስት ምጣኔሃብቱን በፍጥነት የማስፋፋት አካሄድ (አዝማሚያ) ተመዝግቧል፡፡ ከአገር ወስጥ ምርት ግብርና አሁንም ማጠነኛውን ትርፍ እያስመዘገበ የሚገኝ ቢሆንም የአገር ወስጥ ምርት ድርሻው ግን በቀስታ እየቀነሰ ሲመጣ የአገልግሎት ዘርፉ ግን እየጨመረ እንዲያወም በ2000/2001 ዓም ለመጀመሪያ ጊዜ ከግብርናው በልጦ ታይቷል፡፡ (አገልግሎት 45.1 በመቶ፤ ግብርና 43.2 በመቶ) ይህ የዕድገት ሁኔታ ለሚቀጥሉት በርካታ ዓመታት በዚሁ እየቀጠለ እንደሚሄድ ትንበያዎች ቢኖሩም የግብርናው ክፍለኢኮኖሚ የሥራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ የነበረውን የበላይነት (አንዳንዶች እስከ 80በመቶ ያደርሱታል)[30] ግምት ወስጥ ሳይከተት የተደረገ ስሌት ነው፡፡

### ሥር እየሰደደ የመጣ የንግድ ኪሣራ

ከዚህ በታች በተቀማጠው ሠንጠረዥ ላይ እንደሚታየው ባለፉት አምስት ዓመታት ወደ ወጪ የተላከው ምርት በአገራት ብዛትም ሆነ በምርት ዓይነት ከፍተኛ ለወጥ ያሳየ መሆኑን ነው፡፡[31] ከ50 ሚሊዮን ዶላር የሚሆነው የወጪ ንግድ የባቄላ ዓይነቶችን፣ የዘይት ዘሮችን፣ ጫት፣ ወርቅ፣ የአበባ ምርትን እና የቆዳ ወጤቶችን የሚጨምር ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአበባ ምርት ከኢትዮጵያ የወጪ ምርት ከፍተኛውን ቦታ እየያዘ የመጣ ሲሆን በ1993 ዓም

**ሠንጠረዥ 1፡ የኢትዮጵያ የንግድ ሚዛን**

| ዓም | የወጪ ንግድ | የገቢ ንግድ | የንግድ ሚዛን (ልዩነት) |
|---|---|---|---|
| 1999/2000† | 486* | 1611 | -1125 |
| 2000/2001 | 463 | 1557 | -1094 |
| 2001/2002 | 452 | 1696 | -1244 |
| 2002/2003 | 483 | 1856 | -1373 |
| 2003/2004 | 600 | 2587 | -1987 |
| 2004/2005 | 818 | 3633 | -2815 |
| 2005/2006 | 1001 | 4593 | -3592 |
| 2006/2007 | 1189 | 5128 | -3939 |
| 2007/2008 | 1466 | 6811 | -5345 |
| 2008/2009 | 1447 | 7552 | -6105 |
| 2009/2010 | 1736 | 7836 | -6100 |

| |
|---|
| ማስሰቢያ፡ |
| †ዓመቶቹ እንደ አወሮጳወያን አቆጣጠር፤ |
| *ቁጥሮቹ ደግሞ በሚሊዮን ዶላር ናቸው፡፡ |
| ምንጭ Access Capital: 2010 Eth Macro Handbook |

ከነበረው የ300 ሺህ ዶላር የወጪ ምርት ዋጋ በ2000 ዓም 150 ሚሊዮን ዶላር[32] በመድግ ከአጠቃላይ የወጪ ንግድ 10 በመቶ መሆን ችሏል፡፡ ከአበባ ምርት 80 በመቶ የሚሆነው ወደ አወሮጳና አሜሪካ የሚሄድ ሲሆን ወደ ወጪ ከሚላከው የሥጋ ምርት 50 በመቶ ከሚሆነው የሚሄደው በኢትዮጵያ ወስጥ በሥጋ ምርት ላይ ከፍተኛ መዋዕለንዋይ ወዳፈሰሰው አገር ሳውዲ አረቢያ ነው፡፡ (ሳውዲ አረቢያ ኤልፎራ አግሮ–ቢዝነስ ተብሎ በሚጠራው የሞሃመድ አላሙዲ ኩባንያ አማካኝነት ነው ይህንን ተግባራዊ እያደረገች የምትገኘው)

ከዚህ በተጨማሪም ከ1998/1999 ጀምሮ ከቻይና፣ ሕንድ እና መካከለኛው ምስራቅ የሚመጣው የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት (FDI) ከ14 በመቶ ወደ 24 በመቶ ያደገ ሲሆን ወደነዚህ አገራት የሚደረገው የወጪ ንግድ ደግሞ ከ23 በመቶ ወደ 33 በመቶ አድጓል፡፡[33]

ምንም እንኳን ባለፉት ጥቂት ዓመታት ንግድ ላይ ያተኮረ የእርሻ ኢንቨስትመንትና የወጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እየጨመረ ቢሆንም አብዛኛዎቹ የእርሻ ሜዳዎች ገና ማምረት ባለመጀመራቸው ምክንያት በወጪ ንግድ ላይ ገና ትርጉም ያለው ተጽዕኖ ማምጣት አልጀመረም፡፡

**ሣጥን ለ፡ ሳውዲ አረቢያ፣ የከብት ወጪ ንግድና ሞሐመድ አላሙዲ[34]**

በኦሮሚያ ክልል የሚገኘው ኤልፎራ አግሮ–ቢዝነስ የተባለው ኩባንያ በኢትዮጵያ የከብት ኃብት ልማት ላይ ከተሰማሩ ኩባንያዎች ሁሉ ትልቁ ነው፡፡ ኩባንያው የተቋቋመው የመንግሥት ንብረት የሆነው የከብት ሃብት ልማት ድርጅት በትወልድ ኢትዮጵያዊ ለሆኑትና አሁን የኩባንያው ባለቤት ለሆኑት የሳውዲ ቢሊዮነር ሞሐመድ አላሙዲ በተሸጠበት ጊዜ ነበር፡፡ የኤልፎራ ታላላቅ የከብት ማድለቢያዎች ባሁኑ ጊዜ 65ሺህ ከብቶችን እንዲሁም 400ሺህ በጎችንና ፍየሎችን በየዓመቱ ማርባት የሚችል ዓቅም አለው፡፡ ኩባንያው ምርቱን በአገር ወስጥ ለታላላቅ ሆቴሎች፣ ለተለያዩ ድርጅቶችና ለወታደራዊ ተቋማት የሚያቀርብ ሲሆን ወደ ወጪ ደግሞ ለባሕረ ሠላጤው አገራት ይልካል፡፡ ምንም እንኳን መንግሥት ያወጣው ፖሊሲ ዘላኖችን (አርብቶአደሮችን) ከመኖሪያ ቦታቸው በግድ እንዳይፈናቀሉና እንዳይነሱ ጥበቃ የሚያደርግ ቢሆንም ኤልፎራ ሥራውን ከጀመረ ወዲህ በቦረና የሚገኙ አርብቶአደሮች በደረቅ ወራት የሚጠቀሙበትን የግጦሽ ቦታዎች አጥተዋል፡፡

ኤልፎራ የሚለው ስም የተገኘው ከሁለት የቦረና ኦሮምኛ ቃላት ሲሆን ኤላ ማለት "ቋሚ የውሃ ቦታ" ማለት ሲሆን ፎራ ማለት ደግሞ "የዝናብ ወቅት የግጦሽ ቦታ" ማለት ነው፡፡

## የወጪ ዕዳ

የዓለም ባንክና ዓለምአቀፉ የገንዘብ ድርጅት ባደረጉት የዕዳ ይቅርታ (ስረዛ) ምክንያት ኢትዮጵያ ያላት የወጪ ዕዳ በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል፡፡ በ1993 የኢትዮጵያ የወጪ ዕዳ በአገር ወስጥ ከምታመርተው ጋር ሲነጻጸር 90 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2000ዓም ግን ይህ ቁጥር በ12 በመቶ ቀንሷል፡፡ ይህም አነስተኛ የዕዳ ማጠን ማንግሥት ለመሠረተልማት የሚያወጣውን ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር አድርጎታል፡፡ በዚህም ምክንያት ከ1995 እስከ

2000 ባሉት ዓመታት (የዋጋ ግሽበት ከግምት ወስጥ ሳይገባ) ማንግሥት የሚያወጣው ወጪ ከ1.3 ሚሊዮን ዶላር ወደ 2.8 ሚሊዮን ዶላር በእጥፍ አድጓል፡፡ ይህም ማለት ከ21 ሚሊዮን ብር ወደ 47 ሚሊዮን ብር ማሆኑ ነው፡፡[35]



የበቆሎ ምርት በጋምቤላ

## የወጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት (FDI)

ወደ ኢትዮጵያ የሚገባው የወጪ ኢንቨስትመንት በ1992ዓም 135 ሚሊዮን ዶላር ከነበረበት በ1996 ወደ 545 ሚሊዮን ዶላር አድጓል፡፡ በተባበሩት መንግሥታት የንግድና የልማት ጉባዔ (UNCTAD) እንደዘገበው የወጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ከ1992 እስከ 1996 ድረስ በነበሩት ዓመታት በ94 ሚሊዮን እና በ545 ሚሊዮን ዶላር መካከል ሲዋዥቅ የነበረ ሲሆን ከ1998 ዓም ጀምሮ እያሽቆለቆለ ሄዷል፡፡[36] ሆኖም የፌደራሉ ኢንቨስትመንት

ቢሮ ከ1997 ጀምሮ የወጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ ማምጣቱን ይዘግባል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በግብርና ማከ ወደ

አገር ወስጥ የሚባው የወጪ ኢንቨስትመንት ከአጠቃላዩ ቀጥተኛ የወጪ ኢንቨስትመንት 32በመቶ ነው፡፡

| ሠንጠረዥ 2፡ የኢትዮጵያ ዓመታዊ | |
|---|---|
| የወጪ ቀጥተኛ መዋዕለንዋይ ፍሰት | |
| 1984 | 0.17 |
| 1985 | 3.5 |
| 1986 | 17.21 |
| 1987 | 14.14 |
| 1988 | 21.93 |
| 1989 | 288.49 |
| 1990 | 260.67 |
| 1991 | 69.98 |
| 1992 | 134.64 |
| 1993 | 349.4 |
| 1994 | 255 |
| 1995 | 465 |
| 1996 | 545.1 |
| 1997 | 265.11 |
| 1998 | 545.26 |
| 1999 | 221.99 |
| 2000 | 108.54 |
| 2001 | 93.57 |
| አኃዞቹ ወቅታዊ በሆነው የወጪ ምንዛሪ ተመን በሚሊዮን ዶላር ተቆጥረው ነው፡፡ | |
| ምንጭ UNCTAD (2010) | |

ከዚህ በታች የሚገኘው ሠንጠረዥ 3 የወጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ከባለሃብት አገሮች አኳያ ይዘረዝራል፡፡ እነዚህ አኃዞች የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቢሮ የዘገባቸውና ይከሰታሉ ተብለው የሚጠበቁ የካፒታል መዋዕለንዋይ ፍሰቶች ናቸው፡፡ "ሌሎች" በሚለው ሚስሚ ላይ በ2000ዓም ላይ የተጠቀሰው ቁጥር 40በመቶ ከሱዳን እንዲሁም ከሚኬዥያ 14.5በመቶ ይገኛል ተብሎ የተጠበቀ የመዋዕለንዋይ ፍሰት ነው፡፡ ከ1998 ጀምሮ እስከ 2000ዓም ድረስ ከሕንድ የመጣው 80.45 ሚሊዮን ዶላር የወጪ ኢንቨስትመንት በሸንኮራ አገዳ እርሻ ላይ የዋለ ነው፡፡ ከእስራኤል ከገባው መዋዕለንዋይ 50በመቶ የሚሆነው ከአበባ ጋር በተያያዘ ምርት ላይ ሲወል 25በመቶ የሚሆነው በአትክልት ምርት ቀሪው 25በመቶ ደግሞ በባዮነዳጅ (ከዕጽዋትና እንስሳት ተዋጽዖ የሚገኝ ነዳጅ) ላይ የዋለ ነው፡፡ 50በመቶ የሚሆነው ከሳዉዲአረቢያ የተገኘው ቀጥተኛ የወጪ ኢንቨስትመንት በከብት ሃብት ልማት ላይ የዋለ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ ቀጥተኛ የወጪ መዋዕለንዋይ የባለሃብት አገሮች ዝርዝር

| አገራት | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 | 1998 | 1999 | 2000 | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአወሮጳ ማኀበር | 26.63 | 7.41 | 5.34 | 11.72 | 18.47 | 20.87 | 12.11 | 52.61 | 16.37 | 21.22 |
| ሕንድ | | | 31.6 | 1.94 | 13.2 | 8.75 | 70.62 | 2.8 | 12.81 | 32.43 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እስራኤል | 2.75 | 15.76 | | 5.56 | 23.65 | 29.21 | 4.3 | 10.63 | 5.42 | 7.18 |
| ሳውዲአረቢያ | 47.4 | 76.84 | 58.77 | 4.87 | 3.07 | 4.13 | 0.23 | 3.53 | 3.6 | 3.1 |
| አሜሪካ | | | 4.3 | 44.55 | 28.96 | 20.06 | 10.93 | 17.17 | 4.89 | 11.54 |
| ሌሎች | 23.21 | | | 31.36 | 12.66 | 16.98 | 1.82 | 13.26 | 56.91 | 24.53 |
| አጠቃላይ (በመቶ) | **100** | **100** | **100** | **100** | **100** | **100** | **100** | **100** | **100** | **100** |
| ድምር (በሚሊዮን ዶላር) | **43.51** | **56.12** | **19.52** | **223.77** | **380.96** | **180.59** | **349.89** | **1640.47** | **3214.17** | **9250** |
| ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቢሮ፣ 2001 | | | | | | | | | | |

**መጪው ጊዜ**

በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚወጡ ዘገባዎች የአገሪቷ የወደፊቱ የኢኮኖሚ ገጽታ የተመቻቸ እንደሚሆን ይገምታሉ፡፡ አሁን ያሉት ሁኔታዎች እንደ ፕራይቬታይዜሽን እና በኢትዮጵያ የምርት ገበያ የሚከናወኑት ዘመናዊ የገበያ ለውጦች እንደሚቀጥሉም ግምት አለ፡፡ ከፍተኛ የሆነ ዕድገት የሚጠበቅ ከሆነ ማጡሰፊ የሆኑ የማንግሥት ወጪዎች፣ የመሠረተልማት ግንባታዎች እንዲሁም ንግድን ዓላማው ያደረገ የግብርና ተግባራት በሰፊው መቀጠል አለባቸው፡፡

## 1.4 የምግብ ዋስትና ዓወድ

በ1977/1978ዓም ከተከሰተው ረሃብ ጀምሮ ጤ (ችጋር) በኢትዮጵያ አሰቃቂ ችግር ፈጣሪ ክስተት ሆኗል፡፡ ይህም ሁኔታ ኢትዮጵያን በዓለምአቀፍ ደረጃ በረሃብ ስሟ የምትጠራ አገር አድርጓታል፡፡ ምንም እንኳን የረሃቡ ማጠን ተደጋጋሚ ባይሆንም አገሪቷ ባለማቋረጥ ከፍተኛ የሆነ የምግብ ዕጥረትንና የተመጣጠ ምግብ ዕጦትን እየተጋፈጠች ትገኛለች፡፡ በ2001ዓም ከአጠቃላይ ሕዝቧ 10በመቶ የሚሆነው ወይም 7.8 ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ በጽኑ ተርቦ ነበር፡፡ በ2000ዓም አካባበቢ የምግብ ዋጋ በዓለምአቀፍ ደረጃ ሲንር 6.4 ሚሊዮን ተጨማሪ ሕዝብ የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ዕርዳታ ጥገኛ ሆኖ ነበር፡፡ (በ2001ዓም ይህ ቁጥር ቀንሶ ወደ 4.9ሚሊዮን መድረሱ ይታወሳል፡፡)[37] በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ ካሉ አገሮች ሁሉ ኢትዮጵያ ከፍተኛውን የምግብ ዕርዳታ የምትቀበል አገር ናት፡፡ አሜሪካ ለብቻዋ 374 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ የምግብ ዕርዳታ በ2001ዓም የለገሰች ሲሆን በተመሳሳይ ዓመት ለኢትዮጵያ መንግሥት ደግሞ 862 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ድጎማ አድርጋለች፡፡

ከ1957ዓም ጀምሮ ለ15 ጊዜያት ያህል ኢትዮጵያ በጽኑ ድርቅ ተመትታለች፡፡ በ2002ዓም የተደረገው የምግብ ደኅንነትንና አደጋ አመላካች (Food Security Risk Index) እንደጠቆመው ለሁኔታው በእጅጉ ከተጋለጡት 10 አገራት አንዷ ስትሆን ጥናቱ ከተካሄደባቸው 163 አገራት መካከል በ6ኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ ዘግቦ ነበር፡፡[38]



ስዕል 1 በክልል ደረጃ ለምግብ ዕጥረት የተጋለጠው ሕዝብ በመቶ

Data source: Disaster Prevention and Preparedness Agency (DPPA) and Food Security Coordination Bureau (FSCB). Graphics by FEWS NET.

ስዕል 1 የሚያሳየው ዓይነተኛ በሚባለው በ1999ዓም የምግብ ዕርዳታ የሚያስፈልገውን ሕዝብ ሲሆን በአገሪቷ ወስጥ ከሚገኙት ክልሎች በሙሉ የሶማሌ እና የአፋር ዘላኖች በቀጣይነት ለምግብ ዕጥረት እንደተጋለጡ ይታያል፡፡ በሰሜን ምስራቅ ደጋማ ቦታዎች የሚኖረው ሕዝብም ያለማቋረጥ የምግብ ዕጥረት ተጠቂ ሆኗል፡፡ ይህም አካባቢ በበልግ ዝናብ ላይ ጥገኛ የሆኑትን የደቡብና ምስራቅ ትግራይን፤ የምስራቅ አማራ ክልልን (ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ዞኖችን ይጠቀልላል) እስከ ምስራቅ የደቡብ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል እና ምስራቅ የኦሮሚያ ክልልን የሚያካትት ነው፡፡ እነዚህ ክልሎች ተመሳሳይ የምግብ ዕጥረት ሁኔታዎች የሚያጋጥማቸው ሲሆን በተጨማሪም ዋነኛ በሚባሉት ወንዞች ዳርቻ የሚኖሩ ሰዎች በተለየ ሁኔታ ለጎርፍ በመጋለጣቸው ሥር የሰደደ የምግብ ዕጥረት

የተጋረጠባቸው ናቸው፡፡[39] እነዚህም በአዋሽ ሸለቆ የሚገኙ እንዲሁም በጋምቤላና በደቡብ ኦሞ ሸለቆ የሚገኙን የሚያጠቃልል ነው፡፡

## ግብርና በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ የሚከሰተው የዝናብ ሁኔታ በእጅጉ ተለዋዋጭ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የሚዘንበው መጠንም ኀይለኛ ነው፡፡ ይህም ሁኔታ በወቅቶች የሚፈራረቂያ ጊዜና ባጠቃላይ በዓመት ወስጥም ከፍተኛ የድርቅ አደጋ እንዲኖር አድጓል፡፡ በአገሪቱ ወስጥ ካለው የጥራጥሬ እርሻ 10 በመቶ ያህሉ ብቻ በመስኖ የለማ ሲሆን እንደ ቡና፣ የዘይትዘር እንዲሁም የለወዝ ዝርያዎች ያሉ ለወጪ ገበያ የሚውሉ በሙሉ የሚበቅሉት በዝናብ ነው፡፡ ሆኖም እንደ ሸንኮራአገዳ፣ ጥጥ እና አበባ ያሉ ኢንዱስትሪ ተኮር ምርቶች በመስኖ የሚለሙ በመሆናቸው ድርቅ በሚከሰትበት ጊዜ የሰብል ምርቱን 90 በመቶ እንዲቀንስ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የአገሪቱ መሬት እጅግ ዝቅተኛ ሁኔታ ላይ ማኘቱ ለረጅም ጊዜ የሚከሰትን ድርቅ የመቋቋም ችሎታው ወሱን እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በኢትዮጵያ ወስጥ የሚሚረተው ምርት የምግብ ዋስትና ተግባራዊ መሆን ወይም አለመሆን፣ ወቅቱን ጠበቆ በሚዘንበው ዝናብ እና በሌሎች የአየር ጠባይ ሁኔታዎች ላይ በእጅጉ ጥገኛ ነው፡፡[40] በኢትዮጵያ አምስት ዋና ዋና የእርሻ ምርት ዘደዎች አሉ፡፡ እነዚህም፡ –

1. ***የደጋው ክፍል የተቀላቀለ የእርሻ ዘዴ፤*** ይህ ዘዴ 80በመቶ በሚሆነው የአገሪቷ ሕዝብ እንዲሁም ከአጠቃላዩ የመሬት ሥፋት 45በመቶ በሚሆነውና ከ1500 ሜትር የባሕር ጠለል በላይ በሚኖሩ ዘንድ የሚተገበር ነው፡፡
2. ***የቆላው ክልል የተቀላቀለ የግብርና ምርት ዘዴ፤*** ይህ ደግሞ ዘዴ ከፍታቸው ከ1500 ሜትር የባሕር ጠለል በታች በሆኑ አካባቢዎች የሚተገበር ነው፡፡ በእነዚህ ቦታዎች ድርቅን መቋቋም የሚችሉ እንደ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ስንደና ጤፍ እንዲሁም የዘይት ሰብሎችና ጥራጥሬዎች ይሚረታሉ፡፡ በሬዎች ለኃይል ምንጭነት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሲሆን ለአካባቢው ኅብረተሰብ ከብቶች የሚውለው የግጦሽ ቦታና ከሰብሎች የሚገኘው ትርፍራፊ ከብቶችን ለሚርባት ጥቅም ላይ ይወላል፡፡ ከእርሻ ተግባራት ወጪ በእነዚህ ቆላማ አካባቢዎች ለማገዶ የሚውል እንጨትና ከሰል ሽያጭ በሰፊው ይተገበራል፡፡
3. ***የአርብቶአደርነት ህይወት*** ከአጠቃላዩ ሕዝብ 10በመቶ የሚሆነውና በአፋርና በሶማሌ ክልሎች እንዲሁም በቦረና ዞን የሚኖረው ሕዝብ የኑሮ መተዳደሪያው ነው፡፡
4. ***አሰባጥሮ የሚዘስ ልምድ*** በተለይ በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያ የተለመደ ሲሆን ይህም ከአጭር ጊዜ እርሻ በኋላ ሜሬቱን እንደገና ለተወሰነ ጊዜ ሳያርሱ (ባብዛኛው ከ 1 እስከ 2 ዓመታት) የመተው ልምድ ነው፡፡ ሜሬቱ በሚይታረስበት ዓመታት የሚበቅለወን ዕጽዋት ለማስወገድ በበጋ ወራት እሣት የሚለቀቅ ሲሆን ይህም የሚከናወነው የተከላ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ነው፡፡ ይህ የሚተገበርባቸው ቦታዎች ሕዝብ ጥቅጥቅ ብሎ ያልሰፈረባቸው ናቸው፡፡
5. ***ንግድ ተኮር ግብርና*** ተብሎ የሚጠራው በቅርቡ የተጀመረ የእርሻ ማስከ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው የሜሬት ኢንቨስትመንት እየተካሄደ ያለው አሰባጥሮ የሚዘስ ልምድ ገበራዊ በሆነባቸው አካባቢዎች ነው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ የተቀላቀለ የግብርና ተግባር በሚከሄድባቸው የቆላ አካባቢዎች እንዲሁም በአንዳንድ የአርብቶአደር ሥፍራዎች ይኸው የሜሬት ኢንቨስትመንት ተግባር እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ከእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) በየጊዜው ሲጠቀስ የምንሰማው ስታቲስቲክስ ኢትዮጵያ ካላት 111.5 ሚሊዮን ሔክታር ሜሬት 74.5 ሚሊዮን ሔክታር የሚሆነው ለእርሻ ተስማሚ ሲሆን 15.4 ሚሊዮን ሔክታሩ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ምርት በማስጠት ላይ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ እንደ በቆሎ፣

ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ፣ ዳጉሳና ማሽላ የመሳሰሉትን ጥራጥሬዎች እንዲሁም ሌሎች የእህል አይነቶችን፣ የዘይት ፍሬዎችን፣ ፍራፍሬዎችን፣ አትክልቶችን፣ የቃጫ ሰብሎችን፣ ቡና፣ ሻይ፣ ቅመማቅመሞች እንዲሁም ሌሎች የኢንዱስትሪ ሰብሎችን ታመርታለች፡፡[41]

### የምግብ ዋስትና እንዳይኖር የሚያደርጉ እውነታዎች

በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ዕውን እንዳይሆን የሚያደርጉ በርካታ ወስብስብ የሆኑ የስነ ሕዝብ፣ የአየር ጠባይ፣ የፖለቲካና የቴክኖሎጂ ምክንያቶች አሉ፡፡ መሠረታዊ የሆኑት ምክንያቶች ግን የሚከተሉት ናቸው፡– ፈጣን የሕዝብ ዕድገትና የአካባቢ ብክለት፣ ከመሬት ይዞታና ከገበያ አሠራር ወዘተ አኳያ አግባብነት የሌላቸው የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ከግብርና ወጪ ያለው የሥራ ዕድል አናሳነት፣ ወቅታዊ ለሆነው ፍላጎት ብቃት ያለው ምላሽ አለማስጠት (ይህም ለአስከፊ ድህነት፣ ጉስቁልና፣ የንብረት ማሽቆ ምክንያት ሆኗል)፣ በዘላኖች (በአርብቶአደሮች) አካባቢዎች የሚሳ ግጭት፣ የመሠረተልማት አወታሮች ዕጥረት (ይህም የትምህርት፣ የንጹህ ወሃ አቅርቦት፣ የጤና ወዘተ አገልግሎቶችን የሚጨምር ነው)፣ የጾታ መድልዖ እና በተደጋጋሚ ከ1968 እስከ 1970 ባሉት ዓመታት ከ10 ሔክታር በላይ ካላቸው ቤተሰቦች መሬት እየተወረሰ በገበሬዎች ማኅበር አማካኝነት ለገበሬዎች እንዲሰጥ ተደረገ፡፡ በ1970ዎቹ ባሉት ዓመታት መሬትን እና የእርሻ ይዞታዎችን ከግል ባለቤትነት የመውረስ ተግባር ሲከናወን ከቆየ በኋላ በ1981 ደርግ በፊት ሲከተለው የነበረወን አሠራር በመተው ወደ ገበያ መር ሽ ስርዓት ማለወጡ በማወጁ የመሬት ይዞታም አብሮ የለወጡ አካል ሆነ፡፡

በ1983 ዓም በማለስ ዜናዊ የሚመራው ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ (ህወሃት) ሥልጣን ከተቆጣጠረ በኋላም በመሬት ይዞታ ላይ ይህንኑ የሚከሰት ድርቅና ጎርፍ ናቸው፡፡[42] አብዛኛው የግብርና ምርት ለቤተሰባዊ ፍጆታ የሚያስፈልጉትን በማሟላት ላይ ያተኮረ መሆኑ፣ የምርት ትርፍ ሲኖር ደግሞ አነስተኛ አምርቶ ሻጮች ምርታቸወን ወደገበያ የሚያቀርበብት ምቹ ሁኔታ አለመኖር ሌሎቹ ተጨማሪ ምክንያቶች ናቸው፡፡

## 1.5 የመሬት ይዞታ

በ1966 ወደ ሥልጣን የመጣው ደርግ አሁን በኢትዮጵያ የሚገኘወን የመሬት ይዞታ ዜማ እንደወሰነው ይታወሳል፡፡ በ1967 የታወጀው የመሬት አዋጅ በወቅቱ የነበረወን የመሬት አስተዳደር በማስወገድ መንግሥት የመሬት ባለቤት እንዲሆን አድርጎታል፡፡ እነዚህ ለወጦች በ1980 በታወጀው ሕገመንግሥትም ከለላ እንደተደረገላቸው እናገኛለን፡፡ ገበሬዎች ከመኖሪያ ቤታቸው አቅራቢያ የሚገኝ መሬትን ለተወሰነ ነገር ለማጠቀም በነጻ ሲሰጣቸው

"ዓለምአቀፋዊ መብት" እና የመንግሥትን ባለቤትነትን አሠራር ቀጥለብታል፡፡ "መሬትን ለሽያጭ መፍቀድ በቀላሉ ሊጎዱ የሚችሉትንና ምስኪን ገበሬዎችን ያለመሬት ያስቀራል የሚል"[43] ሥጋት ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት በ1987 የታወጀው ሕገመንግሥት ይህንኑ የመንግሥት ባለቤትነትን በድጋሚ በሙናት ታወጇል፡፡ ሕገመንግሥቱ እንደሚለው ከሆነ የመሬት ባለቤቶች በይዞታው ላይ ያላቸወን ሃብት (በተወሰነ መልኩ) እንዲሁም መሬቱን ለሌላ የማስተላለፍ መብታቸው የተጠበቀ ሲሆን መሬቱ የሚወሰድባቸው ከሆነም ተገቢው ካሣ እንዲሠጣቸው ያዛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሕገመንግሥቱ ሰፋ ያለ የዘላኖችን መብት የሚያስጠብቅ ማዘርዘር ይሰጣል፡፡ (አንቀጽ 1.6)



**ከፍተኛ የደን ጭፍጨፋ የተካሄደበት የአማራ ክልል ሜሬት**

በ1988 የተደረገው ሕገመንግሥታዊ የመሬት ይዞታ ማሻሻያ ስለ መሬት ኪራይ እንዲሁም ሊዝ የተለያዩ ለወጦችን ያካተተ ነበር፡፡ ሆኖም እስካሁን የሚሠራበት የመንግሥት የመሬት ባለቤትነት ሥልጣን ብዙ ክርክርና ጭቅጭቅ የሚያስነሳ ጉዳይ ሆኖ ቢቀጥልም ሕጉ ግን በአራት ድምጽ ብልጫ 499 ለ495 በሆነ ድምጽ አልፏል፡፡ *የፌዴራል መንግሥት የገጠር ሜሬት አስተዳደር አዋጅ* (ቁጥር 89/1989) ለክልል ማስተዳድሮች የራሳቸውን መሬት ለማስተዳደር አዋጅ ማውጣት የሚችሉበትን ሥልጣን ይሰጣል፡፡ ይህንን በማጠቀም እስካሁን አራት ክልሎች የራሣቸውን ሕግ ያወጡ ሲሆን የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ ማስተዳድርም ሕጉን የማውጣት የሚጨረሻው ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ (ለዚህም ተግባራዊነት
አዋጅ ቁጥር 46/1992ን እንደ ናሙና ይጠቀሙ)[44] በፌደራል ደረጃ የመሬትን ጉዳይ በተማከተ አግባብ ያለው አካል የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር (MoARD) ነው፡፡ በክልሎች ደረጃ ግን ይህ መሬትን የማስተዳደር ሁኔታ እንደ ክልሉ የሚለያይ ሲሆን በተግባር ተፈጻሚ ሲሆን የሚታየው ግን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም በወረዳ ወይም በቀበሌ ደረጃ ሲከናወን ነው፡፡

በብዙዎች ዘንድ መንግሥት የመሬት ባለቤት መሆኑ ኢንቨስትመንትን እንደሚያበረታታ ይነገራል፡፡ ይህም ምርትን፣ የምግብ ዋስትናን እና የኢኮኖሚ ዕድገትን እንደሚያመነምን እሙን ነው፡ በአንጻሩ ግን ኢህአዴግ የፕራይቬታይዜሽን ተግባራዊነት በገጠር የሚኖሩ በርካታ ምስኪናን መሬታቸውን እንዲሸጡ በማፋፋት ወደ ከተማ እንዲኮበልሉ ያደርጋቸዋል፤ ይህም በከተሞች እየተከሰተ ያለውን ቀወስ በማባባስ ሥር የሰደደ ድህነት እንዲስፋፋ ያደርጋል በማለት ይከራከራል፡፡

## የወቅቱ የመሬት ይዞታ አሠራር

የመሬት ይዞታና የምስክር ወረቀት አሠጣጥ ክልል ደረጃ የሚወሰን ሲሆን ይህም አሠራር በየክልሉ ይለያያል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የሚታረስ

ሜሬት መበትን በተማለከተ ሦስት ዋናዋና ልምዶችን ኢትዮጵያ እየተከተለች ትገኛለች፡፡ እነዚህም አስተዳደርን መሠረት ያደረገ፣ ገበያን መሠረት ያደረገ እና ከገበያ አሠራር ወጣ ያለ ልምድን መሠረት ያደረገ አሠራሮች ናቸው፡፡[45]

1. <u>አስተዳደርን መሠረት ያደረገው፡–</u> በዚህ አሠራር መሠረት ብቃት ያላቸው ቤተሰቦች ማጡ የተወሰነ ሜሬት በባለቤትነት ይሰጣቸው ዘንድ መቢታቸው ያደርጋል፡፡ እነዚህ መበቶች ከሜሬት ጥበቃን እና ማሻሻል በስተቀር በሜሬቱ ላይ ያልተወሰነ መበት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ከዚህ አሠራር ጋር በተያያዘ የሜሬት ከራይን አስሜልከቶ እየጨመረ የመጣ የመበት ሁኔታ ሲኖር ይህ መበት በአብዛኛው የሚሠራበት ነው፡፡
2. <u>ገበያን መሠረት ያደረገ፡–</u> ይህ አሠራር ተግባራዊ እየሆነ የመጣው የሜሬት ይዞታን አስሜልከቶ በአገሪቷ ወስጥ ያለው ፍላጎት ከአቅርቦቱ ጋር ሊጣጣም ባለመቻሉ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የእርሻ ማጠን እያነሰ የሄደ ሲሆን በአንጻሩ ግን የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ መጥቷል፡፡ እነዚህ የከራይ ገበያዎች በአቅርቦትና ፍላጎት ላይ መመሥረታቸው የሚታወቅ ጉዳይ ቢሆንም ያለው አሠራር ግን ባለቤትነትን ማካፈል፣ በጣም ወሱን ለሆኑ ጉዳዮች የአጭር ጊዜ ኮትራት የማስጠትን ሥርዓት የሚከተል ነው፡፡ እነዚህን መበቶች ለሌላው ተላልፈው የሚይሰጡ ከማሆናቸው አልፎ ሜሬትን የማስደር አሰራር ተግባራዊ አለማሆን ሜሬቱን የበለጠ እንዲራቆት አድርጎታል፡፡
3. <u>ከገበያ አሠራር ወጣ ያለና ልምድን መሠረት ያደረገ አሠራር፡–</u> አሁን ያለው ሜሬትን ለኢንቨስትመንት የማስጠት ተግባር ባተኮረባቸው ቆላማ ቦታዎች ይህ ልምድ በስፋት እየተሠራበት ይገኛል፡፡ ይህ አሠራር ከዘር ሃረግና ከጥንት ሲወርድ የመጣውን መበት በከፍተኛ ሁኔታ ግምት ወስጥ የሚያስገባ ነው፡፡ ሆኖም እንደ ቦታውና እንደ ሕዝቡ የዘር ሃረግ ሁኔታ ይህ አሠራር በተለያዩ ቦታዎች የተለያየ የአሠራር ሥርዓትን ይከተላል፡፡

ሊታረስ በማቻለው ሜሬት ላይ ከተሰጡት መበቶች በተጨማሪ ለግጦሽ፣ ለአደን፣ ዓሣ ለማጥመድ፣ ለመንፈሳዊ ወይም ለሌሎች አገልግሎቶች የተፈጥሮ ኃብትን ተካፍሎ ስለማጠቀም ይጠቅሳል፡፡ እነዚህ በተለምዶ በሚደረገው የአሠራር መንገድ የሚከናወኑ ናቸው፡፡ ሌሎች ከተለያየ ቦታ መጥተው ወደእነዚህ ቦታዎች ለመግባት እንዲሁም ቦታዎቹን ለመካፈል ወይም ለማጠቀም በሚፈልጉበት ጊዜ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ባላቸው ነገር ግን ይፋ ባልሆኑ የአሠራር ደንቦች አማካኝነት አጠቃቀሙ ይከናወናል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት የአሠራር ሁኔታዎች ወስጥ የክልሎች ጣልቃገብነት በጣም ወሱን ነው፡፡ አሁን ያለው አሠራር ባጠቃላይ በአራት ከፋፍሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡– (1) ዕገዳ የሌለበት ለሁሉም ክፍት በሆነ ሜልኩ የጋራ ኃብት አጠቃቀምን የሚፈቅድ፤ (2) ዕገዳ ተግባራዊ የሚሆንባቸው ቦታዎች (ለምሳሌ ለግጦሽና ለደን ጥበቃ የተወሰኑ ቦታዎች)፤ (3) ለግል ጉዳይ የተከለሉ ኮረብታዎችና የታጠሩ ቦታዎች፤ እንዲሁም (4) በክልል ቁጥጥር ሥር ያሉ በሚል በአራት ሊከፋፈሉ ይችላሉ፡፡[46]

በኢትዮጵያ ወስጥ የተፈጥሮ ኃብትን በጋርዮሽ ማጠቀም በዓይነትም ሆነ በማጠን እየቀነሰ የመጣ ክስተት እንደሆነ በርካታ ዘገባዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ምን እንደሆነ አንድ ዘገባ እንደጠቆመው ከሆነ የአየር ንብረት ለወጥ (ደረቃማነት እና በረሃማነት ማስፋፋት)፣ የሕዝብ ቁጥር ሜጨመር፣ የመኖር ዓቅም ማነስና ደህነት፣ የፖለቲካው አለሚጋጋትና ደካማ ማዕከላዊ አስተዳደር፣ ሆን ተብለው የሚወጡ የመንግሥት ፖሊሲዎች (የጋራ የሆኑትን ለግል የሚድረግ) እና የጋራ በሆኑት ላይ የተቀናጀ እርምጃ የመውሰድ ተግባር ማሽቆልቆል ናቸው፡፡[47]



**የበርካታዎችን ዓይን የሚስበውና በተፈጥሮ ሃብት የበለጸገው የጋምቤላ ድንግል መሬት**

ዘላኖች (አርብቶአደሮች) ጠንካራ ሕገመንግሥታዊ መብቶች እንዲኖራቸው የተጣለ መሠረት ቢኖርም፣ የዘላኖችን ምርት ለየት የሚያደርገው የመሬት ይዞታን በጋራ የማጠቀም ልምድ ባለፉት ጊዜያት የወጡ የመንግሥት ፖሊሲዎች ችል ሲሏቸው ቆይተዋል፡፡[48] አርብቶአደሮች በተደጋጋሚ መሬትና የመሬት ይዞታቸውን (በቅርቡ በኦሞ ሸለቆ የሚካነባው ግድብ፣ ከአፋር ዘላኖች (አርብቶአደሮች) ጋር በአዋሽ ሸለቆ እንዲሁም ከከረዩ የኦሮሞ አርብቶአደሮች ጋር ያለው ችግር) እያጡ እንደሆነ በርካታ የተለያዩ ዘገባዎች ጠቁመዋል፡፡

የመሬት ይዞታ ዋስትናን እንዲሁም የመሬት ሠርተፊኬትን በተማለከተ ያለው አሠራር በየክልሉ የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ የመሬት ባለቤት የሆኑ ሁሉ በትግራይ የምዝገባ ሠርቲፊኬት ለማግኘት፣ በአማራ ክልል የይዞታ ደብተር ለማግኘት እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል የዕድሜልክ የይዞታ ሠርቲፊኬት ለማግኘት ብቁ ናቸው፡፡ መሬትን እንደገና የማከፋፈል ሁኔታ በትግራይ የተፈቀደ ሲሆን በኦሮሚያ ግን ክልክል ነው፡፡ በትግራይ የቀድሞ የህወሃት ታጋዮችና ቀድመው ወደ ክልሉ የገቡ ምንም እንኳን ኑሯቸውን በከሞዎች አካባቢ ቢማስርቱም

በገጠር የሜት ባለቤት የመሆን መብት አላቸው፡፡ ይህ መብት በየትኛውም ክልል ተግባራዊ አይደለም፡፡

በየክልሉ የሚገኙ ባለሥልጣኖች በገጠር አካባቢ የአገዛዙን የፖለቲካ ድጋፍ ለማግልበት ከሕጉ ወስጥ የፈለጉትን እየመረጡ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ አንድ ዘገባ አሜልክቷል፡፡[49] ሌሎች ዘገባዎች ደግሞ የተለያዩትን የተጠቃሚ መብቶች (በገጠር፣ በከተማ፣ በጋርዮሽና አርብቶአደርነት) ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ እርስበርሳቸው የሚጋጩና የሚቃረረቡ አሠራሮች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ እነዚህን እያንዳንዳቸውን መብቶች የሚስተዳደር አሠራር ከሌሎች አሠራሮች ጋር የተቀናጀ አይደለም፡፡ ይህም አለመሆኑ ተመሳሳይ የሜት ይዞታዎች በተለያዩ የመንግሥት መምሪያዎች ለተለያየ አገልግሎት ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡[50]

### ወቅታዊው የሜት ይዞታ ሚረጋገጫ

ለበርካታ ዓመታት የዓለም ባንክና ሌሎች ዓለምአቀፋዊ ድርጅቶች የኢትዮጵያ መንግሥት የሜት ይዞታዎችን አሠራር ለማሻሻል የሚያደርገውን ጥረት ሲደግፉ ቆይተዋል፡፡ የሜት ይዞታ ሚረጋገጫ ማለት የተጠቀሰውን ንብረት በመመዝገብ የይዞታውን ዋስትና ለሚረጋገጥ የባለቤትነት መብት ሕጋዊ የሚሆንበት ሂደት ነው፡፡ በ2000 ዓም የወጣው የዓለም ባንክ ዘገባ የሜት ይዞታ ሚረጋገጫ ግጭቶችን ለመቀነስ፣ ገበሬዎችን ዛፎችን እንዲተክሉ ለማድረግ፣ ዘላቂነት ያለው የሜት አጠቃቀምን ለማበረታታት እንዲሁም የሴቶችን የኢኮኖሚ የማኅበራዊ ደረጃ ለማሻሻል እንደሚውል ጥቆማ አድርጓል፡፡[51] ሌላ ጥናት ደግሞ የሜት ይዞታ ባለቤት መሆን ሜቱ ይወረስብኛል የሚል አስተሳሰብ በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ጠቁሟል፡፡[52] ሌላ በትግራይ ክልል የተካሄደ ጥናት ደግሞ የሚረጋገጫ ሠርቲፊኬት የተቀበሉ ቤተሰቦች ከቦታቸው የሚፈናቀላቸው ጭንቀት ዝቅተኛ እንደሆነ ሁኔታው ከተከሰተም ካሣ የማግኘት ዕድላቸው ከፍተኛ ነው ብለው እንደሚያምኑ ጠቁሟል፡፡[53]

**ከአፌደሪ ሕገመንግሥት ስለ ሜት ኢንቨስትመንት የሚገኙ አንቀጾችና ሐረጎች**

"ሜት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው፡፡" አንቀጽ 40(3)

"የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ሜት በነጻ የማግኘትና ከሜታቸው ያለመፈቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡፡ አፈጻጸሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል፡፡" አንቀጽ 40(4)

"የኢትዮጵያ ዘላኖች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት ሜት በነጻ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከሜታቸው ያለሚፈናቀል መብት አላቸው፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል፡፡" አንቀጽ 40(5)

"ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ፣ ወይም በገንዘቡ በሜት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የሜት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል፡፡ . . . "አንቀጽ 40(7)

"የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል፡፡" አንቀጽ 40(8)

"መንግሥት በሚያካሂዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ ማዛወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው፡፡" አንቀጽ 44(2)

"መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ኃብትን በሕዝብ ስም በይዞታው ስር በማድረግ ለሕዝቡ የጋራ ጥቅምና እድገት እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡" አንቀጽ 89(5)

እስከ 2000ዓም ድረስ ክልሎች የመሬት ይዞታዎችን ለመመዝገብ በሚያደርጉት ጥረት በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በትግራይና በደቡብ ሕዝብ ክልሎች 6.3 ሚሊዮን ቤተሰቦች (20 ሚሊዮን የመሬት ይዞታዎች) ተመዝግበዋል፡፡ ዛሬም ይህ የመሬት ይዞታ ሚረጋገጫ የማሠጠት ጥረት በእነዚህ አራት ክልሎች እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በ2003/2004 የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመሬት ይዞታ ሚረጋገጫ ተግባራዊ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ሆኖም ይህ የጥናት ቡድን ባደረገው ምርምር መሠረት ማከሰፊ የሆነ የመሬት ሚረጋገጫ የማስጠት ጥረት በሌሎች ክልሎች ሲከናወን አልተማከተም፤ እነዚህም ክልሎች በአብዛኛው ባሕላዊውን የመሬት ይዞታ አሠራር እየተከተሉ የሚገኙ ናቸው፡፡

## 1.6 የመሬት ኢንቨስትመንትን በተመለከተ የሕግ አስተያየት

በ1987 የታወጀው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ (ኢፌዲሪ) ሕገመንግሥት ማንኛውም ከመሬት ጋር የተያያዘ የኢንቨስትመንት አዋጅና ፖሊሲ ምን ላይ ተመርኩዞ መውጣት እንዳለበት መሠረት ይጥላል፡፡ ይህ ሕገመንግሥት የመሬት ባለቤትነት የመንግሥት መሆኑን በድጋሚ አረጋግጧል፡፡ ገበሬዎች ነጻ መሬት ስለሚያገኙበት፣ ከቦታቸው እንዳይነሱ ስለሚደረግላቸው ጥበቃ፣ ዘላኖች (አርብቶአደሮች) ስለሚኖሩባቸው መብቶች እንዲሁም ከቦታ የሚነሳቀል ሁኔታ በሚከሰትበት ወቅት ሊከፈል ስለሚገባ ካሣ በአጽንዖት ይናገራል፡፡

### ስለ መሬት አጠቃቀም ሕጋዊ አሠራር

ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው *የፌዴራል መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 89/1989* ክልላዊ መስተዳድሮች በሥራቸው ያለውን መሬት ማስተዳደርና መቆጣጠር በተመለከተ ህግጋትን ማውጣት እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት አራት ክልሎች ይህንን ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ *(ትግራይ – አዋጅ ቁጥር 23/1981፤ አማራ – አዋጅ ቁጥር 46/1992፤ ደቡብ ሕዝብ – አዋጅ ቁጥር 53/1995 እና ኦሮሚያ – አዋጅ ቁጥር 56/1994)* እንዲሁም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በቅርቡ አዋጁን ይፋ ያደርጋል፡፡[54] እነዚህ አዋጆች በሙሉ የኅብረተሰቡን ተሳትፎ አስፈላጊነትን አጥብቀው ይናገራሉ (አንቀጽ 4)፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አዋጆቹ ስለ መሬት ክፍፍል እንዲሁም ካሳ በመክፈል መሬትን ስለመውሰድ (ለተወሰኑ ማሻሻያዎች)፣ መሬትን ስለማከራየት፣ በጋርዮሽ፣ በቡድንና በግል የመሬት ይዞታን ስለማጠቀም መብቶች ይዘረዝራሉ፡፡ እንዲሁም አዋጆቹ ስለመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሠረታዊ ሥርዓት–ቅርጽ ይሰጣሉ፡፡ (አንቀጽ 13 (2))

### ስለኢንቨስትመንት ሕጋዊ አሠራር

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ ዋንኛው ሕግ *አዋጅ ቁጥር 280/1994* (እና የማሻሻያ አዋጅ 375/1995) ሲሆን ከኢንቨስትመንት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ሕጎችንና ፖሊሲዎችን የሚዘረዝር ነው፡፡ የኢንቨስትመንት ዋና ዓላሞች የወጪ ንግድን በማበረታታት፣ የቴክኖሎጂና የክህሎት ሽግግር በማድረግ

ይሰጣል" የሚል አንቀጽ ማካተቱ ነው፡፡ የወጪ ባለሃብቶች ማሻ ካፒታልም ከ100ሺህ ዶላር ያነሰ መሆን እንደሌለበት ይገልጻል፡፡

በ1952 የተደነገገው የንግድ ሕግ የንግድ እንቅስቃሴዎችን በተማከተ መሠረታዊ መመሪያ ይሰጣል፡፡ ከዚህ ሕግም በኋላ የወጡ የተለያዩ አዋጆች የንግድና የሠራተኛን ሁኔታ በተማከተ ተጨማሪ ማዘርዝር በተለያዩ ጊዜያት ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡

የኢንቨስትመንት አዋጅ 84/1995 ማጠነኛ ለውጥ በማድረግና አንዳንድ ማበረታቻዎችን (የግብር እና ከቀረጥ ነጻ ዕቃዎችን ማስገባት፣ ወዘተ) በማከል እንዲሁም ለአገር ወስጥ ባለሃብቶችና ለመንግሥት ብቻ የሚፈቀዱ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ክፍላተ ኢኮኖሚዎችን ይነድፋል፡፡ አገር ወስጥ ተመርተው በጅምላ ስለሚሸጡ ሸቀጦች፣ ከወጪ ለሚመጡ ምርቶች በግብአትነት ስለሚገለግሉ ዕቃዎች እና ሌሎች እሴት ታክሎባቸው የሚከናወኑ የኢንዱስትሪ ተግባራት ለአገር ወስጥ ባለሃብቶች እንዲፈቀዱ ያዛል፡፡ ሌሎች ከሜሬት ይዞታ ጋር ግንኙነት ያላቸው የኢንቨስትመንት ተግባራት ለአገር ወስጥም ሆነ ለወጪ ባለሃብቶች በአዋጁ መሠረት ተፈቅደዋል፡፡

ለወጪ ባለሃብቶች የሜሬት ይዞታን ሚዳላደል በተማከተ ወሳኝ የሆነ ለውጥ የተካሄደው በ2001ዓም ነው፡፡ ይህም አዋጅ 29/1993 የወጪ ባለሃብቶችን በተማከተ ከ5000 ሄክታር በላይ የሆነ ይዞታን የፌደራል መንግሥት ኃላፊነቱን እንዲወስድ በታወጀበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ግን የክልል ማስተዳድሮች ያለገደብ የአገር ወስጥንም

"የወጪ ኢንቨስትመንት በአገሪቷ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ተገቢውን ሚና እንዲጫወት"[55] በማድረግ የወጪ ምንዛሪ ማስደግ ነው፡፡ አስገራሚው ጉዳይ በአንቀጽ 35(3) ላይ እያንዳንዱ የክልል ማስተዳደር ". . . ሜሬት በሚጭበበት ጊዜ ከምንም በማስቀደም ለተፈቀዱ ኢንቨስትመንቶች ቅድሚያ

ሆነ የወጪ የሜሬት ኢንቨስትመንትን ያከናወኑ ነበር፡፡ (ለበለጠ ሚጃ ክፍል 2.6 ይሚልከቱ) ይህ አሠራር በሂደት ላይ ተለዋዋጭነትን፣ የተማከለ ዕቅድና ትብብር አለመኖርን እንዲሁም የማስና ማስፋፋት የማስሉ የተለያዩ ችግሮችን አስከትሎ ነበር፡፡ (ከኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ስለሚገኙ ሕጎች ዝርዝር ተቀጽላ ሀ ይሚልከቱ)

## ደህነትን የማጥፋት ዕቅድና ሌሎች የልማት ዕቅዶችና ፖሊሲዎች

አሁን በኢትዮጵያ ያለወን የሜሬት ኢንቨስትመንት ዓወድ አቅጣጫ የተወሰነው በተለያዩ የፖሊሲ ዕቅዶች፣ ስትራቴጂክ ዕቅዶች፣ የደህነት ማስወገጃ/የልማት ዕቅዶች ነው፡፡ ልማት መር የግብርና ኢንዱስትሪ (ADLI) የተሰኘው የስትራቴጂክ ዕቅድ ከ1985 ጀምሮ የኢትዮጵያ መንግሥትን ስትራቴጂ ቅርጽ ያስያዘ ሲሆን ይህ ስትራቴጂ ዋና ዓላማ ያደረገው የገበሬዎችን ምርታማነትን በተማከተ የመዋቅር ለውጥ ለማምጣት እንዲሁም የፋብሪካወን ክፍለኢኮኖሚ በተማከተ ደግሞ በዘመናዊ ሜልኩ እንደገና እንዲዋቀር በማድረግ ዕቅድ ላይ በግልጽ በማትኮር ነው፡፡ *የኢፌዴሪ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ* (1994) የሚበለወም የተነደፈው ልማት መር የግብርና ኢንዱስትሪን እንደ ሜው ብቻ ሳይሆን ለኢንዱስትሪው ዕድገት እንደ ዕቅዱ ግብ አድራሽ በማድረግና የሰው ኃይልን በዋነኛነት የሚጠቀም የወጪ ንግድ መር የኢንዱስትሪ ዕድገት ለማድረግ ነው፡፡[56]

ከዚህ በተጨማሪም ከ1997 - 2002 *ድህነትን ለማጥፋት ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለው ዕቅድ* (PASDEP) በሚል የተነደፈው የተባበሩት *መንግሥታት* ካወጣው የሚሊኒየሙ የልማት ዕቅድ (MDGs) ጋር በጥምረት ተፈጻሚ እየሆነ እንዲሠራ ነው፡፡ ይህ ዕቅድ ግብርንናን ወደ ትርፋማ ንግድነት ማለወጥ፣ የግሉን ክፍለኢኮኖሚ ልማት እንዲሁም ለሚሊኒየሙ የልማት ዕቅድ (ተፈጻሚነት) ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ኃብቶችን ማሳደግ ላይ ያተኩራል፡፡ይህንንም ዕቅድ ተከትሎ ነው *የልማትና ትራንስፎርሜሽን* ስትራቴጂ ማደፍ የተቻለው፡፡ በቅርቡ የተለቀቀው ይህ የትራንስፎርሜሽን ንድፍ ከ2003 - 2009 ድህነትን ለማስወገድ የሚቻልበትን ሥርዓተቅርጽ ይሰጣል፡፡ ይህ ስትራቴጂ በግብርና እና በኃይል (ኤነርጂ) ዕድገት፣ በመሠረተልማት መሻሻልና ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ላይ ያተኩራል፡፡ በመሆኑም ስትራቴጂው ተግባራዊ ሲሆን በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የኃይል (የኤነርጂ) ምርት ዕድገት በአምስት እጥፍ እንዲሁም የግብርና ግብአቶች ዕድገት በእጥፍ ይመዘገባል የሚል ራዕይ መንግሥት አለው፡፡

## 1.7 የኢንቨስትመንት (የመዋዕለንዋይ) ዓወድ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባለሃብቶችን ለመሳብ በሚል ኢትዮጵያ የግብር ቅነሳን፣ ምቹ የመሬት ይዞታንና የኢንቨስትመንት ፈቃድን በተመለከተ ደግሞ ቀልጣፋና ፈጣን አሠራርን የመሳሰሉ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን ስትተገብር ቆይታለች፡፡ እነዚህን ጠቃሚ የሚባሉ የገበያ እሴቶችን

- ከግብር እና ቀረጥ ጋር በተያያዘ ነጻ ስለመሆን የወጡ ግሩም ማበረታቻዎች
- ጥብቅ ያልሆኑ ሕጎች
- ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ የሆነ የመሬና አሠራር

***"ኢትዮጵያን ለኢንቨስትመንት የሚጥነው ርካሽ የሠራተኛ ጉልበት፣ የተጠጋጋ መሬትና ለንግድ ምቹ ሁኔታ ሰላላት ነው፡ "***

አዲትያ ቪ. አጋርዋል የኢምፒ ባዮቴክ ኩባንያ ዳይሬክተር 30ሺህ ሄክታር መሬት ጃትሮፋ ለተባለ በተለይ ለባዮዲዝል ምርት የሚውል ሰብል ለማምረት ከኦሮሚያ ክልል ከተረከቡ በኋላ የተናገሩት፡፡ [57]

***"ኢትዮጵያን ለግብርና ኢንቨስትመንት የሚጥነው ያላትን የሠራተኛ ጉልበት፣ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ እንዲሁም መንግሥት የውጪ ኢንቨስትመንትንና ልማትን ለማሳደግ የሚሰጠውን ድጋፍ በመሚከት ነው፡፡"***

በጋምቤላ ክልል አኩሪአተር ለማምረት 25ሺህ ሄክታር መሬት የተረከበው የሩቺ ሶያ ኩባንያ ቃል አቀባይ፡፡ [58]

ኢትዮጵያ በትጋት ለዓለምና ብቃት ላላቸው ባለሃብቶች ስታስተዋውቅ ቆይታለች፡፡ ከዚህ የጥናት ቡድን ጋር የተገናኙ የአገር ወስጥና የወጪ ባለሃብቶች ኢትዮጵያ ለምን ለኢንቨስትመንት ምቹ እንደሆነች የተለያዩ ምክንያቶችን የሰጡ ሲሆን በጣም ተደጋጋሚነት ያላቸው ምክንያቶችም የሚከተሉት ናቸው፡ -

- በጣም ርካሽ የመሬት ከራይ
- ለእርሻ ተስማሚ የሆነ የአየር ንብረት
- ዝቅተኛ የሠራተኛ ጉልበት (የሠራተኛ ጉልበት በርካሽና በብዛት ይገኛል)

- ማጠነሰፊ የሆነ በልማት ላይ ያልዋለ መሬት
- ከገበያ ቅርበት አኳያ ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ
- ማጠነሰፊ የወሃ አቅርቦት

- ምርት ወደወጪ ለማላክ ያለው ተስማሚነት (ለሕንድ አሚራጭ አይደለም)
- ወደሌሎች ገበያዎች በቀላሉ ለመድረስ ያለው ምቹ አማራጭ
- የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማውጣት ያለው የተመቻቸ አሰራር በባለሃብቶቹ የተጠቀሱት ናቸው፡፡

ከእነዚህ ሁሉ በተጨማሪ የኢትዮጵያ መንግሥት መሬት ለሚከብ የሚፈልጉ ባለሃብቶች ጉዳያቸውን በቀላሉ የሚያስፈጽሙበት "የመሬት ባንክ" ሙቋቋሙ ሌላው ተጠቃሽ ሁኔታ ነው፡፡ በፌደራል መንግሥት ሥር ያለው የመሬት ይዞታ በጣም ሰፊና ተያያዥነት ያለው ሲሆን ለወጪ ባለሃብቶች ከ5ሺህ ሄክታር ወይም ከዚያ በላይ ለማስጠት የሚያስችል ነው፡፡

## ዓለምአቀፋዊ ስምምነቶች

ኢትዮጵያ የምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ ወይም ኮሜሳ (COMESA) ተብሎ የሚጠራው እና የሌሎች ታላላቅ የንግድ ቡድኖች አባል በመሆኗ 380 ሚሊዮን ሕዝብ ያካተተና ተመጣጣኝ ታሪፍን የሚከተል ገበያ ወስጥ ትገኛለች፡፡ በርካታ ታላላቅ ባለሃብቶች ምርታቸውን ለማሻጥ ያላቸውን ሰፋያለ ዕድል ሲጠቅሱ ኮሜሳን ያወሳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ የበርካታ ቁልፍ የሆኑ ዓለምአቀፋዊ ስምምነቶች ፈራሚ አገር በመሆኗ የወጪ ባለሃብቶች ሊያጋጥማቸው የሚችልን የኪሣራ አደጋ በመቀነስ ረገድ ምቹ ነች፡፡ እንዲሁም *በአገር ወስጥና በሌሎች አገራት ተወላጆች መካከል የሚፈጠር የኢንቨስትመንት ክርክር ስምምነት ዉል* (ICSID) የሚባለውና የዓለም ባንክ ያወጣው በወጪ ባለሃብቶች መካከል የሚፈጠርን ክርክር የማላገያ ዓለምአቀፍ ስምምነት እንዲሁምየ*ዓለምአቀፍ የኢንቨስትመንት ዋስትና ኤጀንሲ* (MIGA) የሚባለውና ለወጪ ባለሃብቶች ከፖለቲካ ጋር የተያያዙ እንደ ሃብት መወረስ የማሰሉ አደጋዎችና የጦር ጉዳቶች ላይ ዋስትና የሚሰጥ ድርጅት አባል አገር ነች፡፡[59]

ከኢትዮጵያ የሚላኩ ሸቀጦች በሙሉ "ከጦር መሣሪያ በስተቀር" (EBA)[60] በሚባለው ስምምነት መሠረት ተቀባይነት ያላቸው በመሆናቸው በአወሮጳ ገበያዎች ተቀባይነት ለማግኘት በቀላሉ የሚችሉ ሲሆን እንዲሁም የአፍሪካ ዕድገትና ዕድል ሕግ (AGOA) ፈራሚ አገር በመሆኗ ወደ የኢትዮጵያ ሸቀጦች በአሜሪካ ገበያዎች ለማሻጥም ይችላሉ፡፡ ከዚህ ሌላም ከኢትዮጵያ የሚላኩ ሸቀጦች አብዛኛዎቹ *አጠቃላይ የምርጫ አሠራር* (GSP) በሚባለው የአወሮጳ ኅብረትና የአሜሪካ አሰራር የቅድሚያ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህ አሠራር ምክንያት አብዛኛው ከኢትዮጵያ ወደውጭ የሚላክ ሸቀጥ ከኮታ ተጽዕኖና ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ነው፡፡

**ሣጥን ሐ. የፌደራሉ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ**[61]

- ባለሃብቱ ከወጪ ዕቃዎችን ለማስመጣት ከሚከፈለው ቀረጥ ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዲሆን እንዲሁም ዋጋቸው ከካፒታል ዕቃዎቹ ጠቅላላ ዋጋ 15በመቶ የማይበልጥ መለዋወጫዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡
- ሸቀጦችን አምርቶ ወደወጪ ለማላክ የሚጠቀምባቸውን ጥሬ ዕቃዎችና የማሸጊያ ዕቃዎች ከወጪ ለማስገባት ከተጣለው የጉምሩክ ቀረጥና ሌሎች ቀረጦች ነጻ ነው፡፡
- ለወጪ ንግድ የተዘጋጁ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ማንኛውም ወደ ወጪ በሚላክ ሸቀጥና አገልግሎት ላይ የተጣለው ቀረጥ ነጻ ናቸው፡፡
- ዱቤ ለማግኘት የተነደፈው ቀላል አሠራር፡- አንድ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ልማት ባንክ ተቀባይነት ካገኘ፤ ባለሃብቱ ከኢንቨስትመንቱ 30በመቶ የሚሆነውን በዋስትና ገንዘብ ተቀማጭ ካደረገ ባንኩ እስከ 70በመቶ የሚሆን ብድር ይፈቅዳል፡፡
- 50በመቶ የሚሆነውን ምርቱን ወደወጪ የሚልክ ወይም 75በመቶ የሚሆነውን ምርቱን እንደ ምርት ግብዓት ለሌላ ላኪ የሚያደርግ ማንኛውም ባለሃብት ከ 2 – 7 ዓመት ድረስ ከገቢ ግብር ክፍያ ነጻ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
- ነባር የግብርና ድርጅትን በማስፋፋት ወይም በማሻሻል ካሚተው ምርት ቢያንስ 50በመቶውን ወደወጪ በማላክና ምርቱን በ25በመቶ በሜጨምር የሚገኝ ገቢ ለሁለት ዓመት ከገቢ ግብር ክፍያ ነጻ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
- ከገቢ ግብር ነጻ የመሆን መብት በተሰጠበት ዘመን ወስጥ ኪሣራ ያጋጠማቸው የንግድ ተቋማት የገቢ ግብር ነጻ መብቱ ዘመን እንዳለቀ ለግማሽ የነጻ መብቱ ዘመን የደረሰባቸውን ኪሣራ ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

- አንድ ድርጅት በሚዋጋበትም ሆነ በሚፈርስበት ጊዜ በሚደረግ የአክሲዮን ንብረት ሽያጭም ሆነ ማስተላለፍ በሚፈጸምበት ጊዜ አንድ የወጪ ባለሃብት የሚያደርገው ክፍያ ከማንኛውም የግብር ክፍያ ነጻ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከ30 አገራት ጋር የሁለትዮሽ የንግድ ስምምነቶችን አሏት፡፡ እነዚህም አገራት በጣም የተለያዩና ዋንኛ የሆኑ ባለሃብቶች የሚንቀሳቀሱባቸው አገራት ሲሆኑ ከእነዚህም መካከል በርካታዎቹ በኢትዮጵያ ወስጥ በሰፋፊ ሜሬቶች ላይ በግብርና ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በኢትዮጵያ የድርብ (የእጥፍ) ግብር መካላከያ ውል ከ12 አገራት ጋር የፈረመች (እንዲህ ዓይነቱን ውል ሕንድ ከ64 አገሮች ጋር ፈርማለች) እንዲሁም ከ19 አገራት ጋር የኢኮኖሚ ወዳጅነት ስምምነት የፈረመች አገር ናት፡፡[62]

## ሌሎች ማበረታቻዎች

ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ኢትዮጵያ ሌሎች በርካታ አሠራሮች አሏት፡፡[63] እነዚህ ማበረታቻዎች ግልጽ፣ ለሁሉም የሜሬት ይዞታ ስምምነቶች ተመሳሳይ የሆኑ (አንዳንድ ዘገባዎች አድልዖ እንዳለ ቢዘግቡም) እንዲሁም በተለያዩ የግብይት ማስተዋወቂያ መድረኮችና ጽሑፎች የሚተዋወቁ ናቸው፡፡[64] እነዚህ ማዘርዝሮች የሚያተኩሩት የወጪ ንግድን፣ ግብርን፣ የጉምሩክ ቀረጥን፣ የሜሬት ኪራይን፣ ብድርና የመሳሰሉ የተሻሻሉ የፋይናንስ አሠራሮችን በማበረታታት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡[65] ሆኖም በአገር ወስጥ ያለውን የምግብ ምርት አቅርቦት ዋስትና ያለው እንዲሆን የተዘረጉ ምንም ዓይነት ማበረታቻዎች የሉም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ ክልላዊ መስተዳድሮች ራሳቸው በሚፈልጉት መንገድ የቀረጹዋቸውና ከሌሎቹ ክልሎች የተለዩ ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች አሏቸው፡፡ ለምሳሌ የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ባለሃብቱ እንደሚያመርተው የሰብል ዓይነት የተለያየ የሜሬት ኪራይ አከፋፈል ሥርዓትን ይከተላል፡፡[66] ይህም ትርፍ የሚያስገኙ ምርቶችን እንዲሁም እንደሚጠበቅበት በልማት ላይ ያልዋለ የሜሬት ይዞታ ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የታቀደ አሠራር ነው፡፡ በፌደራል ደረጃ ደግሞ "… በልማት ወደኋላ በቀሩ አካባቢዎች ማለትም በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉልና ጉሙዝ፣ ደቡብ ኦሞ፣ አፋር ክልል፣ በሶማሌ ክልልና ወደፊት … በሚወሰኑት ክልሎች …"[67] አካባቢዎች የሚደረግ ኢንቨስትመንት ተጨማሪ ከገቢ ግብር ነጻ የመሆን መብት ይሠጣል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በፌደራል ደረጃ የሚሰጡት ማበረታቻዎች በሙሉ በአገር ወስጥም ሆነ በወጪ ባለሃብት ላይ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

የሜሬት ይዞታን ለሌላ ሰው ስለማስተላለፍ ወይም የሜሬት ይዞታን በዋስ በማስያዝ ገንዘብ ስለማበደር በፌደራልና በክልል ደረጃ የተለያዩ ድንጋጌዎች አሉ፡፡ ይህ የጥናት ቡድን የሜሬት ይዞታቸውን እንደማዣ በማጠቀም ከባንኮች ገንዘብ የተበደሩ በርካታ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች ጋር ተገናኝቷል፡፡ ለግብርና ልማት ሜሬትን እንደ ማዣ አድርጎ ብድር ለመቀበል ያለውን አስቸጋሪነት በተመለከተ መንግሥት የሜሬት ይዞታን መቆጣጠሩ ተገቢ አለመሆኑ ሁልጊዜ በተለምዶ ከሚቀርቡት መከራከሪያዎች አንዱ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታ እንዲኖር አዋጅ ቁጥር 280/1994 ሌሎች ተጨማሪ ከገንዘብ ጋር ያልተነካኩ ማበረታቻዎችን ይሠጣል፡፡ ወስርስን መካላከል፣ ሰራተኞችን በየክልሉ የማዘዋወር ነጻነት እንዲሁም በአገር ወስጥ ባለሙያው ካልተገኘ የወጪ ባለሙያዎችን ለመቅጠር ያለው ቀላል አሠራር ለአብነት ከሚጠቀሱት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በ2001ዓም የተቋቋመው የግብርና ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) ለወጪ ባለሃብቶች የተቀናጀና ቀልጣፋ አገልግሎት ይሠጣል፡፡ እነዚህ ሁሉ ሜሬት ለሚከብ ከወጪ የሚመጡ ባለሃብቶችን በአንድ ማዕከል በማስተናገድ እንዲሁም አሠራሩ የሚወስደውን የጊዜ ማጠን በመግለጽ የሚሠጡት አገልግሎቶች በበርካታ ባለሃብቶች ዘንድ ኢንቨስትመንትን በማበረታታት ረገድ ጠቃሚ ናቸው በማለት በዋንኛነት የጠቀሷቸው ነጥቦች ናቸው፡፡

ለማጠቃለል ያህል ኢትዮጵያ የመጓሻ ካፒታልን በተመለከተ ለቀቅ ያለ መመሪያን የምትከተል ነች፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቀጥተኛ የወጪ ኢንቨስትመንት ፖሊሲ የወጪ ንግድን በተመለከተ የወጪ ባለሃብቶች የተወሰነ የክንውን ግብ እንዲኖራቸው አይጠይቅም፤ ከወጪ ዕቃ ለማስገባት የወጪ ምንዛሪ ገደብ አይደነግግም፤ ለአገር ውስጥ ጥቅም የሚሟሉ ዕቃዎችን ዝቅተኛ ማጠን አይወስንም፤ ከወጪ ስለሚቀጠሩ ባለሞያዎች የቁጥር ገደብ አይሰጥም፡[68]

እነዚህ ሁሉ ማበረታቻዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ማስራት የሚፈልጉ ባለሃብቶችን ለመሳብ የተወጡ ናቸው፡፡ ካሩቱሪ የተባለው የሕንድ ድርጅት ዋና ሥራአስኪያጅ የአበባ ምርት በኢትዮጵያ ለማካሄድ ያለውን ማበረታቻ "ምራቅ የሚያስወጥ" ነው ሲሉ ይገልጹታል፡፡ ይህም የሚያካትተው መንግሥት ለሚቆጣጠረው የአየር ትራንስፖርት የሚከፈለውን ርካሽ የማጓጓዣ ወጪ፣ ግብር የማይከፈልባቸውን ጊዜያትን፣ ሥራው ሲጀመር የሚሰጠው በጣም ዝቅተኛ የሊዝ ክፍያ ማጠን፣ ነጻ የግብር ጊዜያትና ከቀረጥ ነጻ የመሆን መብትን በሙሉ የሚጨምሩ ናቸው፡ "ይህ በእውነቱ ቀይ ምንጣፍ አንጥፎ ለኢንዱስትሪው አቀባበል የሚደረግ ያህል ነው"[69] በማለት የካሩቱሪው ዋና ሥራአስኪያጅ ይናገራሉ፡፡ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ማበረታቻዎች በግብርና ላይ ለተሠማሩ የሜቴት ይዞታ ባለሃብቶች በሙሉ የሚሠጡ ናቸው፡

# 2. የሜት ይዞታ ኢንቨስትመንት ጥናት

"የወረዳ ሜት አለካክ በጣም በግምት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ አንድ ኮረብታ ላይ አንዱ ይቆምና ባሻገር እስካለው ያለውን ኮረብታ ተመልክቶ ሲያበቃ ‹እንግዲህ ይህንን ያህል ነው› በማለት ግምቱ ይሠጣል፡፡"

ለኢንቨስትመንት የሚጠቱን ሜቶች አለካክ በተመለከተ የቤንሻንጉል ክልል ባለሥልጣን ከተናገሩት[70]

## 2.1 አጠቃላይ ወቅታዊ የኢንቨስትመንት ገጽታ

በኢትዮጵያ ስለሚካሄደው የሜት ኢንቨስትመንት በርካታ የሚጃ ምንጮች ቢኖሩም ያለው የስታቲስቲክ ሚጃ ማዛባት፣ ትክክለኛ አለመሆንና ጥንቃቄ ሙደል ይታይበታል፡፡ አብዛኛዎቹ ዘገባዎች ከአገሪቱ ወስጥ በተወሰነ አካባቢ ላይ ብቻ ያተኮሩ ሲሆን የሚጃው ምሉዕነት በጣም ዝቅተኛ ነው (አንዳንዱ ሚጃ ያለውን ወሱንነት ሳንጨምር)፡፡ ሚጃ በአብዛኛው የሚሰበሰበው የመንግሥት ባለሥልጣናትን በግል በማ ጋገር ወይም ከመገናኛ ብዙሃን ከሚሥጠው በማሰብሰብ ነው፡፡ በመንግሥት ደረጃ በተለያዩ ማስሪያቤቶች መካከል ያለው የሚጃ ልወውጥ በጣም ዝቅተኛ ከመሆን ባሻገር የሜት ይዞታን በተመለከተ የተሟከለ አሠራር አለመኖር፣ የግልጽነት ችግር እንዲሁም የሜት ኢንቨስትመንት ወሎች በተመለከተ "የወሰን አከላለል" (ቅየሳንና የማሰሉትን በተመለከተ) ጥቂቶቹ ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው፡፡ ይህ የጥናት ቡድን ያገኘው ሚጃ በአብዛኛው የተሚኮዘው ከመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር በግል ባደረገው ግንኙነት በተሰጠው ላይ የተሚኮዘ ነው፡፡ በሚሁም በአንዳንድ ወቅቶች ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ ያሉት ሚጃዎች ዝርዝር ሲኖራቸው የተቀሩት በርካታ ሚጃዎች በግምታዊ ማጠቃለል ላይ የተመኩዙ ናቸው፡፡

ይህ የጥናት ቡድን ያገኘውን ሚጃ ቦታው ላይ በገሃድ ከሚታየው ጋር ያለውን ልዩነት ለማቀናጀት ባደረገው ጣራ የደረሰበት ድምዳሜ የሚገረው ስታቲስቲክስ ለባለሃብቶች ከሚጠው የሜት ማጠን ያነሰ እንደሆነ ነው፡፡ የጥናት ቡድኑ እስከ ጥር 2003 ድረስ 3,619,509 ሄክታር ሜት ለኢንቨስትመንት እንደተሰጠ ግምቱ ነበረው፡፡ በዚህ የቁጥር ማጠን ላይ ሠንጠረዥ 4 ዝርዝሩን ያቀርባል፣ እንዲሁም ተቀጽላ ሐ የዚህን ሚጃ ድክመት ያብራራል፡፡

<u>ሣጥን መ የካሩቱሪ ከላንያ የሜት ሊዝ ምስጢር</u>

በኢትዮጵያ ከተከናወኑ የሜሬት ኢንቨስትመንት ወሎች መካከል ካሩቱሪ ኩባንያ ያደረገወን ስምምነት ከሁሉም በላይ የመገናኛ ብዙሃንን ቀልብ ስቧል፡፡ በ2000ዓም አካባቢ ይህ ታላቅ የሕንድ ኩባንያ በኢትዮጵያ ወስጥ እያካሄደ ካለው የአበባ ምርት በተጨማሪ ለሰብል ምርት በጋምቤላ ክልል 300ሺህ ሄክታር ሜሬት ለ99ዓመት በሊዝ መወሰዱ ተሰሚ፡ ይህንን ያህል ትልቅ የእርሻ ሜሬት በኪራይ የተረከበበት ዋጋ ደግሞ ከ15 እስከ 20 ብር (በዶላር 1.25) መሆኑ አብሮ ተነገረ፡፡ ይህ እንግዲህ በኢትዮጵያ ወስጥ ከወጪ ባለሃብቶች ጋር ከተካሄዱት የሜሬት ኢንቨስትመንት ወሎች መካከል የፌዴራሉ መንግሥት በጉዳዩ ወስጥ ሳይገባ ካሩቱሪ ከጋምቤላ ክልል ማስተዳደር ጋር የፈጸመው ወል ነው፡፡

የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) እንደሚለው ከሆነ ይህ ወል ከካሩቱሪ ጋር ከተፈጸመ በኋላ ከ2001ዓም ጀምሮ የፌራደራሉ መንግሥት ከ5ሺህ ሄክታር ሜሬት በላይ የሆኑ የሰፋፊ ሜሬቶችን ወል በራሱ ማከናወን ጀመረ፡፡ የዳይሬክቶሬቱ ቃል አቀባይ ይህንን አስመልክተው ለዚህ የጥናት ቡድን እንደተናገሩት የማከስፊ ሜሬቶችን ወል፣ የሊዝ ዘመኑ መርዘም፣ የኪራይ ተመኑ ማነሱ፣ ወዘተ ያስከተሉትን ነገሮች ከተመለከተ በኋላ መንግሥት ወደፊት በሚደረጉ ወሎች ላይ ኃላፊነቱን ለመወሰድ በመወሰን ከካሩቱሪ ጋርም ሊዙን እንደገና ተደራድሮበታል፡፡ የዳይሬክቶሬቱ ኃላፊ የሆኑት አቶ ኢሣያስ ከበደ ለካሩቱሪ የተሰጠው ሜሬት 300ሺህ ሳይሆን 100ሺህ እንደሆነ እንዲሁም የሊዙ ዘመን ለ30ዓመታት እንደሆነና ዋጋወም በሄክታር 111ብር (7ዶላር በሄክታር) እንደሆነ ለዚህ የጥናት ቡድን ገልጸዋል፡፡ በጽሕፈት ቤታቸው ግድግዳ ላይ የተለጠፈው ካርታም የተሰጠው የሜሬት መጠን 100 ሺህ 136 ሄክታር እንደሆነ ያሳያል[71]፡፡

ካሩቱሪ ግን በመገናኛ ብዙሃን ሁልጊዜ እንደሚናገረው ከሆነ የሜሬቱ መጠን 300ሺህ ሄክታር እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህም በማነሳት በአብዛኛው ዘንድ ያለው ግምት ምናልባት 100ሺህ ሄክታር አሁን ለአጭር ጊዜ ተሰጥቶ ቀሪው ደግሞ (እስከ 300ሺህ ሄክታር ያለው) የአፈጻጸሙ ሁኔታ እየተገመገመ እንዲካሄድ ተብሎ ይሆናል የሚል ነው፡፡ ሌሎች እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ የሜሬቱ መጠን ተቀንሷል ብሎ ይፋ ማድረግ የካሩቱሪን አክሲዮን ዋጋ ክፉኛ ሊጎዳው ስለሚችል ይሆናል (ኩባንያው 300ሺህ ሄክታር ሜሬት ሚከቡን ባስታወቀ ጊዜ የአክሲዮን ዋጋው ማሻቀቡን ልብ ይሏል) በመጀሚያው የሜሬት መጠን የጸኑት የሚል አመለካከት አለ፡፡ ካሩቱሪ ከወሰደው 100ሺህ ሄክታር አካባቢ ያለወን ሜሬት በመመልከት ቀሪው 200ሺህ ሜሬት የት እንደሚሆን ግልጽ የሆነ ነገር የለም፤ በአቅራቢያው ያለው ሜሬትም ለሌሎች እየተሰጠ ይገኛል፡፡ (ያለው ግምት ግን ኩባንያው አሁን ከወሰደው 100ሺህ ሄክታር አካባቢ እንደሚሆን ነው) እወነታው 100ሺህ ሄክታር ይሁን 300ሺህ ሄክታር ወይም በእነዚህ ቁጥሮች መካከል፤ ካሩቱሪ

ለመላው ዓለም እንደተናገረው የ300ሺህ ሄክታር ሜሬት ሚከቡ ጉዳይ ያለቀለት አይደለም፡፡

የሜሬት ኢንቨስትመንትን በተመለከተ የሚተዋወቅና ሽያጭ በስፋት የሚካሄደው በአራት ክልሎች ነው፡፡ (እነዚህም፡ የጋምቤላ፣ የደቡብ ሕዝብ፣ የቤንሻንጉል እና የኦሮሚያ ክልሎች ናቸው) ከእነዚህ ክልሎች መካከል የዚህ ጥናት ቡድን ወደ ደቡብ ክልል ሜድ ባይችልም የማስረተልማዙን እድገትና የሚወጡትን ወገናዊ ዘገባዎች በመመልከት ብቻ የሜሬት ኢንቨስትመንት እየተጧጧፈ እየሄደ እንደሆነ ለሚዳት ይቻላል፡፡ በፌደራል ደረጃ በተለይ የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በየካቲት 2001ዓም ከተቋቋመ በኋላ በድምሩ 200ሺህ ሄክታር በሚሆን ሜሬት ላይ 16 የኢንቨስትመንት ስምምነቶች ተደርጓል[72]፡፡ እነዚህ ስምምነቶች እያንዳንዳቸው ከ5ሺህ ሄክታር በላይ ሲሆኑ ሁሉም ከወጪ ባለሃብት ጋር የተደረጉ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ እንደሚለው ከሆነ ከ1997 ጀምሮ 1ሺህ100 የወጪ ባለሃብቶች የተመዘገቡ ሲሆን (64ቱ ብቻ ናቸው ተግባራዊ ሥራ የጀመሩት) ከ5ሺህ ሄክታር በላይ 72 የወጪ ባለሃብቶች የኢንቨስትመንቶች ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ (ከ2.9 ሚሊዮን ሄክታር በላይ ሜሬት ላይ የ36.5 ሚሊዮን ብር ወይም የ2.2

ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ማለት ነው) ከዚህ ሁሉ ጥያቄ ምን ያህሉ እንደጸደቀ ግልጽ የሆነ ማስረጃ የለም[73]፡፡

ይህንን ዓይነት ስምምነት አስመልክቶ ከክልላዊ ማስተዳድሮች የሚሰጠው ዘገባ ተዓማኒነት የሌለወና ተለዋዋጭ ከመሆን አልፎ በክልሎችና በፌደራሉ መንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ የየትኛወም ክልላዊ ማስተዳደር ቢሮ በክልሉ ወስጥ ከሚገኘው መሬት ምን ያህሉን የፌደራሉ መንግሥት እንደፈቀደ የሚያወቀው ነገር የለም፡ ፡ እንዲሁም የፌደራሉ መንግሥት የክልል ማስተዳድሮች ምን ያህል መሬት ለባለሃብቶች እንደሰጡ የሚያወቀው ሚጃ የለም፡፡ የአንደኛው ክልላዊ ማስተዳደር የኢንቨስትመንት ቢሮ እንዳማለከተው ክልላቸው በየጊዜው ለባለሃብቶች የተሰጠውን መሬት የሚዘረዝር ቅጽ እየሞሉ ከመላክ በላይ በየመሥሪያዎቻቸው መካከል ከዚህ የበለጠ ግንኙነት እንደሌለ ጠቁመዋል፡፡ ከዚህም ሌላ በአንድ ክልላዊ ማስተዳደር ሥር የሚገኙ የተለያዩ ባለሥልጣናት በጉዳዩ ላይ የተለያየ አኃዝ ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ ማስተዳደር ኢንቨስትመንት ቢሮ 271ሺህ ሄክታር መሬት ለ220 ያህል ባለሃብቶች እንደተሰጠ ይናገራል፡፡ ይህ እንግዲህ ለሸምበቆ ፕሮጀክት ከተሰጠው 390ሺህ ሄክታር በተጨማሪ ማለት ነው፡፡ በጋምቤላ የክልሉ ባለሥልጣናት 256ሺህ ሄክታር መሬት በሊዝ እንደተሰጠ ይናገራሉ (ይህም ለካሩቱሪ የተሰጠውን 100ሺህ ሄክታር መሬት ጨምሮ ማለት ነው)፡፡ የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እንደሚለው ከሆነ ደግሞ 188ሺህ 540 ሄክታር የመሬት ይዞታ እስከ 1999 ድረስ ለ889 ባለሃብቶች ማስጠቱን ከእነዚህም መካከል 45ቱ የወጪ ዜጎች መሆናቸውን ይናገራል፡፡ ለወጪዎቹ ዜጎች ከተሰጠው የሦስቱ የመሬት ስፋት ከ10ሺህ ሄክታር በላይ ሲሆን ከ1999 ዓም በፊት ያለውን ሚጃ "በበጀት እጥረትና በቅንጅት ጉድለት" ምክንያት ማግኘት እንደማይቻል የኢንቨስትመንት ቢሮው ይናገራል[74]፡፡

በተጻራሪው ግን የዓለም ባንክ በ2002ዓም "በእርሻ መሬት ላይ እየጨመረ የመጣው ዓለምአቀፍ ፍላጎት፤ ቀጣይነትና ተመጣጣኝ ጥቅም ያስገኝ ይሆን?" (*Rising Global Interest in Farmland: Can it Yield Sustainable and Equitable Benefits*) በሚል ርዕስ ያወጣው ዘገባ ከ1996 እስከ 2000 ድረስ ባሉት ዓመታት 1.2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለ406 ባለሃብቶች በአምስቱም ክልሎች እንደተሰጠ ይዘግባል፡፡ በመሆኑም ከዚህ መሬት ላይ 49በመቶ የሚሆነው ለአገር ወስጥ ባለሃብቶች የተሰጠ ሲሆን 5በመቶ ብቻ የሚሆኑት ወይም 23ቱ በአማካይ 4ሺህ ሄክታር መሬት የወሰዱ የወጪ ባለሃብቶች ናቸው፡፡ ቀሪው 383 ባለሃብቶች ማለትም 95በመቶው የአገር ወስጥ ባለሃብቶች ሲሆኑ እነዚህም በአማካይ የወሰዱት የመሬት መጠን 616 ሄክታር ነው፡፡

ሌላ ዘገባ ደግሞ ከዚህ የተለየ ሚጃ ይሰጣል፡፡ ይህ በ2001ዓም "መሬት ነጠቃ ወይስ የልማት ዕድል?" *(Land Grab or Development Opportunity?)* በሚል ርዕስ የወጣ ዘገባ እንደሚለው ከሆነ ከ1996 እስከ 2001 ድረስ በነበሩት ዓመታት 602ሺህ 760 ሄክታር መሬት እንደተሰጠ ሲዘግብ ይህም የ78.5 ሚሊዮን ዶላር የካፒታል ወጪ እንደሚያካትት ይናገራል፡፡ ከዚህ ወስጥ 362ሺህ ሄክታር መሬትና 56ሚሊዮን ዶላሩ ከአገር ወስጥ ኢንቨስትመንት ሲሆን ይህም 240ሺህ ሄክታር እና 24ሚሊዮን ዶላር ከሆነው የወጪ ኢንቨስትመንት ጋር የሚጻጸር ነው፡፡ ማጠቃለፊ (ከ5ሺህ ሄክታር በላይ) ኢንቨስትመንቶችን በተማለከተ የአገር ወስጥ ኢንቨስትመንቱ 12.6 ሚሊዮን ዶላር የካፒታል ወጪ 286ሺህ ሄክታር መሬት የጠቀለለ ሲሆን 10.8 ሚሊዮን ዶላር የሚሆነው የካፒታል ወጪ 210ሺህ ሄክታር የሚሆነው መሬት ለወጪ ኢንቨስትመንት እንዲዉል መደረጉ በንጽጽር ሊታይ ይገባዋል፡፡ (አንድ ማስተዋል የሚገባው አስፈላጊ ጉዳይ እነዚህ ቁጥሮች ሁሉ በዕቅድ የተያዙ የካፒታል ወጪዎች እንጂ በተግባር የተከናወኑ አለመሆናቸውን ነው)፡፡

ከዚህ በላይ በተሰጡት የተለያዩት መረጃዎች መሠረት አንድ ግልጽ የሆነ ነገር መናገር ይቻላል፡፡ በመጀመሪያ፣ ምንም እንኳን እጅግ ሰፋፊ ቦታዎች እየተሰጡ ቢሆንም ከእነዚህ ውስጥ ሥራ በመጀመር ምርት እያመረቱ የሚገኙት ጥቂት ፕሮጀክቶች ብቻ መሆናቸው ነው፡፡ በቤንሻንጉል ጉሙዝ የሚገኝ አንድ መደብ (መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት) መሬት ከተረከቡት ውስጥ 5በመቶው ብቻ ሥራ መጀመራቸውን ይናገራል፡፡ ሁለተኛው፣ ምንም እንኳን መጠነ ሰፊ የመሬት ይዞታዎች ማስጠቱ የመገናኛ ብዙሃንን ትኩረት ቢስብም በአገር ውስጥ ለኢንቨስትመንት የተሰጠው ተመሳሳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ሦስተኛ፣ ለኢንቨስትመንት በተሰጠው የመሬት መጠንና በእርግጠኛነት በሊዝ በተሸነሸነው ሄክታር መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ "እርግጠኛ ነው" ተብሎ የሚነገረው መረጃ ባልተሟላና ጥቃቅን በሆኑ የመረጃ ምንጮች ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡

ከዚህ በታች የሚገኘው ሠንጠረዥ 4 ይህ የጥናት ቡድን ከእያንዳንዱ ክልል ያገኘውንና ትክክል ነው ተብሎ የሚታመነውን መረጃ ጠቅለል ባለ መልኩ የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህ ቁጥሮች የተገኙት ከዚህ በላይ ከተጻፈው ዘገባ ላይ፣ የመሬትን ኢንቨስትመንት በተመለከተ ከመንግሥት ባለሥልጣናት በቀጥታ የተገኘ፣ ከባለሃብቶች፣ ይህ የጥናት

ቡድን በግምገማ በማግኘት ካጠናቀረው፣ ከመገናኛ ብዙሃን ዘገባ፣ እንዲሁም የመሬትን ይዞታ በተመለከተ ዓለምአቀፋዊ መረጃ ከሚሰበስበው የመረጃ ምንጭ በማጠናቀር ነው፡፡ ስለሆነም እነዚህ ቁጥሮች በትክክል አለማግኘታቸው የመሬት ኢንቨስትመንትን እውነተኛ ገጽታ እንደሚያሳዩ ግልጽ ቢሆንም በተቻለ መጠን የተገኘውን መረጃ ሁሉ በዚህ ሠንጠረዥ ውስጥ ለማካተት ጥረት ተደርጓል፡፡ የጥናት ቡድኑ በተቻለው አጋጣሚ በኢትዮጵያ ውስጥ በመሬት ኢንቨስትመንት ላይ የሚካሄደውን በተመለከተ የመረጃዎቹን ጥንቅር ትክክለኛ በሆነ መንገድ ለማካናወን ቢጥርም በመጨረሻ በተቀጽላ ሐ ላይ በዝርዝር እንደተገለጸው መረጃው ያለውን ግድፈት ተዘርዝሯል፡፡ ከዚህ በታች ያለው ሠንጠረዥም በእያንዳንዱ ክልል እየተከናወነ ያለውን በጥንቃቄ የሚመረምርና በአሁኑ ወቅት ያለውን የመረጃ ትክክለኛነት የሚዳስስ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ዝርዝር ማስፈርት/ደረጃ ምደባ በተቀጽላ ሐ ላይ ተሰጥቷል፡፡

| ሠንጠረዥ 4፡ የሜሬት ኢንቨስትመንት ስታቲስቲክ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ክልል | ከፌደራል የተገኘ በሄክታር | የክልሉ ስፋት | የተዘጋጀ በመቶ (%) | የተሰጠ በመቶ (%) | የተዘጋጀና የተሰጠውድምር በመቶ (%) | የተሰጠ የሜሬት ይዞታ | የባለሃብት ቁጥር | እስካሁን ያለው | ጥልቀት |
| ጋምቤላ | 829,199 | 2,580,200 | 32% | 10% | 42% | 256,000 | 202 | መካ-ከፍ* | መካከለኛ |
| ደቡብ ሕዝብ | 180,625 | 11,093,100 | 2% | 4% | 6% | 470,287 | 8 | መካከለኛ | መካከለኛ |
| ቤንሻንጉል | 691,984 | 4,928,900 | 14% | 13% | 27% | 635,831 | 220 | ከፍተኛ | ከፍተኛ |
| አፋር | 409,678 | 9,670,700 | 4% | 0% | 4% | 11,000 | 1 | አይታወቅም | ዝቅተኛ |
| ኦሮሚያ | አለ | 35,300,700 | አይታወቅም | 4% | አይታወቅም | 1,319,214 | 899 | መካከለኛ | መካከለኛ |
| ትግራይ | አይታወቅም | 8,000,000 | አይታወቅም | 1% | | 46,105 | | አይታወቅም | ዝቅተኛ |
| ሶማሊ | አይታወቅም | 27,925,200 | አይታወቅም | 0% | | 6,052 | | አይታወቅም | ዝቅተኛ |
| አማራ | አለ | 15,917,400 | አይታወቅም | 1% | | 175,000 | 3 | አይታወቅም | ዝቅተኛ |
| ሌሎች ክልሎች | አይታወቅም | አይታወቅም | አይታወቅም | | | 500,020 | | አይታወቅም | ዝቅተኛ |
| ፌደራል | አይታወቅም | አይታወቅም | አይታወቅም | | | 200,000 | 16 | ከፍተኛ | መካከለኛ |
| **ድምር** | 2,111,486 | | | | | 3,619,509 | 1349 | | |
| *መካ-ከፍ ማለት ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ | | | | | | | | | |
| ምንጭ የጥናት ቡድኑ ምልከታ | | | | | | | | | |

## 2.2 የሜሬት ኢንቨስትመንት መሠረታዊ ሞዴሀ

የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) እንደሚለው ከሆነ እርሻ ላይ ያተኮረ የሜሬት ኢንቨስትመንት ለኢትዮጵያ ልማት ወሳኝነት ያለው ነው፤ ምክንያቱም ለወጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሁም ገበሬዎች ወደ ዘመናዊ የግብርና መንገዶች እንዲዛወሩ በማገዝ በኩል ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው ዳይሬክቶሬቱ አስተያየቱን ይሰጣል፡፡ ከዚህም ባሻገር ደመወዝ የሚከፈላቸውንና የግል ሥራዎችን በማበረታታት አገሪቱ እንድትጠቀም ያደርጋል፡፡ የወጪ ምንዛሪ ማጠባበቂያ ይጨምር ዘንድ ከፍተኛ ፍላጎት ባለበት ባሁኑ ጊዜ ገንዘብ የሚያስገኙ ሰብሎችን (የሸንኮራ አገዳ፣ ጥጥ፣ ሩዝ ወዘተ) ለማምረት የሚያስችል የኢንቨስትመንት ማበረታቻና የግብይት ጥረት በስፋት ይደረጋል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን እንዲህ ዓይነቱ ኢንቨስትመንት አካሄድ የረጅም ጊዜ የምግብ ዋስትናን ተግባራዊ ያደርጋል ብለው ከሚያምኑ በርካታ ባለሃብቶች ጋር እንዲሁም ከመንግሥት መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር ተነጋግሯል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ኢህአዴግ በሜሬት ኢንቨስትመንት ላይ ያለው ፍላጎት አገር በቀል የአንድ አካባቢ ተወላጅ የሆነውን ሕዝብ ከየቦታው በማስነሳት፣ በማግለልና ኃይሉን በማሳጣት ሕዝቡ ከመንግሥት በዕርዳታ

በሚሰጠው የምግብ ዕርዳታ ላይ ጥገኛ እንዲሆን በማድረግ በቆላ አካባቢዎች የሚገኙ የአርነት ቡድኖች (አማጺያን) ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅለው እንዳይታገሉ ለማድረግ ነው በማለት የሚከራከሩ አሉ፡፡ ከሜሬት ጋር የተያያዙ ሃብቶች ኢህአዴግን ለሚደግፉ የትግራይ ተወላጆችና ለከተማው ልሒቃን የማስጠቱ ጉዳይ መንግሥትን ሚደገፍ በልዩና አድሎዓዊ መንገድ ለማጠቀም እንደሚያስችል የሚቀርብ ሌላ የመከራከሪያ ነጥብ ነው፡፡

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ያለው ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታ አገሪቱን ከወጪ ለሚመጣ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ማስህብ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ እንደ ሠራተኛ ጉልበት የመሳሰሉ ዝቅተኛ ወጪ የሚያስከትሉ ግብዓቶች፣ የአዋጆች ወስብስብ አለማሆንና የአሠራር ሂደቶች ቀልጣፋነት፣ በርካታ ለእርሻ ምቹ የሆኑ የሜሬት ይዞታዎች ማግኘት፣ ስትራቴጂካዊ የቦታ አቀማመጥ፣ የንግድ ስምምነቶችና በርካታ የወሃ አቅርቦት መኖር በኢትዮጵያ ንግድ ማካሄድ ምንያህል አትራፊ እንደሆነ ከብዙ በጥቂቱ የሚያሳዩ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በማጨረሻም በዓለም ላይ ያለው ሁኔታ ለእርሻ ኢንቨስትመንት ምቹነት አለው፡፡ እነዚህም ሁኔታዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የምግብ ዋጋ መጨመር፣ የኢንዱስትሪ ዕድገት ሲጨምር ለምግብና የአግሮነዳጆችን ያለው ፍላጎት አብሮ ማደግ እንዲሁም የሕዝብ ቁጥር ማደግ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

## 2.3 ምን ያህል ሜሬት ነው የተዘጋጀ ነው?

በኢትዮጵያ ወስጥ ለኢንቨስትመንት የተዘጋጀው የሜሬት ማጠን ምን ያህል እንደሆነ ሚጃ ለማግኘት አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን ትክክለኛነቱም እንደ ሚጃው ምንጭ የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ የግብርና እና የገጠር ልማት ሚኒስትር በ2001 ዓም በኢትዮጵያ ያለው የግብርና ኢንቨስትመንት ብቃት (*Agricultural Investment Potential of Ethiopia*) በሚል ለሰብል ምርት፣ ለከብት እርባታ እና ከተለመደው ወጪ ለሚሆሚቱት እንደ ዓሣ ምርት፣ ሐር፣ ማር፣ ወዘተ ላሉት የምርት ዓይነቶች የተዘጋጀወን ምቹ ቦታ ይዘረዝራል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚያማለከተው ከሆነ 3ሚሊዮን ሐክታር ለጥጥ ምርት፣ 1.6 ሚሊዮን ሐክታር ለዘይት ሰብሎች፣ 280ሺህ ሐክታር ለሩዝ፣ ወዘተ እንደሆነ ይተነትናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በቆላማ ስፍራዎች ካሉት ሰፋፊ የሜሬት ይዞታዎች ሌላ በአማራና በኦሮሚያ ክልሎችም ሰፋፊ ቦታዎች እንዳሉ ይጠቁማል፡፡

ሠንጠረዥ 5፡ ለየሰብል ዓይነቱ የተዘጋጀ ሜሬት (በሺዎች ሐክታር)

| | ደቡብ ሕዝብ | ጋምቤላ | ኦሮሚያ | አፋር | አማራ | ቤንሻጉል | ትግራይ | ሶማሊ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሩዝ | 75 | | 25 | | 30 | 50 | | 100 | 280 |
| በቆሎ | 300 | 200 | 150 | | 300 | 200 | | 250 | 1400 |
| አበባ | 346 | | 150 | | 270 | | | | 766 |
| በቦና | 155 | 20 | 246 | | 5 | | | | 426 |
| ሻይ | 75 | 15 | 55 | | 5 | | | | 150 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅመም | | | | | | | | | 0 |
| ጥጥ | 601 | 316 | 407 | 200 | 679 | 303 | 269 | 225 | 3001 |
| የዘይት ሰብል | 4 | 19 | 185 | 8 | 541 | 715 | 125 | 4 | 1601 |
| የባቄላ ዓይነቶች | 390 | | 526 | | 689 | 25 | 20 | | 1650 |
| ጎማ | 150 | 50 | | | | | | | 200 |
| የዘንባባ ዘይት | 300 | 100 | 50 | | | | | | 450 |
| ምንጭ የግብርና እና የገጠር ልማት ሚኒስትር በ2001 ዓም በኢትዮጵያ ያለው የግብርና ኢንቨስትመንት ብቃት[75] | | | | | | | | | |

**ሠንጠረዥ 6፡ በፌደራሉ የሜሬት ባንክ የሚገኝና በአፌደራ ለግብይት የቀረበ**

| ክልል | በአጠቃላይ የቀረበው ሜሬት በሔክታር | ከስ ቦታዎች ብዛት | አማካይ የሜሬት ማጠን | የክልሉ ስፋት | ከክልሉ የቀረበውበመቶ (%) |
|---|---|---|---|---|---|
| ጋምቤላ | 829,199 | 7 | 118,457 | 2,580,200 | 32% |
| ደቡብ ሕዝብ | 180,625 | 4 | 45,156 | 11,093,100 | 2% |
| ቤንሻንጉል | 691,984 | 4 | 172,996 | 4,928,900 | 14% |
| አፋር | 409,678 | 9 | 45,520 | 9,670,700 | 4% |
| **ድምር** | 2,111,486 | 24 | 87,979 | | |

በአጠቃላይ ያለው አዝማሚያ ከ3.6 እስከ 4.5 ሚሊዮን ሔክታር ሜሬት በኢትዮጵያ ለንግድ ተኮር የሜሬት ኢንቨስትመንት እንዲወል የተዘጋጀ መሆኑ ነው፡፡ የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) ቃልአቀባይ እንደሚለው ከሆነ 1.2ሚሊዮን ሔክታር የሚሆነው በኦሮሚያ፣ 1.4ሚሊዮን ሔክታር በቤንሻንጉል፣ 1.2ሚሊዮን ሔክታር በጋምቤላ እንዲሁም 300ሺህ ሔክታር በደቡብ ሕዝብ ተዘጋጅቶ ይገኛል፡፡ ከዚህ ወስጥ 1.7 ሚሊዮን ሔክታር ከጋምቤላ (7 ኪስ ቦታ፣ 830ሺህ ሔክታር) በደቡብ ክልል (4 ኪስ ቦታ፣ 180ሺህ ሔክታር) እና በቤንሻንጉል (4 ኪስ ቦታ፣ 692ሺህ ሔክታር) በፌደራሉ የሜሬት ባንክ ተቀማጭ ሆኗል፡፡[76] ቀሪው (ከ1.9 እስከ

2.8 ሚሊዮን ሔክታር) ወደ ፌደራሉ ባንክ ገቢ ያልሆነው ለማስፋፊያ ሰፊ ኢንቨስትመንት የሚጠቅሙ ወይም ትናንሽ የተሰባጠሩ የመሬት ይዞታዎች ሲሆኑ እነዚህም ይዞታዎች በክልላዊ ማስተዳድሮች ለባለሃብቶች እንዲሰጡ ተመድበዋል፡፡ ሆኖም ግን የመሬት ባንክ ከተቋቋመ ወዲህ የክልል ማስተዳድሮች በርካታ ሰፋፊ የመሬት ይዞታዎች ከእነርሱ ቁጥጥር በመውጣታቸው የፌደራሉ መንግሥት ያለ ክልሎች ተሳትፎ በራሱ ቁጥጥር ሥር እያደረጋቸው መሆኑ እያሳሰባቸው መሆኑን በርካታ ማስተዳድሮች ገልጸዋል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን ያነጋገራቸው ጥቂት የዘርፉ ተወካዮች የመሬት ባንኩ ብቃት ያላቸውና ወጤታማ ማስፋፊያ የመሬት ይዞታዎችን ለወጪ ባለሃብቶች ለማዳረስ አመቺ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በበኩሉ በአፋር ክልል ሰፊ የመሬት ይዞታዎች በቅርቡ ለኢንቨስትመንት እንደሚዘጋጁ ገልጸዋል፡፡ የኢፌዴሪ መንግሥትም በታችኛው አዋሽ ሸለቆና በአካባቢው ወስጥ ከ410 ሺህ ሔክታር በላይ 9 ከስ ቦታዎችን ለሽያጭ የማቅረቡን ሂደት ቀጥሎበታል፡፡ በአፋር ክልል ለሚገኙና መተዳደሪያቸው በአዋሽ ወንዝ ላይ ለተመሠረተው ዘላኖች (አርብቶአደሮች) የታችኛው አዋሽ ሸለቆ ቦታ ወሳኝ ጥቅም ያለው ነው፡፡

የዳይሬክቶሬቱ ባልደረባ የሆኑት አቶ ኢሣያስ ከበደ በደጋማው ክልል የሚገኙት የኢንቨስትመንት ቦታዎች እንደ አትክልትና የአበባ እርሻ ሥራዎችን ለማከናወን አመቺ በሆኑ በትናንሽ ቦታዎች ላይ የተዘጋጁ ናቸው ይላሉ፡፡ በእነዚህ ቦታዎች ያለው የተስፋፋ የመሠረተልማት እንዲሁም ከማስተኛ አርሶአደሮች ጋር በኅብረት ለመሥራት ያለው አማራጭ ከፍተኛ ነው፡፡ ሆኖም በቆላማው ክልል የመሠረተልማቱ ያልተስፋፋ ከመሆኑ ባሻገር የመሬቱ ይዞታ ሰፋፊና ተያያዥ በመሆኑ ጥራጥሬ፣ የባቄላ ዓይነቶች ወይም የዘይት ሰብሎችን ለማምረት ከማስፋፊያ በላይ ተስማሚ ነው፡፡

## 2.4 ባለሃብቱ ማነው?

በኢትዮጵያ መዋዕለንዋያቸውን እያፈሰሱ ካሉት መካከል አብዘኛዎቹ የግል ኩባንያዎች ሲሆኑ ከእነዚህም ወስጥ ብዙዎቹ የሕንድ ኩባንያዎች ናቸው፡፡ ይህ የጥናት ቡድን ባካሄደው ምርምር መሠረት የኢንቨስትመንት ፈንድ ወይም የዋስትና ተቀማጭ (hedge funds) ኩባንያዎች (በሌሎች የአፍሪካ አገራት እንዳደረጉት) በቀጥታ በኢትዮጵያ ወስጥ የኢንቨስትመንት ሥራ እያከናወኑ ስለመሆናቸው የተገኘ ግልጽ ማስረጃ የለም፡፡ ሆኖም ግን እንደነዚህ ዓይነት ኩባንያዎች ሌሎች በኢትዮጵያ ወስጥ በእርሻ ሥራ ላይ በተሰማሩ ኩባንያዎች በማጠቀም በተዘዋዋሪ መዋዕለንዋያቸውን አላፈሰሱም ማለት አይቻልም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ያለው ሚኒ እንደሚጠቁመው እስካሁን በቀጥታ በእርሻ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሁለት አገሮች (ጅቡቲና ግብጽ)[77] ብቻ መሆናቸውን ነው፡፡ በኢትዮጵያ መሬት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በመዋሉ በማንኛውም ጊዜ የሚደረጉ ድርድሮችም ሆነ ስምምነቶች ከፌዴራሉ መንግሥት ጋር ወይም ደግሞ ከክልል ማስተዳድሮች ጋር ነው፡፡ ወደፊት ወደ ድርድር የሚጠሩ የንግድ ሊዝ ዝወወሮች ቢኖሩም እስካሁን የግል ባለሃብቶች ከግለሰቦች ጋር ያደረጉት ስምምነት የለም፡፡



የአኙዋክ ሴት የቀድሞ የእርሻ ማሳደሯ አቋርጣ የአጎራባች ማደር ለማጠቀም ስትጓዝ

## የወጪ ባለሃብቶች

ምንም እንኳን ስለ ሁሉም የወጪ ባለሃብቶች ትክክለኛና የተሟላ ሚረጃ ባይገኝም ካለው ሁኔታ በማሳት ግን አንዳንድ አቅጣጫዎችን ማጠቆም ይቻላል፡፡ ከሚልከዓምድራዊ አቀማመጥ በማሳት ከባሕረ ሠላጤው አገራት እንዲሁም ከሕንድ (በግለሰብ ደረጃ ከፍተኛ የሚሬት ይዞታ ይዘዋል) ከፍተኛ ማጠን ያለው ኢንቨስትመንት እየተካሄደ እንደሆነ ለማናገር ይቻላል፡፡

በሜዕድን ቁፋሮና የሙሥረተልማት ግንባታ ቻይና ቀዳሚ ብትሆንም በሚያስገርም ሁኔታ ከሚሬት ኢንቨስትመንት ስምማቶች ሁሉ ስትርቅ ቆይታለች፡፡ ሆኖም በቅርቡ የተገኙ ሚረጃዎች እንደሚጠቁሙት አንድ የቻይና ኩባንያ በጋምቤላ ክልል የሸንኮራ አገዳ ለማምረት የ25 ሺህ ሐክታር የሚሬት ስምማት ለመቀበል ዝግጅቱን አጠናቅቆ ለፊርማ እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡ ይህም ሲጠናቀቅ ኩባንያው በኢትዮጵያ ማዋዕለንዋዩን ለማፍሰስ የሚጀምሪያው የቻይና ድርጅት ይሆናል፡፡[78]

### ሠንጠረዥ7፡ በሚሬት ይዞታዎች ላይ ሃብታቸውን ያፈሰሱ ሕንዳውያን[79]

| ኩባንያ | መጠን በሔክታር | ምርት | ክልል |
|---|---|---|---|
| ካሩቱሪ | 100,000 | ሩዝ፣ የዘንባባ ዘይት፣ በቆሎ፣ የሸንኮራአገዳ | ጋምቤላ |
| ካሩቱሪ | 11,000 | | ኦሮሚያ |
| ካሩቱሪ | 100 | የአበባ ምርት | ኦሮሚያ |
| ሩቺ ሶያ | 25,000 | አኩሪአተር | ጋምቤላ |
| ቢ.ኤች.ኦ. አግሮ | 25,000 | ለነዳጅየሚውሉ ሰብሎች | ጋምቤላ |
| ሻፖርጂ ፓሎንጂና ኩባንያው | 50,000 | የእጣን ዛፍ (Pongamis pinnata) | ? |
| እማሚባዮቴክ | 100,000 | የምግብ ዘይት | ኦሮሚያ |
| ሶናቲ የአግሮ ፋርምኩባንያ | 10,000 | ሩዝ፣ ጥራጥሬዎችና የባቄላ ዓይነቶች | ጋምቤላ |
| ሮምተን አግሪ ኃ.የተ.ግ | 10,000 | ቲማቲም | ኦሮሚያ |
| አልሚዳ | 28,000 | ስኳር | ኦሮሚያ |

## የአገር ውስጥ ባለሃብቶች

የአብዛኛው የመገናኛ ብዙሃን አትኩሮት በውጪ ተወላጆች ስለተያዙት በሰፋፊ የእርሻ ቦታዎች ሆኖ ሳለ በአገር ውስጥ ባለሃብቶች እየተወሰዱ ያሉት አነስተኛ የመሬት ይዞታዎች በአጠቃላይ የመሬት ኢንቨስትመንት ላይ ያለው ተጽዕኖ ቀላል አይደለም፡፡ ከዚህ በላይ በንዑስ ክፍል 2.1 እንደተወሳው አብዛኛዎቹ ባለሃብቶች (95 በመቶ የሚሆኑት) ከአገር ውስጥ ሲሆኑ በአጠቃላይ ለባለሃብቶች ከተሰጠው መሬት ከግማሽ በላይ የሚሆነው በእነዚሁ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች የተያዘ ነው፡፡ በአጠቃላይ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ባህርይ መሠረታዊ የቴክኖሎጂ እሴቶችን ማጠቀማቸው፣ የእርሻ መሬታቸው አነስተኛ መሆኑ፣ ምርት ለመጀመር መፍጠናቸው፣ ከሚጠቀሙት ቴክኖሎጂ አንጻር በአንድ ሔክታር ላይ በርካታ ሠራተኞች መቅጠራቸው፣ እንዲሁም ከውጪ ባለሃብቶች ጋር ሲነጻጸሩ ብቃታቸውም ሆነ ያላቸው ልምድ ዝቅተኛ መሆኑ ተጠቃሽ ነው፡፡

ከበርካታ ነዋሪዎች የሚሰማው አቤቱታ እነዚህ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች እርሻን በተመለከተ ተገቢውን ዕውቀትም ሆነ ችሎታ የላቸውም የሚል ነው፡፡ በአገር ውስጥ ባለሃብቶች ተወስዶ በተገቢው መልኩ ሰብል ሳይመረትባቸው የቀሩ ቦታዎችን በተመለከተ የዚህ ጥናት ቡድን በተደጋጋሚ መረጃ ደርሶታል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም በተባይና በፈንገስ በመጠቃታቸው ሲሆን ሌሎቹም ቦታዎች በሰብል አመራረጥ ላይ በተፈጸመ ስህተትና በባለሃብቶች ልምድ ማነስ የተከሰቱ ናቸው፡፡

**ሣጥን ሠ፡ የትግራይ የመሬት ኢንቨስትመንት**

ስለ መሬት ኢንቨስትመንት ሲወራ ከሚዘነጉ ጉዳዮች መካከል ዋንኛው የትግራይ ተወላጆች እያገኙ ያሉት የተለየ ጥቅም ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በሥልጣን ላይ ያለው ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ከአጀማመሩ ከትግራይ ልጆች የተወጣጣ ነበር፡፡ ደርግ በ1983 ሲወድቅ ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ (ህወሃት) ሥልጣኑን የተረከበ

ሲሆን ይህንንም ያደረገው ኢህአዴግን በመሞሻሂት ነበር፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለህወሃት ካድሬዎች እና ሌሎች የትግሬ ምርጦች የተለየ ጥቅም እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ሁሉ ሲመቻቹ ቆይተዋል፡፡

ከሌሎች ይልቅ የትግራይ ሰዎች ኢንቨስትመንትን በተመለከተ የተለየ ጥቅም እንዲሁም መሬትን በነጻ፣ ብድርን በተመለከተ ደግሞ ለየት ያለ ጥቅም ያገኛሉ ተብሎ በብዙዎች ዘንድ በስፋት ይታመናል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን ከነበኛቸው የትግራይ ተወላጅ ከሆኑ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች መካከል ከአንዱ በስተቀር አብዛኛዎቹ ባለሃብቶች የትግራይ ተወላጆች በመሆናቸው ብቻ መሬት ለሚከብም ሆነ ብድር ለማገኘት እንዴት ቀላል እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ በጋምቤላ ክልል ባለሥልጣን የሆኑ ግለሰብ እንደተናገሩት ደግሞ በጋምቤላ ክልል ወስጥ ኢንቨስት ካደረጉ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች መካከል 75 በመቶው የትግራይ ተወላጆች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ሁሉም ማለት ባይቻልም እነዚህ አብዛኛዎቹ የትግራይ ባለሃብቶች የተወሰነ የእርሻ ልምድ ወይም ከናካቴው ምንም ዓይነት ልምድ የሌላቸው ናቸው፡ በርካታዎቹ በመሬት ጥርጊያ (የጫካ ምንጣሮና የማሰሉትን) እና በከሰል ምርት ላይ የተሰማሩ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ምርት ወደማምረቱ ዘልቀው ገብተወብታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የኢህአዴግን ድጋፍ በየገጠሩ ለማስፋፋትና የየክልሉን ማስተዳድር ሥልጣን በአብላጫ ለመቆጣጠር እንዲያመች በቆላማ የአገሪቱ ቦታዎች ከማኘት የአገሬው ነዋሪዎች ቁጥር እንዲበልጥ ሆን ተብሎ በእነዚህ ቦታዎች ትግሬዎች እየሰፈሩ ናቸው የሚል አማካከት አለ፡፡ ይህ የጥናት ቡድን በነበኛቸው ቆላማ የክልል ማስተዳድሮች ወስጥ አብዛኛውን ሥልጣን ትግሬዎች ተቆጣጥረውት እንደሚገኙ ተሜልክቷል፡፡ በነዚሁ ክልሎች የአብዛኛዎቹ የንግድ ተቋማት ባለቤቶች ትግሬዎች ሲሆኑ (ሌሎች ደገኞች የተወነሰ ቁጥር ቢኖራቸውም) ለአገር ወስጥ የግብርና ኢንቨስትመንትን የተሰጡት የመሬት ይዞታዎች ሁሉም ማለት ይቻላል በትግሬዎች ቁጥጥር ሥር ይገኛል፡፡

የሊዝ ስምምነት ከሚጸሙ በፊት በሚያረው ድርድር መሬት ለሚከብ ማመልከቻ ያስገቡ ባለሃብቶች ግብርናን በተመለከተ ያላቸው ልምድ ወይም ባስገቡት ማመልከቻ መሠረት ሊያከናወኑ ስላሰቡት የልማት ተግባር ያላቸው ልምድ ምን ያህል እንደሆነ ምርመራ አይካሄደም፡፡ በርካታ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች ትርፍ አምጪ ሰብሎችን ከማምረት ይልቅ በአካባቢው የተለመዱትን የእህል ዓይነቶችን እንደ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ሰሊጥ፣ ለወዝ፣ ወዘተ ያሉትን ሲያመርቱ ነው

የሚስተዋሉት፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ስለ ሰብሎች ያላቸው እወቀት ወሱን በመሆኑ፣ የሚያመርቱት በትናንሽ እርሻዎች ላይ በመሆኑ የወጪ ገበያ አቅርቦትን ማሻፈን አለመቻላቸው፣ ትርፍ አምጪ ሰብሎችን ለማምረት ከፍተኛ የካፒታል ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ በመሆኑ፣ ከብዙዎቹ ምክንያቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የአብዛኛዎቹ እርሻዎች ግብዓቶች እርሻው ከሚካሄድበት አካባቢ የሚገኝ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የአብዛኛዎቹ መሬቶች ምንጣሮ የሚካሄደው በመጥረቢያና በቆንጨራ መሆኑ አብሮ የሚጠቀስ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አብዛኛዎቹ ባለሃብቶች ፈጣን ገቢ ለማግኘት[80] መሬቱን ለከሰል ሲሉ ካጸዱት በኋላ ቦታውን ያለሥራ መተዋቸው እንዲሁም የመሬት ዋጋ ሲጨምር ቦታውን ለሌላ ባለሃብት የማዘወራቸው ጉዳይ በብዙዎች ዘንድ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን በአገር ወስጥ ባለሃብቶች

የተወሰዱ በርካታ ቦታዎች ለሕገወጥ ነገር ግን በጣም ትርፋማ ለሆነ የከሰል ምርት መዋሉን በበርካታ ቦታዎች ተሜልክቷል፡፡

በእነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች በጾታቸው ወንዶች ሲሆኑ እጅግ በርካታዎቹ በእርሻዎቻቸው ላይ አይኖሩም፡፡ እንዲያውም በጣም ብዙዎቹ የአዲስአበባ ነዋሪዎች ሲሆኑ እርሻዎቻቸውን አስተዳዳሪዎች ወይም ቃልአቀባዮቻቸው እንደሚሉት ከሆነ ባለሃብቶቹ እርሻዎቻቸውን ጎብኝተው አያወቁም ማለት ይቻላል፡፡

## የአገሬው ነዋሪ ተሳትፎ

የመሬት ኢንቨስትመንት በሚካሄድባቸወቅ ቦታዎች የአገሬው ነዋሪ ተሳትፎ እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ በጋምቤላ ክልል ሦስት የአገሬው ባለሃብቶች ሲኖሩ የአንደኛው መሬት ባካባቢው ለሚካሄደው የመንደር ምስረታ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ተወርሶባቸዋል፡፡ ባለሃብቱ በሊዙ ላይ በሰፈረው ስምምነት መሠረት ተገዢ መሆናቸውን ቢገልጹም አዳዲሶቹ ሰፋሪዎች አንድ ቀን በድንገት መሬቱን አጽድተው ለራሳቸው ለማድረግ የመጡ ቀን ነበር መሬቱ ከእርሳቸው የተወሰደ መሆኑን ያስተዋሉት፡፡ ይህ ሲሆን የባለሃብቱ ሠራተኞች አዲሶቹን ሰፋሪዎች ከቦታው በሚያባርሯቸው ጊዜ ባለሃብቱ በክልሉ ማስተዳድር በቁጥጥር ሥር ከወደቁ በኋላ ጉዳዩን አስሜልክቶ አቤቱታ ሲያቀርቡ "አሁን ላለው የፖለቲካ ሥርዓት አባል እስካልሆንክ ድረስ ያለህ በሙሉ ይወሰዳል" የሚል ምላሽ ነበር የተሰጣቸው፡ በአሁኑ

ወቅት ሜቱ የማደር ምሥሂታ እንዲካሄድበት እየተደረገ ይገኛል (ስለ ማደር ምሥሂታ ፕሮግራም ሣጥን ቸ ተጨዌ ማዘራሪያ ይሰጧል)፡፡ ባለሃብቱ በምትኩ ሌላ ቦታ እንደሚሰጣቸው ተስፋ ተገብቶላቸው የነበረ ቢሆንም እስካሁን የተሰጣቸው ምንም ዓይነት ካሣም ሆነ ቦታ የለም፤ ያወጡት የካፒታል ወጪም ከስሮ ቀርቷል[81]፡፡ በቤንሻንጉል ክልል ከአገሬው ነዋሪዎች ምንም ባለሃብት የለም፡[82]

## ዳያስፖራ (በወጪ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ)

ሌላ በጣም ትንሽ ትኩረት የተሰጠው የባለሃብቶች ቡድን በወጪ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ በወጪ ለሚኖሩና በርካታ ለሚሆኑ ባለጠጎች ወደ ኢትዮጵያ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ከፍተኛ ማበረታታት እየተካሄደ ይገኛል፡፡[83] ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ማስተዳድር የኢንቨስትመንት ቢሮ የተገኘው ሚጃ እንደሚጠቁመው ከሆነ በእርሻ ከተሰማሩት 227 ባለሃብቶች ዘጠኙ (4በመቶው) የወጪ ባለሃብቶች ሲሆኑ አርባው (18በመቶው) ግን ከዳያስፖራ እንዲሁም ቀሪው 78በመቶ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች ናቸው ይላል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን ተዘዋወሮ የጎበኛቸው የዳያስፖራ የሜት ይዞታዎች ከ500 እስከ 2000 ሔክታር ሲሆኑ ይህም በአገር ወስጥ ባለሃብቶች ከተያዘው ሜት በአማካይ የሚበልጥ ቢሆንም በወጪ ባለሃብቶች ከተያዘው ግን በእጅጉ ያነሰ ነው፡፡

የሜት ኢንቨስትመንት የማመልከቻ ሂደትን በተመለከተ ዳያስፖራዎች እንደወጪ ባለሃብቶች የሚስተናገዱ ሲሆን በተለይ በኦሮሚያ አንድ ዳያስፖራ ተስፋ የገባወን ያህል ካፒታል እንዳለው የሚያሳይ የባንክ ሰነድ[84] ማቅረብ አያስፈልገውም፡፡ ይህ የጥናት ቡድን በጋምቤላ ክልል ያነጋገረው አንድ የዳያስፖራ ባለሃብት ያስገባው ማመልከቻ አስፈላጊወን ካፒታል የሚያሳይ የባንክ ሰነድ አባሪ አድርጎ ባለማቅረቡ ምክንያት ማመልከቻው ወድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡ በእርሻ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ያሉት ምክንያቶች እንዳሉ ሆነው በትወልድ አገራቸው ኢንቨስት ማድረግ አንዱ አበረታች ምክንያት እንደሆነ ብዙዎች በወጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያወያን ይናገራሉ፡፡ እንዲሁም በሚኖሩበት አገርና ቤተሰቦቻቸው ባሉበት አገር (ኢትዮጵያ) መካከል ጊዜያቸወን ከፋፍለው ማጠቀም መቻላቸወንም አብረው እንደምክንያት ይጠቅሳሉ፡፡ ሌላው የዳያስፖራ ባለሃብቶች ከአገር ወስጥ ባለሃብቶች ይልቅ የተሻለ የካፒታል አቅም እንዳላቸው ተጠቃሽ ነው፡[85]

## የሜት ወሎቹ ዓላማ

ይህ የጥናት ቡድን የሚመሬቸው አብዛኛዎቹ የሜት ወሎች የታቀዱት ለምግብ ምርት ነው፡፡ የዚያኑ ያህል ደግሞ ከበርካታ የወጪ ባለሃብቶች ጋር ማጠነሰፋፊ በሆኑ የሜት ይዞታዎች ላይ ወል ሲፈጸም ይስተዋላል፤ በተለይም ከሕንድ ባለሃብቶች ጋር ለነዳጅ የሚውል ሰብል ለማምረት ስምምነቶች እየተደረጉ ናቸው፡(ጃትሮፓና ፖንጋሚያ ፒናታ የተባሉትን ለባዮዲዝል ምርት የሚውሉ ሰብሎችን ጨምሮ)[86] በአጠቃላይ ሲታይ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች የምግብ ሰብሎችን በማምረት ላይ የተሰማሩ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

በወሎቹ ወስጥ በተለያዩ አንቀጾች ላይ የባለሃብቱ ድርጅት በማመልከቻው ላይ በግልጽ እንዳስቀመጠው የሚከበወን ሜት ለታቀደው ዓላማ ብቻ እንዲያወል ተጽፎ ይነበባል፡፡ ሆኖም የቤንሻንጉል ክልላዊ ማስተዳደር ኢንቨስትመንት ቢሮ ቃልአቀባይ ለዚህ የጥናት ቡድን እንደተናገሩት ከሆነ ምንም እንኳን በየሩብ ዓመቱ ክልሉ በሜቱ ላይ ቁጥጥር እንዲያደርግ የሰፈረ ቢሆንም በበጀት ዕጥረት ምክንያት ይህንን ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡ በጋምቤላ ክልል የሚደረጉት ወሎች ደግሞ የልማት ሥራው ወሉ ከተፈረማበት ቀን አንስቶ ጀምሮ በአንድ ዓመት ወስጥ መጀመር እንዳለበት ከማናገር አልፎ በዓመቱ የተወሰነ ሥራ መካሄድ እንዳለበት አለበለዚያ ሜቱ እንደሚወረስ ያስረዳል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን ከጎበኛቸው ቦታዎች የአንዱ የአገር ወስጥ ባለሃብት ቦታ ብቻ በመንግሥት ባለሥልጣናት ተመርምሯል፡፡

## የምግብ ምርትን በተመለከተ ምን ተከሰተ?

ከዚህ በፊት በ1.7 ክፍል ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት የምግብ ምርትን ለአገር ወስጥ ፍጆታነት ሳይሆን ለወጪ ንግድ ይወል ዘንድ እንደሚያበረታታ ተመልክተን ነበር፡፡ በጋምቤላ ክልል ከተሰማሩት ባለሃብቶች መካከል ዋንኛው ሳወዲ ስታር ኩባንያ ለዚህ የጥናት ቡድን እንደገለጸው ከሆነ ቅድሚያ ሰጥተው የሩዝ ምርትን ወደ ወጪ ለመላክ እንደሚያመርቱና ለወጪ ንግድ ሊበቃ የማይችለወን ለአገር ወስጥ ገበያ እንደሚሸጡት ተናግረዋል፡፡ ሩዙን ለገበያ ከማቅረባቸው በፊት ደብረዘይት ወደሚገኘው የማጣሪያ ቦታ ለማስዋብ እንደሚልኩት ተናግረዋል፡፡

ሌሎች ባለሃብቶች ግን ገበያ በሚገኝበት ቦታ ሁሉ እንደሚሸጡ ሲናገሩ በተለይ ግን ከሚጓጓዣ ወጪ ዝቅተኛነትና የሎጂስቲክስ ቅለት አኳያ በአገር ወስጥ ገበያ ለማሸጥ እንደሚሞርጡ ተናግረዋል፡፡ በተመሳሳይ ሜሌኩ በርካታ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች ለአገር ወስጥ ገበያ የሚውል ምርት የሚያመርቱ ሲሆን የሙረተልማትና የማከፋፈያ ዘደዎች የተስፋፉ ቢሆን ኖሮ ምርታቸወን ለወጪ ገበያ ለማቅረብ እንደሚሞርጡ ገልጸዋል፡፡

የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ቃልአቀባይ (AISD) እንደሚሉት ከሆነ ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት እሴት (ዋጋ) የተጨሚባቸው የእርሻ ሂደቶች እየተከናወኑ ባይሆንም ማስሪያቤታቸው ግን ይህንን እሴት እየጨሙ የሚያመርቱ ኢንዳስትሪዎችን እንደሚደግፍ ተናግረዋል (ከኢንቨስትመንት አዋጁ ጋር እንዴት ሊጋጭ እንደሚችል መ/ቤቱም እንዴት ሊደግፍ እንደሚችል ግልጽ የሆነ ነገር የለም) በዳይሬክቶሬቱ መ/ቤት ወስጥ ያሉ ምንጮች ለዚህ የጥናት ቡድን እንደገለጹት ከሆነ መ/ቤታቸው ባለሃብቶች የገንዘብ ሰብሎችን እንዲያመርቱ እንደሚያደፋፍር ሆኖም ግን የሜጨሻው ወሳኔ ግን የባለሃብቱ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሃሳብ ይህ የጥናት ቡድን በተዘዋወረባቸው በሁሉም የክልል ማስተዳደሮች ሲደጋገም አስተውሏል፡፡

## 2.5 መሬት ለኢንቨስትመንት እንዴት እንደሚሞሚጥ?

### የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ

በተለያዩ ክልሎች (በትግራይ፣ በኦሮሚያ፣ በአሜራና በደቡብ ሕዝብ) የወጡት የመሬት አጠቃቀም አዋጆች ስለመሬት አጠቃቀም ዕቅድ አጠቃላይ ግንዛቤ ይሰጣሉ፡፡[87] የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዋናው ዓላማ በየቦታው በስፋት የሚገኘወን መሬት በተገቢው መንገድ ለጥቅም እንዲወል፤ የተለያዩ የመሬት አጠቃቀም ስልቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ፤ እንዲሁም በመሬቱ ላይ ጉዳየኛ (stakeholder) የሆኑቱ ሁሉ ፍላጎታቸው በተመጣጣኝ ሜሌኩ እንዲስተናገድ ለሚድረግ ነው፡፡ ሆኖም መሬት ከፖለቲካ ጋር በተጣሚባት እንደ ኢትዮጵያ ባለ አገር እንዲህ ዓይነቱን ሂደት መተግበር ቀላል አይደለም፡፡ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በጋምቤላ ክልል እየተካሄደ ሲሆን በከፊል ኦሮሚያ ደግሞ እየተጠናቀቀ ይገኛል፡፡ በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉልና ኦሮሚያ ክልላዊ ማስተደዳደሮች የሚገኙ ባለሥልጣናት የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ ተግባራዊነቱ ሥራቸወን እንደሚያቀላጥፍላቸው፣ ግጭትን እንደሚያቃልል፣ የተቀናጀ አሠራርን እንደሚያበረታታ እንዲሁም የመሬት አጠቃቀምን በብቃት ለመተግበር ይረዳል በሚለት ይናገራሉ፡፡

ትክክለኛ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በሌለበት ቦታ ለንግድ የሚሥጠው የእርሻ መሬት የሚወሰነው በጊዜያዊነት ሲሆን በሌሎች ቦታዎች የሚገኙትን ሜሬቶች በተመጣጠነ ሜሌኩ የማጠቀምን ሁኔታ ተግባራዊ አያድርግም፡፡ (ለምሳሌ፣ ለወጪ ንግድ ከሚውለው በተጨማሪ ለአገር ወስጥ አጠቃቀም እንዲወል የሚያስፈልገወን ሜሬት ሚጋገጥን በተሜለከተ) ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ የፖሊሲ ግልጽነት ወይም ተገቢው ቴክኒካዊ ብቃት ሳይኖር ሜሬትን ለተለያዩ ተጠቃሚዎች ማሻንሸን በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ በተለያዩ የመንግሥት እርከኖች በሥራ ላይ የዋለው ማስፈርት ወጥነት ስለሌለው ለወል የተዘጋጀው የመሬት ይዞታ ለመወሰን የሚደረገው ሂደት የተለያየ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ለንግድ ተኮር እርሻ እንዲወል የሚሰጠው መሬት (ትናንሽ የመሬት ይዞታዎች) እምብዛም ተጠያቂነትም ሆነ የቴክኒክ ብቃት በሌለበት በወረዳ ወይም በቀበሌ (መንደር) ደረጃ ነው፡፡[88] ከመሬት ኪራይ የሚገኘው ገበም በቀጥታ የሜሄደው ወደ ወረዳው አስተዳደር ነው፡፡ በወረዳ ደረጃ ለሚገኙ የመንግሥት አካላት የገቢው ማጠን እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ለሚሰና በር እንደሚከፍት ያላቸወን ፍርሃት አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን የገለጹ ሲሆን በተለይም ደግሞ ይህ የኪራይ ገቢ በምንም ዓይነት ሜሌኩ ግልጽ እና ዝርዝር ባለው ሁኔታ የሚከናወን ባለመሆኑና ማንም ተጠያቂ ስለማይሆን ገቢው ወደ ጠቅላይ ግምጃ ቤት እንዲላክ ሃሳብ ይሠጣሉ፡፡ ምንም እንኳን ተመኑ የተለያየ ቢሆንም ከ10ሺህ ሔክታር የመሬት ሊዝ ከ17500 እስከ 42700 ዶላር ወደ ወረዳው ካዝና በየዓመቱ የሚገባ ሲሆን ይህም ከ120ሺህ እስከ 260ሺህ ዶላር ዓመታዊ በጀት (በ1994 1.1 ሚሊዮን ብር እስከ 2.4 ሚሊዮን ብር ነበር)[89] ላለው የወረዳ አስተዳደር ከፍተኛ የገንዘብ ማጠን ነው፡፡

ለልማት የሚሰጠው መሬት ለእርሻ ተስማሚ ስለማሆኑ የሚያጠና የባለሙያ ቡድን በማንግሥት ደረጃ ስለሌለ ባለሃብቶች በራሳቸው ባለሙያ አስጠንተው በሚያቀርቡት ሚጀና ላይ ወሳኔያቸውን እንደሚሚኮዝ የማንግሥት ባለሥልጣናት ይናገራሉ። እነዚሁ ባለሥልጣናት ተመጣጣኝ የመሬት አጠቃቀምን ተግባራዊ የሚያደርጉበት ማንገድ እንደሌለ ከማናገር በተጨማሪ የመሬት አጠቃቀሙ ዕቅድ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ሥራቸውን እንደሚያቃልልላቸው ተስፋ ያደርጋሉ።[90]

## የመሬት ሚጣ

በፌደራል ደረጃ የመሬት ሚጣ የሚከሄደው የአፈሩ ተስማሚነት፣ የወሃ ማግኘትና በአካባቢው ሰፋሪ አለሞኖር መሠረት በሚድረግ ነው። የመሬት ሚጣው ሂደት የሚጀሚረው የክልሉ ማስተዳድር በእጩነት በተሚጠው የመሬት ይዞታ ላይ ተገቢውን የማነበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምርመራ ካደረጉ በኋላ ሲሆን በዚህም ምርመራ መሠረት የክልል ማስተዳድሩና የፌደራሉ ማንግሥት የመሬት ይዞታው ለኢንቨስትመንት ያለውን ተገቢነት ይሚምራሉ። አንድ የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) ባለሥልጣን እንደተናገሩት በርካታ የመሬት ይዞታዎች በዚህ የምርመራ ደረጃ ላይ ወድቅ ይደረጋሉ ምክንያቱም "መሬት የፖለቲካ መሣሪያ" ነወና። "ምክንያቱም የመሬቱ ይዞታ ግጭት የሚያስነሳ ከሆነ ለኢንቨስትመንት ተስማሚ ስላልሆነ ይኸው ለባለሃብቱ ይነገረዋል" ብለዋል። ሆኖም መሬቱ ተስማሚ ከሆነ ወደ ፌደራሉ የመሬት ባንክ ይተላለፍና ለወጪ ባለሃብቶች ዝግጁ ይሆናል።

ነገር ግን "በአካባቢው ሰፋሪ አለሞኖር" የሚለው አባባል አደናጋሪ ነው። ለምሳሌ፣ በጋምቤላ ክልል በፌደራሉ የመሬት ባንክ ወስጥ የተካተቱት የመሬት ይዞታዎች የተበታተኑና አነስተኛ ቁጥር ካላቸው ቤተሰብ ጀምሮ እስከ 1ሺህ ሰዎች የሚኖሩባቸው የኑዌርና አኙዋክ መንደሮች ይገኙባቸዋል። እነዚህ ትልልቅ የመሬት ይዞታዎች የተለያዩ ሰብሎችን ለማዝበቀል ምቹ መሆናቸው እየተገለጸ ለባለሃብቶች እየተስተዋወቁ ይገኛል (በጋምቤላ ከሚገኘው አጠቃላይ መሬት 32በመቶ ወይም 1.7ሚሊዮን ሔክታር የሚሆነው በፌደራሉ የመሬት ባንክ ወስጥ ለኢንቨስትመንት ተመዝግቦ ይገኛል)።

**"በጋምቤላ የሚገኘው መሬት በሙሉ በጥቅም ላይ ወሏል። እያንዳንዱ ማኅበረሰብ የራሱን ግዛት፣ የራሱ ወንዞች እንዲሁም የእርሻ መሬቶች ይንከባከባል። በጋምቤላ በጥቅም ላይ ያልዋለ ወይም የባከነ መሬት አለ የሚለው የማንግሥትና የባለሃብቶች በሬ ወለደ ፕሮፓጋንዳ ነው።"**

ኒይካው አቻላ፤ ከአኒያ የማዳን ድርጅት (Anyaa Survival Organization)[91]

በክልል ማስተዳድር ደረጃም የመሬት ሚጣው የአሠራር ሂደት ተማሳሳይ ነው። በቤንሻንጉል ክልል የመሬት ይዞታን በሊዝ የመፍቀድ ኃላፊነት ያላቸው የአንድ ወረዳ ባለሥልጣን እንደተናገሩት አፈሩ ተስማሚ ከሆነ፣ ወሃ በአካባቢው ከተገኘ፣ በአካባቢው ሰፋሪ ከሌለና ቦታው ጥቅጥቅ ባለ ደን የተሸፈነ ካልሆነ (ጥቅጥቅ ያለ ደን ያለበት መሬት ማጠነሰፊ ምንጣሮ የሚያስፈልገው በማሆኑ) መሬቱ ለኢንቨስትመንት ይሠጣል።

የጋምቤላ የኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊዎች የመሬት ይዞታው ለቱሪስት ማስህብ የሚሆን፣ ለምንም ዓይነት ጥቅም ይሁን ግን የተከለለ፣ የተጠበቀ የደን መሬት ከሆነ እንዲሁም የእርሻ ሥራ እየተካሄደበት ከሆነ በሊዝ እንደማይሰጥ ገልጸዋል። "የቱሪስት ማስህብ" እና "የተጠበቀ የደን መሬት" የተባሉት ቦታዎች የት እንደሆኑ ሲጠየቁም ባለሥልጣኖቹ እርስበርሳቸው በስፋት ከተወያዩ በኋላ በክልሉ እንደዚህ ዓይነት ቦታዎች እንደሌሉ አምነዋል።[92] የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ እየተባለ በስፋት የሚታወቀው ቦታ (ይፋ ባይሆንም) በሳውዲ ስታር ኩባንያ በሰፊው ተማንጥሯል። (ለዝርዝሩ ሣጥን ፪ ይመልከቱ)

የመሬት ይዞታን ለባለሃብቶች ከማስጠት አኳያ ለዘላኖች፣ አሰባጥሮ ለሚዜስ፣ ለግጦሽ ወይም ለጋራ ጥቅም ስለሚውል የመሬት ይዞታ ይህ

የጥናት ቡድን ባካሄደው በየትኛውም ቃለምልልስ ወቅት ሲጠቀስ አልተስተዋለም፡፡ ሆኖም የጥናት ቡድኑ እነዚህ ሁኔታዎች በምን ዓይነት ሜሉኩ እንደሚሄዱ ሲጠይቅ ከክልል ማስተዳድርም ሆነ ከፌደራል መንግሥት ባለሥልጣናት የተሰጠው ሜልስ ጉዳዩ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (EIA) በሚደረግበት ጊዜ የሚታይ መሆኑን ነው፡፡ (እንደ እውነታው ከሆነ ይህ ግምገማ አይካሄድም ማለት የሚቻል ሲሆን በክፍል 3.5 ላይ ዝርዝሩ ተቀምጧል) በዚህ ጉዳይ ላይ ይህ የጥናት ቡድን ያነጋገራቸው በሁለት ክልላዊ ማስተዳድሮች ወስጥ ስለ ሜሬት ሊዝ ኃላፊ የሆኑት ባለሥልጣናት በሙሉ ይህንን የተጽዕኖ ሪፖርት ፈጽሞ ያላዩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በሊዝ ከተሰጡት ቦታዎች ሜካከል በዚህ የጥናት ቡድን የተጎበኙትና በማምረት ላይ የሚገኙት በታዎች በሙሉ በዋንኛ የወሃ ምንጭ አጠገብ የሚገኙ ሲሆን ለመንገድ ቅርብና ወሱን በሆነ የሰው ኃይል የሚከናወኑ ናቸው፡፡ (ሆኖም ግን በሁሉም ቦታዎች በጥቂቱም ቢሆን የሰው ኃይል ማስፈለጉን ልብ ይሏል) አብዛኛው የሜሬት ይዞታ በከፊል ወይም በሙሉ በደን/በጫካ የተሸፈነ በመሆኑ መመንጠር የሚያስፈልገው ነበር፡፡

## ሣጥን ፫፡ የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ

በጋምቤላ ክልል በየመንደሩ የሚገኙ ነዋሪዎች ባለሃብቶች የጋምቤላን ብሔራዊ ፓርክ እየሜጠሩ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ በፌደራል መንግሥት ደረጃ የተከለሉ ቦታዎችን የሚያስተዳድረው የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን (ኢዱልጥባ - EWCA) እንደሚለው ከሆነ የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ የተፈጠረው በ1956ዓም ሲሆን የሚያካትተውም 5,061 ካሬ ኪሎሜትር ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በይፋ የታወቀ አስተዳደር ወይም ዕቅድ ወይም የተከለለ የፓርክ ድንበር የለውም፡፡ በቅርቡ በተካሄደ ጥናት በፓርኩ ወስጥ 69 የተለያዩ አጥቢ እንስሳት ከእነርሱም ሜካከል 58ቱ ግዙፍ አጥቢዎች መሆናቸው ተደርሶበታል፡፡ ከዚህ

በተጨማሪም ፓርኩ በጣም ተፈላጊ የሆነ ረግረግ ቦታ ያለው ሲሆን በመቶዎች የሚቆጠሩ የአእዋፍ ዝርያዎች እና በኢትዮጵያ ካለው የዓሣ ዝርያ 69በመቶውን የሚወክል 92 የዓሣ ዝርያዎች ይገኙበታል፡፡

እስከ 2000ዓም ድረስ ፓርኩን የማስተዳደር ኃላፊነት የጋምቤላ ክልላዊ ማስተዳድር የነበረ ሲሆን ከዚያ በኋላ ግን የማስተዳሩን ጉዳይ የፌደራሉ መንግሥት በሚከብ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን በክልሉ የሚገኙትን ቦታዎች በሜካለልና በማየት በክልል ማስተዳደሩ የሚገኙትን የተጠበቁ ቦታዎች የወሰን ሚብ ያዘጋጃል፡፡ ይህ ሂደት እየተካሄደ ባለበት ወቅት ዋንኛ የሆነ የሜሬት ሊዝ ፊርማ ይከናወን ነበር፡፡ (ለምሳሌ በ2000ዓም አካባቢ ለካሩቱሪ ኩባንያ 300ሺህ ሄክታር ሜሬት ተሰጥቶት ነበር) የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን በፓርኩ አካባቢ 438ሺህ ሔክታር የሚሆን የሜሬት ይዞታ በሊዝ እንደተሰጠ ሲገልጽ ይህ ሁሉ የሆነው ምንም ዓይነት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሳይካሄድ ነበር፡፡

የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን የሜሬት ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ከፌደራል መንግሥት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሚያደርግ ቢሆንም "በጋምቤላ ክልል ለእርሻ ሜሬት ያለው ፍላጎት እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ" ይህንን የልማት ተግባር በአጭር ጊዜ ወስጥ ለማስቆም አስቸጋሪ እንደሆነ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ይናገራል፡፡ እንዲሁም የዚሁ መ/ቤት ቃልአቀባይ የሆኑት ሲናገሩ "ከግብርና ሚ/ር ጋር ግጭት ወስጥ መግባታችንን እንረዳለን፤ ምክንያቱም ሁለታችንም በተለያየ ዓላማ ላይ የተሰማራን በመሆናችን ነው፤ ለማንኛውም የሚሆነውን ወደፊት እናያለን" ብለዋል፡፡



የባለሥልጣኑ መ/ቤት እንደሚለው ከሆነ የጋምቤላ ክልላዊ ማስተዳድር እስከ 5ሺህ ሔክታር ሜሬት በሊዝ ማስጠት እንደሚችል ሲገልጽ በተለይ እንዲጠበቁ የተከለሉ ቦታዎችን ለኢንቨስትመንት ላለማስጠት ማስተዳደሩ ወሳኔ ሜድረጉን ይገልጻል፡፡

በማከልም የባለሥልጣኑ መ/ቤት የወቅቱ ሁኔታ ወሳኝ በመሆኑ በእጩነት የተያዙት የሜሬት ይዞታዎች ተመንጥረው ለባለሃብቶች ከማስጠታቸው በፊት አሁን የጀመረወን የጥበቃ ሂደት አጠናክቆ በሥራ ላይ ለማዋል ተስፋ ያደርጋል፡፡ ይህንን የሥራ አፈጻጸም ፕላን በሰኔ 2003 እወን ሆኖ በተግባር ላይ ይወላል በማለት በጣም ተስፈኛ የሆነ ዕቅድ አወጥቷል፡፡ ይህ የሥራ አፈጻጸም ዕቅድ የፖሊሲ መሣሪያዎችንና ደንቦችን እንዲሁም ከተከለሉት ቦታዎች ወስጥ ለልማት ተቀባይነት ያላቸው ቦታዎችን የሚዘረዝር ይሆናል፡፡ምንም እንኳን የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ ድንበር የተከለለ ባይሆንም የአካባቢው ነዋሪ የፓርኩ ክልል ነው ብሎ ሁልጊዜ የሚያምንበት የሜሬት ይዞታ እንደ ካሩቱሪና ሳዉዲ ስታር በማሰሉት ማጠነሰፊ የእርሻና ንግድ ባለሃብቶች ተመንጥሯል፡፡ እጅግ በርካታ ዓሣዎች የሚኙበት የወሃ ስፍራ እና በርካታ የአእዋፍ ዝርያ የሚኙበት ደን የካሩቱሪ ኩባንያ ሩዝ እንዲያበቅልበት ተፈቅዶለታል፡፡ በአቅራቢው የሚኝ ጥቅጥቅ ያለ የደን ቦታም ሙሉ በሙሉ ተመንጥሯል፡፡ ምንም እንኳን የዱር እንስሳት ልማትና

ጥበቃ ባለስልጣን ጥረት እያደረገ ቢገኝም ይህንን ፓርክ የማዳኑ ዕድል ያከተመለት ይመስላል፡፡

## 2.6 የሜሬት ኢንቨስትመንት ሂደት

**"የፌደራል መንግሥት ኃላፊነት እንደተሰጠን ሁሉ ማጠነሰፊ ትርፍ ሊያስገኙ የሚቹሉ ጥቅሞችን በምንማከትበት ጊዜ ጥፋት ላለማስራት ፈጠን ያለ እርምጃ መወሰድ ይገባናል፡፡ (ባለሃብቶች) ግንኙነት የሚያደርጉት ከአንድ ድርጅት ጋር እንዲሆን እንጥራለን፤ እንዲሁም የሚደረገው ሂደት ግልጽ እንዲሆን . . . ይህንንም ዓይናችንን ከፍተን ነው የምንከታተለው፡፡"**

የአፌደሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ማለስ ዜናዊ ስለ አዋጅ 29/1993 ከተናገሩት[93]

በኢትዮጵያ የሜሬት ይዞታ ኢንቨስትመንት ቀስ በቀስ እያደገ ያለ ሲሆን የተለያዩ የመንግሥት ተዋንያን የሚሳተፉበት ነው፡፡ የአፌደሪ ሕገመንግሥት የገጠር ሜሬት አስተዳደርን ሥልጣን ለክልል ማስተዳድሮች የሰጠ በመሆኑ እነዚህ ማስተዳድሮች ሰፋፊ የሜሬት ይዞታዎችን ከባለሃብቶች ጋር እየተደራደሩ ሲሰጡ ቆይተዋል፤ አሁንም እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

ሆኖም በጥር 2001 አዋጅ ቁጥር 29/1993 የአሰራሩን ሂደት ቀይሮታል፡፡ በፌደራሉ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሥር የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) ለግብርና ተግባር ታሳቢ የሚሆኑ የሜሬት ይዞታዎችን የማለየት፣ እንደዚህ ዓይነት ቦታዎችን ከየክልሉ የማሰብሰብና ለባለሃብቶች የማስተላለፍ ተግባራትን እንዲያከናወን ተቋቁሟል፡፡ እንዲሁም የባለሃብቶችን ተግባራት በመቆጣጠር ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡[94] በአሁኑ ጊዜ ከ5ሺህ ሔክታር በላይ የወጪ የእርሻ ሜሬት ኢንቨስትመንት በዳይሬክቶሬቱ ኃላፊነት ሥር የወደቀ ቢሆንም ከ5ሺህ ሔክታር በታች ያለው ግን እስካሁን በክልል ማስተዳድሮች ኃላፊነት የሚከናወን ነው፡፡

በየትኛውም ደረጃ ማለትም በፌደራል መንግሥት ይሁን በክልል ይህ የሜሬት ይዞታ ጉዳይ ይከናወን ዘንድ የሜሬት ኢንቨስትመንት ሂደት ሦስት ክፍሎች አሉት፡ (1) የኢንቨስትመንት ሰርቲፊኬት፤ (2) የሜሬት አጠቃቀም ስምምነት እና (3) የሜሬት ርክክብ

### የኢንቨስትመንት ሰርቲፊኬት

የኢንቨስትመንት ሰርቲፊኬት ለማግኘት የሚደረገው ተግባር እንዲሁም ሂደቱ ቀላል ነው፡፡ ባለሃብቱ ሊያከናወን ስላሰበው ፕሮጀክት፣ ቦታ፣ የካፒታል ኢንቨስትመንት ማጠን፣ የካፒታል ምንጭ፣ የሜሬት ይዞታው ማስፈርት፣ የሚቀጠሩት ቋሚ/ጊዜያዊ ሠራተኞች ብዛት፣ ዓመታዊ የምርት ግምት፣ የምርቱ ገበያ (ለአገር ወስጥ ፍጆታ ወይስ ለወጪ)፣ የጥሬ ዕቃ ማስፈርት፣ የማልገያ ወጪ ማስፈርት እና ፕሮጀክቱ ተግባራዊ የሚሆንበትን ወቅት ያካተተ አንዲት ማጠነኛ ቅጽ በመሙላት ማመልከቻወን ያቀርባል፡፡[95] ቀጥሎም 600ብር ከከፈለ በኋላ በአራት ሰዓታት ወስጥ የኢንቨስትመንት ሰርቲፊኬት እንደሚቀበል የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ይናገራል፡፡ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ሰርቲፊኬት ከክልላዊ ማስተዳድሮች ማግኘት ይችላሉ፡፡

### የሜሬት አጠቃቀም ስምምነት

አግባብ ባለው የመንግሥት አካልና በባለሃብቱ መካከል የሚፈጸመው የሜሬት አጠቃቀም ስምምነት የሊዙን አጠቃቀም ጠቅላላ ሃሳብ እንዲሁም የእያንዳንዱን ወገን ኃላፊነት ይዘረዝራል፡፡ ከ5ሺህ ሔክታር በላይ

በሊዝ ለሚወስዱ የወጪ ባለሃብቶች ስምምነቱ ከእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) ጋር በሚደራደር የሚካሄድ ሲሆን ይህ ካልሆነ ግን አግባብ ካለው የክልል ማስተዳድር ቢሮ ጋር በማጋገር ይሆናል፡፡ የእነዚህ ስምምነቶች ዝርዝር በክፍል 2.7 ላይ ተብራርቷል፡፡

### የሜሬት ርክክብ

እንደ ሊዙ ስምምነት ድርድር በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ የሜሬት ርክክቡ ሂደትም እንዲሁ ይለያያል፡፡ በፌደራል ደረጃ በግምት 1.7ሚሊዮን ሔክታር የሚሆን ሜሬት በፌደራሉ የሜሬት ባንክ ወስጥ ተቀምጦ ይገኛል፡፡ የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) ዳይሬክተር እነዚህ የሜሬት ይዞታዎች "በጣም አገሪቷ" እንደሚገኙ ቢገልጹም በአፌደሬ[96] መንግሥት በስፋት ለሽያጭ እየተዋወቁ የሚገኙት ይዞታዎች በአብዛኛው በቆላማ የአገሪቷ ክፍሎች የሚገኙ ናቸው፡፡

በክልል ደረጃ ሜሬት የሚሚጠው በወረዳ ሲሆን አንዳንድ ጊዜም በክልሉ ማስተዳድር ድጋፍና ተጽዕኖ ሊከናወን ይችላል፡፡ የሜሬትን ርክክብ ሂደትን በተማለከተ የተለያዩ ባለሃብቶች በየክልሉ የተለያየ ልምድ አላቸው፤ የአሠራር ሂደቱም በየክልሉ በስፋት የተለያየ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከባለሃብቱ የሚፈለገው ሚጃ የቦታው ፕላን፣ የሜሬት ይዞታው ስፋት፣ ቦታ እና የማልገያ ወጪ ተፈላጊ ማስፈርቶች ናቸው፡፡[97] በአንዳንድ ቦታዎች ባለሃብቶች የሚፈልጉትን ቦታ አስቀድመው ከሚጡ በኋላ የወረዳ ኃላፊዎችን ጠጋ በማለት ሊዞን እንዲያጸድቁላቸው ይጠይቃሉ፡፡ በሌላ ሁኔታ ግን ባለሃብቱ ባቀረበው የማጠን፣ የቦታ እና የዓይነት ማስፈርት መሠረት ወረዳው የሜሬት ይዞታ ያፈላልጋል፡፡

አንድ የአገር ወስጥ ባለሃብት ለዚህ የጥናት ቡድን እንደተናገሩት የፌደራሉን መንግሥት ጠጋ ብለው በቤንሻንጉል የሜሬት ይዞታ እንደሚፈልጉ ሲጠይቁ ባለሃብቱ በመንግሥት ወደ ቦታው ተወስደው የተለያዩ የሜሬት ይዞታዎችን እየተዘዋወሩ እንዲማለከቱ ሚደረጋቸውን አስረድተዋል፡፡ ሌላ የአገር ወስጥ ባለሃብት ደግሞ በማሚልከቻቸው ከጠየቁት የሜሬት ማጠን ያነሰና ከዚህ በፊት ታይቶ የማያወቅ እንዲሁም ሊያሚርቱ ላቀዱት ምንም የሚይጠቅም የሜሬት ይዞታ እንደተሰጣቸው ይናገራሉ፡፡ በርካታ የወረዳ ኃላፊዎች ለዚህ የጥናት ቡድን ሲናገሩ የሜሬት ይዞታዎችን እንዲያስተላልፉ ከክልል ማስተዳድር የግዴታ ተጽዕኖ እንደሚደረግባቸው አስረድተዋል፡፡ እነዚህ የሜሬት ርክክብ ሂደቶች የጊዜ ገደብ ከጥቂት ቀናት እስከ በርካታ ወራቶች ይፈጃሉ፡፡

ሌላው በክልል ደረጃ እያንዳንዱ በማስተዳድሩ የኃላፊነት ዕርከን የሚገኝ ማምሪያ ሁሉ በኢንቨስትመንቱ ሂደት ወስጥ የተለያየ ኃላፊነት ያለው ሲሆን እነዚህ ማምሪያዎች እርስበርስ የማጋገራቸው ጉዳይ የሚያታሰብ ነው፡፡ ለምሳሌ፤ የኢንቨስትመንት ሰርቲፊኬት የሚሰጠው አካል የሜሬት ይዞታ ሊዞን ከሚሰጠው ጋር ወይም በአካባቢው የምግብ ዋስትና ጉዳይን ከሚከታተል የመንግሥት መ/ቤት ጋር ወይም የአካባቢውን ተፈጥሮ ከሚያመጣው ድርጅት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ላይኖረው ይችላል፡፡ ስለሆነም የኢንቨስትመንት ሂደቱ አግባብ ባላቸው መ/ቤቶች ማካከል ወጥነትና ትብብር ባለው ሜልኩ የሚካሄድ ባለማሆኑ ለአሠራር ጉድለትና ለሚስና የተጋለጠ ነው፡፡

## 2.7 የስምምነቱ ይዘት

### የኪራይ ተመን

በኢትዮጵያ ወስጥ የኪራይ ተመን በስፋት የተለያየ በማሆኑ በአሁኑ ጊዜ የተመኑን አሰራር ቀላልና ዘመናዊ ለሚድረግ በተለይም በፌደራል ደረጃ የሚፈጸመትን ከፍተኛ የወጭ ስምምነቶችን በተማለከተ ጥረት እየተካሄደ ይገኛል፡፡

**ሠንጠረዥ 8፡ የሜሬት ሊዝ ኪራይ በተወሰኑ አገሮች**
**(የአንድ ሔክታር ሜሬት ዋጋ በዶላር የዓመት ክፍያ)[98]**

**ኢትዮጵያ (ከ2001 በፊት)፡** 1ዶላር ከ25 ሳንቲም እስከ 10ዶላር

**ኢትዮጵያ 2001 ለወጪ** 26ዶላር እስከ 42ዶላር

**ኢትዮጵያ 2001 ለሌሎች፡** 1ዶላር ከ75ሳንቲም እስከ 8ዶላር

**ሱዳን፡** ከ3ዶላር እስከ 20ዶላር

**ማሊ፡** ከ6ዶላር እስከ 12ዶላር

**አፍሪካ በአማካይ፡** ከ350ዶላር እስከ 800ዶላር

**ብራዚል/አርጀንቲና፡** 5ሺህ ዶላር እስከ 6ሺህ ዶላር

**ጀርመን፡** 22ሺህ ዶላር

የቤንሻንጉል ኢንቨስትመንት ቢሮ ለዚህ የጥናት ቡድን እንደገለጸው ለአገር ወስጥ ባለሃብቶች የሚሬት ሊዝ ከራይ ተመን ከ50 እስከ 70ብር በሔክታር (ከ3 እስከ 4.25 ዶላር በሔክታር) ሲሆን የፌደራሉ ማግሥት ደግሞ በቤንሻንጉል ክልል ለሚገኝ የሜሬት ይዞታ የወጪ ባለሃብቶችን ከ432 ብር እስከ 700ብር በሔክታር (ከ26.30ዶላር እስከ 42.70ዶላር በሔክታር) እንደሚያስከፍል ተናግረዋል፡፡

በጋምቤላ ክልል የሚገኙ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች ለዚህ የጥናት ቡድን ሲናገሩ በአሁኑ ወቅት የአገር ወስጥ ባለሃብቶች የሚከፍሉት የከራይ ማጠን 1.75 ዶላር በሔክታር (30 ብር በሔክታር) ሲሆን በሚቀጥው ዓመት ይህ ዋጋ ሦስት ዕጥፍ ያድጋል ተብሎ እንደሚጠበቅ አስታውቀዋል፡፡ መጀሚሪያ ላይ ካሩቱሪ የሜሬት ይዞታወን ሲቀበል በሔክታር 1.25ዶላር (20ብር በሔክታር) የከፈለ ቢሆንም ከዚያ በኋላ ከፌደራል መንግሥት ጋር ባደረጋቸው ድርድሮች ዋጋው ወደ 6.75ዶላር በሔክታር (111 ብር በሔክታር)[99] ከፍ ብሏል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ባዘጋጀው በራሪ ጽሑፍ ላይ ዓመታዊ የሜሬት ሊዝ ዋጋ በሔክታር ከ4.30 ዶላር (70.4 ብር) እስከ 8 ዶላር (135 ብር) ሊሆን እንደሚችል ይገልጽና ዋጋው "በዞኑ ባለው የልማት ደረጃ እንዲሁም ለሁሉም የአየር ጸባይ ተስማሚ ከሆነ የጫና መንገድ ባለው ርቀት"[100] መሠረት የሚወሰን መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የወሃ ሃብት በአጠገቡ ያለ የሜሬት ይዞታ በከፍተኛ ዋጋ እንደሚተመን ይገልጻል፡፡

"በመርህ ደረጃ እኛ የከራይ ትርፍ ለማግኘት አይደለም ዋናው ዓላማችን፡፡ ይልቁንም እኛ የምንፈልገው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና የኢንቨስትመንት ተግባራትን ማየት ነው፡፡ ከዚህ የምናገኘው ጥቅም ከሜሬት ከራይ ከምናገኘው በእጅጉ የላቀ ነው፡፡"

አበራ ደሬሳ፣ የአፌደሬ የግብርና ሚኒስትር[101]

አዲስ የዋጋ ተመን እንደሚተገበር እየተነገረ የመጣው በሚያዚያ ወር 2002ዓም ነበር፡፡ በዚህም ከአዲስ አበባ 700ኪሜ ርቀት ላይ (ምናልባትም በቤንሻንጉልና ጋምቤላ ምስራቃዊ ጠረፍ) አንድ ባለሃብት 111ብር በሔክታር (7ዶላር አካባቢ) በዝናብ ለሚታረስ ሜሬት እንዲሁም 158 ብር በሔክታር በመስኖ ለሚለማ ሜሬት ይከፍላል፡፡ የሜሬቱ ይዞታ ወደ አዲስአበባ እየቀረበ ሲመጣ ዋጋወም 0.25 ዶላር በኪሎሜትር ወይም 4.05ብር በኪሜ (4.17ብር በኪሜ በመስኖ ለሚታረስ) እየጨመረ ይሄዳል፡፡ እንዲሁም የሜሬቱ ይዞታ ከአዲስ አበባ በአንድ ኪሜ እየራቀ ሲሄድ ዋጋው በ4.05ብር በኪሜ እየወረደ ይሄዳል፡፡[102] ይህ የሊዝ ዋጋ ተመን በየአስር ዓመቱ የሚሻሻል ሲሆን በአሁኑ ወቅት ያለው የሊዝ ተመን በቆላማ የአገሪቷ ክፍሎች በሥራ ላይ ከዋለው ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም በኦሮሚያ እና በሌሎች የደጋማ ክልሎች በሚገኙ የሜሬት ይዞታዎች ላይ የሊዝ ከራይ ተመኑ ሰሰራበት አይስተዋልም፡፡

ከላይ በሠንጠረዥ 8 ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው በኢትዮጵያ እየተሰራበት ያለው የዋጋ ተመን ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነጻጸር እጅግ ዝቅተኛ ቢሆንም የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) ግን የዋጋው ዝቅተኛነት ምክንያት በኢትዮጵያ ባለሃብቱ ሥራወን "ከምንም (ከባዶ) የሚጀምር" በመሆኑ ነው በማለት ይከራከራል፡፡ ይህም ማለት ባለሃብቱ ጫካ መንጥሮ ሜሬቱን ማስናዳት ሲጠበቅበት ቀጣይ ተግባራትን ዘመናዊ ባልሆነ የመሠረተልማት ላይ ጥገኛ በመሆን የሚያካሂድ በመሆኑ ነው በማለት ዳይሬክቶሬቱ ያስረዳል፡፡ ይህም ሆኖ ግን በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ያለው ጠቅላላ አማካከት የሜሬት ዋጋ ያለማቋረጥ እየጨመረ እንደሚሄድ ነው፡፡

## የክልሎች የሜሬት አጠቃቀም ስምምነት ዝርዝር

"ከመንግሥት ጋር ያለን ግንኙነት በግልጽ በንግድ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ መንግሥት ለሚከራየው ሜሬት ኪራይ ያስከፍለናል . . . በተሰጠን ሜሬት ላይ የንግድ ፍላጎታችንን ለሟካት የምናከናወነው ተግባር የራሳችን ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህም ምንም ዓይነት የአስተዳደር ተጽዕኖ፣ ግዴታ፣ ወይም ወል የለም፡፡"

በጋምቤላ ክልል የሚገኝ የወጪ ባለሃብት[103]

የሜሬት ይዞታ ስምምነቱ ዝርዝር በየክልሉ ይለያያል፡፡ ሆኖም በዚህ የጥናት ቡድን የተሚሚ አንድ ክልል እንደሚመለከተው የተፈጸሙት ስምምነቶች በሙሉ ተመሳሳይ እንደሆኑ እንዲያውም በወጪም ይሁን በአገር ውስጥ ባለሃብቶች የተፈጸሙት ስምምነቶች ተመሳሳይ እንደሆኑ ለማንዘብ ችሏል፡፡ በአምስት ገጽ በተዘረዘረው የስምምነት ወል ላይ የተጠቀሱት ማስፈርቶች ቋሚነት ወይም ዘላቂነት ያላቸው ናቸው፡-

**ተለዋዋጭ የወል ቃል**

- የጊዜ ገደብ
- የሜሬት አገልግሎት ዋጋ

**ቋሚ የወል ቃል**

- በሞት ጊዜ ወሉን የማዛወር ስርዓት፤
- የሥራ ቃልኪዳን፡- ባለሃብቱ ሥራውን በተረከበ በዓመት ውስጥ ሥራ መጀመር አለበት፤ አለበለዚያ ሜሬቱ ይነጠቃል፡፡ በቂ ምክንያት እስከሌለው ድረስ በየዓመቱ በሜሬቱ ላይ ሥራ ማከናወን አለበት፡፡
- የባለሃብቱ ኃላፊነት፡- ሜሬቱን ለማዘጋጀት፣ ቢሮና የአስተዳደር ጽ/ቤት ለመክፈት፣ የነዳጅ ሚደያ ለመክፈት፣ ለሠራተኞች የጤና የት/ቤት አገልግሎቶችን ለማስጠት፣ እንዲሁም የመሠረተልማት ተግባራትን ለማከናወን ፈቃድ አለው፡፡
- ማንኛውም ዓይነት ግጭት ሲፈጠር ባለሃብቱ ለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ያሳውቃል፡፡
- ባለሃብቱ የአካባቢን ብክለና የአፈር መሸርሸርን በአንክሮ በመከታተል እንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎችን በሚመለከትበት ጊዜ ለኢንቨስትመንት ቢሮ ማሳወቅ አለበት፡፡
- የኢንቨስትመንት ቢሮው ኃላፊነቶች፡- ለባለሃብቱ ሜሬት ማስጠት፣ የባለሃብቱን ግዴታዎች መከታተል፣ ባለሃብቱ በሰላም በተሰጠው ሜሬት ላይ ሥራውን እያከናወነ መሆኑን መከታተል፡፡
- ስምምነቱ በተከናወነ በ45 ቀናት ውስጥ የሜሬቱ ርክክብ ሚፈጸም አለበት፡፡
- በሜሬቱ ላይ የሚገኝ ማንኛውም ዓይነት ንብረት መመዝገብ አለበት፤ ማንኛውም በሜሬቱ ላይ የሚገኝ ንብረት ሊሻሻል ይችላል፡፡
- ወሉን የማስረዝ ምክንያቶች፡- የማስረከቢያ ጊዜው ካለፈ፣ የሜሬቱን ግብር አለመክፈል፣ ከአንድ ዓመት በላይ በሜሬቱ ላይ (ያለ ምንም በቂ ማስረጃ) ሥራ አለማከናወን፣ ወይም የኢንቨስትመንት ቢሮው ሜሬቱን ሳያስረክብ ሲቀር፡፡
- ከ6 ወራት በኋላ ሊሻሻል ይችላል፡፡
- ዝወውር ይፈቀዳል ሆኖም የኢንቨስትመንት ቢሮው እንዲያውቀው ማደረግ አለበት፡፡

የሊዝ ሰነዱ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ጥረት እየተደረገ ቢሆንም የሊዙን የወል ቃሎች ተግባራዊ ለሟድረግ ብዙም እንቅስቃሴ አይታይም፡፡ የክልልና የወረዳ መስተዳድሮች ዋናው ትኩረታቸው ከሜሬት ኪራይ የሚገኘውን ክፍያ የማሰብሰብ ብቻ ነው፡፡ እንዲሁም የእርሻ አስተዳዳሪዎች (በተለይም የአገር ውስጥ ባለሃብቶች በሊዝ የወሰዷቸውን እርሻዎች የሚያስተዳድሩት) የሊዙ ተከራዮች ባለመሆናቸው በስምምነቱ ላይ የሰፈሩት ጉዳዮችና ኃላፊነቶችን የራሳቸው አድርጎ ያለመወሰድ ችግር አለ፡፡ ከዚህ ሌላ ግን በሊዙ ላይ የሰፈሩት አንዳንድ ነጥቦች ራሳቸው አሻሚ በመሆናቸው ለመተግበር አስቸጋሪ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ ለምሳሌ የአካባቢ ብክለትና የአፈር መሸርሸር ማለት የሚቻለው እንዴት ነው? ባለሃብቱ ሥራውን አላከናወነም የሚያስብለው በቂ ምክንያቶች ምንድናቸው? "የሜሬት ግጭት" ተብሎ የተጠቀሰው ምንን ያካተተ ነው? የሚሉት ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በሚጨሻም የሊዙ ስምምነት ባለሃብቱ የሚያገኘው ጥቅም እየጨመረ የሚሄድበትን ሁኔታ እንዲሁም በሥራ ላይ ሊከሰቱ የሚቺሉ ሁኔታዎች እየቀነሱ ስለሚሄዱበት ሁኔታ አስረጅ የሆነ ምንም ቃል የለም፡፡ በባለሃብቱ ማመልከቻ ላይ እንደተገለጸው የሠራተኛ ቅጥር ጉዳይና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በተጠየቀው መሠረት እንደሚዝገበሩ የሊዝ ስምምነቱ ምንም ዋስትና አይሰጥም፡፡ ከዚህ በተጨሜሪም በማመልከቻው ላይ የተጠቀሰው የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ካፒታል እንደተባለው በሥራ ላይ ስለመዋሉ ምንም ዓይነት ማረጋገጫ የለም፡፡

## ሊዙ በሥራ ላይ የሚቆይበት ጊዜ

"እዚህ አገር ሜሬት የመንግሥት ንብረት ነው፤ ሆኖም መንግሥት ይህንን መብቱን በሊዝ መልክ ይሰጣል፡፡ ይህም የሚዛዋወር፣ የሚታደስ መብት ሲሆን ቃለማሃላው በብዙ መልኩ ሲታይ የሊዝ የባለቤትነት ያህል ሊቆጠር ይቻላል ለማለት ያስደፍራል፡፡" የካሩቱሪ ጠቅላይ ሥራአስኪያጅ፤ ሳይ ራማክሪሻን[104]

የተለያዩ ምንጮች የሊዙን የሥራ ዘመን ሲያስረዱ አንዳንዶች እስከ 99 ዓመት እንደሚደርስ ይጠቅሳሉ፡፡ በ2000 እና 2001ዓም የተፈረሙት የሊዝ ውሎች በሥራ ላይ የሚቆዩበት ዘመን እንደየውሉ የሚለያይ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የሚከናወኑት ውሎች ግን ወጥነት ያላቸውና ዘመናዊ አሠራርን የተከተሉ ናቸው፡፡ በፌደራል ደረጃ የሚፈረሙት የሊዝ ውሎች በአብዛኛው ለ25 ዓመት የሚቆዩ ሲሆን የካፒታል ግብዓቶችን በሰፊው ለሚጠቀሙ ሰብሎች ምርት (እንደ ስኳር፣ የአግሮነዳጅ የመሳሰሉት) ሲባል የሊዙ ዘመን እስከ

45ዓመት ሊደርስ ይችላል፡፡ እንዲሁም እነዚህ በፌደራል ደረጃ የሚፈረሙ ሊዞች እንደገና ለ45 ዓመት ሊታደሱ ይችላሉ፡፡ በክልል ደረጃ ደግሞ ለምሳሌ በቤንሻንጉል የሜሬት ሊዝ ወል ከ20 እስከ 35 ዓመት ሊደርስ የሚችል ሲሆን ይህም የሜሬት ይዞታው በማሳኖ ወይም በዝናብ የሚለማ የሚሆኑ ጉዳይ ወሳኝነት አለው፡፡ በኦሮሚያ ደግሞ የሜሬት ሊዝ ከ20 እስከ 45ዓመት ድረስ ሥራ ላይ እንዲወል ሆኖ ሊፈረም ይችላል፡፡



ከፍተኛ ማጠን ያለው የአፈር ደለል የተሸከመ ወንዝ በኦሮሚያ ክልል

## ሣጥን ሰ፡ ሳውዲ ስታርና የፖኬዲ ማደር

በትወልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑት የሳውዲው ዜጋ በሊዮኔር ማሕሙድ አላሙዲ በባለቤትነት የሚያስተዳድሩት ሳውዲ ስታር የግብርና ልማት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ በጋምቤላ ክልል በአልዌሮ ወንዝ አካባቢ አቦቦ አቅራቢያ 10ሺህ ሐክታር ሜሬት ላይ ሥራውን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከተለያዩ የዜና አውታሮች የሚሰማው ወሬ ግን ሳውዲ ስታር አሁን ከወሰደው የሜሬት ይዞታ በተጨማሪ 500ሺህ ሐክታር ሜሬት ከጋምቤላና ከሌሎች ክልሎች በመውሰድ 1ሚሊዮን ቶን ሩዝ የማምረት ፍላጎት እንዳላቸው ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ ሌላ በቆሎ፣ ጤፍ፣ የሸንኮራአገዳ፣ እና የዘይት ፍሬዎች የማምረት ተስፋ እንዳላቸውም ይነገራል፡፡[105] እነዚሁ ከዜና አውታሮች የተገኘው ዘገባ እንደሚጠቁመው ኩባንያው ከጋምቤላ ለ60ዓመት በወሰደው 10ሺህ ሐክታር የሜሬት ይዞታ ላይ ምንም ዓይነት የሜሬት ኪራይ ክፍያ እንደማይከፍል[106] (በነጻ የተሰጠው) መሆኑን ቢጠቁሙም ሌሎች ግን በሐክታር 158ብር (9 ዶላር ከ60ሣንቲም በሐክታር) ኩባንያው እንደከፈለ ይናገራሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት ሳውዲ ስታር በልዩ ፈቃድ በጋምቤላ ሩዝ እያሚተ ሲሆን በደብረዘይት ደግሞ የሩዝ ምርቱ ወደውጪ ለገበያ የሚዘጋጅበት (የሚቀለወልበት) ፋብሪካ ከፍቷል፡፡

"ፎርብስ" ተብሎ በሚጠራውና በዓለም ላይ የሚገኙ ባለጸጎችን ዝርዝር በሚያወጣው መጽሔት መሠረት አላሙዲ ከዓለማችን የ64ኛውን የባለጸጋነት ደረጃ አጎናጽፏቸዋል፡፡[107] ግለሰቡ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ወስጥ በተለያዩ የንግድ ማስኮች የተሰሙሩ ሲሆን ከእነዚህም ማካከል የኮንስትራክሽን፣ የከብት ልማት እና የወርቅ ሥራዎች ጥቂቶቹ ናቸው፡ ከገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ጋር የቅርብ ትስስር እንዳላቸው የሚገረው እኚህ ግለሰብ

በ1997ዓም የምርጫ ዘመቻ ወቅት ኢህአዴግን የሚወክል ዓርማ ያለበት የውስጥ ሸሚዝ ለብሰው በማሳየታቸው ከፍተኛ ክርክር አስነስቶ ነበር፡፡ ከሁለት ዓመት በኋላም "ለኢትዮጵያ እና ለሕዝቧ ላበረከቱት ምሳሌያዊ የልማት ተግባር" ለሚሌኒየም ጊዜ የተሰጠውን "የሚሊኒየም ልዩ የወርቅ ሜዳልያ" በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠልቆላቸዋል፡፡

በጋምቤላ የሳውዲ ስታር ቃልአቀባይ የሆኑት አቶ ግርማ ቦጋለ ድርጅታቸው ልዩ የሆነ ብልሃት በማጠቀም ለሩዝ ምርት የሚያስፈልገውን የውሃ ማጠን እንደሚቆጣጠሩ (እንደሚወስኑ) ቢናገሩም የአልዌሮ ወንዝ (ሳውዲ ስታር በሊዝ በወሰደው አካባቢ ተገድቧል) 1ሺህ 800 ሔክታር የሩዝ እርሻ ሜሬት በመስኖ ለሜልማት የሚያስችል ውሃ ብቻ ነው ማቅረብ የሚቻለው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የአልዌሮን ወንዝ በመጥለፍ የሩዝ እርሻውን ለሜልማትና የ30ኪሜ በሲሚንቶ የሚሠራ የማስኖ ቦይ ሥራ ለማከናወን ጨረታ ወጥቷል፡፡ ለሳውዲ ስታር ተጨማሪ የውሃ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ በዚሁ አልዌሮ ወንዝ ላይ ሌላ ግድብ ለማሠራት ዕቅድ ወጥቷል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን ቦታውን በጎበኘበት ወቅት የማስኖ ቦዮቹን ለማዘጋጀት ማጠነሰፊ የሆነ የምንጣሮና የጽዳት ሥራዎች ሲከናወኑ ተሜልክቷል፡፡

በሳውዲ ስታር የሚሚተው ሩዝ በአብዛኛው ለወጪ ንግድ የሚቀርብ ሲሆን ለወጪ ገበያ የመቅረብ ብቃት የሌለው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ሩዝ ደግሞ (ከ7 ሚሊሜትር በታች የሆነው) ለአገር ወስጥ ገበያ ወይም "የሚሻጫ ገበያ በተገኘበት ቦታ" ይሸጣል፡፡

በማስረጃ ለሚረጋገጥ ባይቻልም ሳውዲ ስታር ለቀንበላ ሠራተኞቹ በግምት በቀን 50ብር (3ዶላር) ይከፍላል የሚባል ዘገባ አለ፤ ይህም በአሁኑ ወቅት ከሚከራበት 10-12 ብር የቀን ክፍያ በእጅጉ የላቀ ነው፡፡ ኩባንያው በየ100ሺህ ሔክታር ሜሬት ከ4ሺህ እስከ 5ሺህ ጊዜያዊ ሠራተኞችን ሊቀጥር ይችላል የሚል ግምትም አለ፡፡

ሳውዲ ስታር በሊዝ በተረከበባቸው የሜሬት ይዞታዎች ላይ የሚገኙ ትናንሽ መንደሮች (ኦሬድሂና ኦሪጂን ጨምሮ) አሁን በጋምቤላ እየተካሄደ ባለው የመንደር ምስረታ ፕሮግራም መሠረት ከአልዌሮ ወንዝ ባሻገር ወደ ፖኬዲ እንዲዛወሩ ተደርጓል፡፡ (ሣጥን ቸ ተጨማሪ ሚጃ ይሰጣል) የአካባቢው ነዋሪዎች የአልዌሮን ወንዝ በአሁኑ ጊዜ ዓሣ ለማጥመድ፣ ለመጓጓዣ፣ ለውሃ አቅርቦት፣ ለእርሻ እንዲሁም ከወረራ ለመካላከያነት ይጠቀሙበታል፡፡

ከአልዌሮ ወንዝ ባሻገር ሳውዲ ስታር ተግባራቱን ከሚያከናውንበት ሞዱ ከአቦቦ ከተማ 36 ኪሜ ርቀት ላይ የምትገኘውን ፖኬዲን ይህ የጥናት ቡድን የጎበኘ ሲሆን ከወንዙ ባሻገር ከፍተኛ የጥርጊያና ምንጣሮ ተግባር የሚያከናውኑ ዶዘሮች ድምጽ ማስማት ይቻላል፡፡ በወንዙ ዳርቻ የሚገኙት መንደሮች የአሰባጥሮ እርሻ ስልትን በማከተል በቆሎ ያሚርቱ ነበር፡፡ ሆኖም አሁን እነዚህ አካባቢዎች በሙሉ በሳውዲ ስታር ተመንጥረዋል፡፡ ይህም በሚሆኑ የእርሻ ቦታዎቹ ወደአለሚኖር ቢቀየሩም የወንዙ መሠረጃዎች ግን አልተነኩም፡፡ አካባቢው በሳውዲ ስታር ከመመንጠሩ በፊት መንደረተኞች የምግብ እጥረት በሚያርበት ጊዜ ጫካውን ምግብ ለማሰብሰብ፣ ለማገዶ እንጨት እንዲሁም ለህክምና ይጠቀሙበት ነበር፡፡

ነዋሪዎቹ ከአካባቢያቸው ተነስተው ወደሌላ ከማዛወራቸው በፊት ከመንግሥትም ሆነ ከሳውዲ ስታር ጋር ዝወውራቸውን በተማከተ ምንም ዓይነት ምክክር አልተደረገም፡፡ መንደረተኞቹ አካባቢያቸውን ለቅቀው መውጣት እንዳለባቸው የሚያውቁት ዶዘሮች በአካባቢያቸው ምንጥሮ ለሚድረግ ሲያጓሩና ሜሪያቸው ለባለሃብት ማጠቱ ሲነገራቸው ብቻ ነው፡፡ ጉዳዩ ተገቢ አለሚሆኑንና የትውልድ ቀያቸው ለዚህ ምንጥሮ መዳረጉን ለመንግሥት ሲያሳውቁ የመንግሥት ባለሥልጣኖች የማሰሳቸው ሚልስ "እናንተ ምንም ሜሬት የላችሁም፣ መንግሥት ብቻ ነው ሜሬት ባለቤት"[108] የሚል ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት በጋምቤላ ምንም ዓይነት የሜሬት ባለቤትነት ሚረጋገጫ ሰርቲፊኬትም ሆነ ዋስትና የሚሰጥ አሠራር የለም፡፡

የአገር ውስጥ ባለሃብቶች የሜት ይዞታዎችን በወንዙ በኩል በስተሰሜን ያለውን ቦታ እየወሰዱ ባለበት ባሁኑ ጊዜ፣ ሳውዲ ስታር ደቡባዊውን ክፍል እየማጠረ ከሚሆኑ ጋር ተዳምሮ፣ የአልዌሮ ወንዝ ማደቡ የሚቆጣጠር በሆነበት፣ የማደር ምሥራታው ፕሮጀክት ተጽዕኖ፣ በአካባቢው የሚኙ ጎሣዎች የሚደርስት የሚቋርጥ ወረራ እንዲሁም አካባቢያቸው አጠቃላይ ሁኔታ እየተለወጠ ከሜዱ አንጻር የፖኬዲ ነዋሪዎች መጻዒ ዕድል አስቃቂ እንደሚሆን ማመት አያዳግትም፡፡ አንድ የማደሩ አዛውንት ወደ አንድ ልጅ እየጠቆሙ የተናገሩት እየተካሄደ ያለውን ሁኔታ ያጠቃልለዋል፤ **"ለእነዚህ ልጆቻችን ያለው የወደፊት ተስፋ ምንድነው? የምንማበውን ከማግኘት አኳያ ስንመለከተውም ሁኔታው በጣም አስቸጋሪ ነው . . . በአቾለሲ እና በዓሳ ብቻ መኖር አንችልም፡ ይህ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡"**

## 2.8 ምክክርና ግልጽነት

### ማኅበረሰባዊ ምክክር

ይህ የጥናት ቡድን ከተዘዋወረባቸው ቦታዎች በአንዱ እንኳን ከተፈናቃይ የአካባቢው ነዋሪዎች ጋር የሉዙን ቦታ በተመለከተ ምንም ዓይነት ማኅበረሰባዊ ምክክር አለመደረጉን አረጋግጧል፡፡ በሁሉም የሥልጣን ዕርከን ላይ የሚኙ የመንግሥት ባለሥልጣናት በሰጡት ቃለምልልስ ምክክር የሌላ አካል ኃላፊነት ወይም በሌላ የመንግሥት ማምሪያ መካሄድ ያለበት ነው በሚል ነበር፡፡ ሌሎች የመንግሥት ባለሥልጣናት ደግሞ ምክክርን በተመለከተ በደንብ የተቀመጡ ሰነዶች እንዳሉና እነዚህም ሰነዶች በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (EIA) ውስጥ እንደተካተቱ ይናገራሉ፡፡ ሆኖም የትኛውም የመንግሥት መ/ቤት ይህንን ሚጃ ቅጂ ሊሰጥ አልፈለገም ወይም አልቻለም፡ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ 299/1995 የክልል ማስተዳድሮች የተጽዕኖ ጥናት ዘገባውን በተመለከተ ኅብረተሰቡን ማጠየቅ አለባቸው በማለት ይደግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከኅብረተሰቡም ሆነ ተጽዕኖው ካረፈባቸው ማኅበረሰቦች የሚመጣ ማኛቸውንም ዓይነት አስተያየት በዘገባው መካተት አለበት ይላል፡[109] የመንግሥት ባለሥልጣናት እንደሚሉት ከሆነ ማኅበረሰባዊ ምክክር በሦስት የተለያዩ ሒደቶች ይካሄዳል፡

- የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ በባለሃብቱ መቅረብ እንዳለበት ሆኖም ይህ ግምገማ ተግባራዊ እንዲሆን የሚስገድድ ባለመኖሩ ግምገማው አይካሄድም ማለት ይቻላል፤
- ሜቱ ለኢንቨስትመንት ተገቢ መሆኑን የሚወስነው የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግምገማ መካሄድ እንደሚገባው ሆኖም በተግባር የተደረገው የሚያሳየው ግን ግምገማው ወደ ፌደራል ባንክ ለሚሄዱ ትልልቅ የሜት ይዞታዎች መካሄዱን፤
- የሊዙ ርክክብ ከመደረጉ በፊት በወረዳ ወይም ቀበሌ ባለሥልጣናት በኩል ያልፍ ዘንድ እንደሚገባው ሆኖም ግን በተግባር እየተደረገ ያለው የትኛውም የወረዳም ሆነ የቀበሌ ባለሥልጣን እንደት፣ መቼ እንዲሁም ወረዳው ወይም ቀበሌው በምን ደረጃ ምክክር መደረግ እንዳለበት ማንም የሚያውቅ አለመሆኑ ያለው የአሠራር ሁኔታ ነው፡

### ግልጽነት

የሜት ኢንቨስትመንትንም ሆነ የውል ድርድር በተመለከተ ምንም ዓይነት ግልጽነት የለም ማለት ይቻላል፡፡ አንድ የቀድሞ የፌዴራሉ ፓርላማ አባል የሆኑ ሲናገሩ "(ስምምነቱን) ማንም አይቶት አያውቅም፤ ይቅርና አግባብ ባለው የሚኒስቴር መ/ቤት የሚሰሩት እንኳን አይተውት አያውቁም፡ ምናልባት ጉዳዩን ጥብቅ ትስስር ያለው ሚኒስትር እንደ ወሌታ ተቆጥሮ እንዳያይ ሊደረግ ይችላል፤ ከዚያ ሌላ ግን ምንም ነገር የለም" ብለዋል፡፡ ጉዳዩን አስመልክቶ አንድ ባለሃብት ሲናገሩ ደግሞ በስምምነቱ ላይ የሰፈሩት በሙሉ በምስጢር ማጠበቅ አለባቸው የሚል ሚሰሪያ አንቀጽ በመኖሩ ነው ይህ ሊሆን የቻለው ይላሉ፡፡ ሆኖም ከተለያዩ የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር በተደረገው ቃለምልልስ የሚፈረሙትን ውሎች ዝርዝር በተመለከተ አጠቃላይ የሆነ የግልጽነት ዕጥረት ስለመኖሩ ማስረጃ ማቅረብ የሚያሻው አይደለም፡

## 2.9 ሕግ ማክበርና ክትትል

አብዛኛዎቹ የሊዝ ስምምነቶች በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የተወሰነ ሥራ እየተካሄደ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ አንቀጽ አላቸው፡፡ በጋምቤላ ክልል የሚደረገው ስምምነት እንደሚለው ከሆነ ሥራ ለማከናወን የሚፈቅድ በቂ ምክንያት እስከሌለ ድረስ የልማት ሥራው በአንድ ዓመት ወስጥ መካሄድ እንዳለበትና ከዚያም ባሉት ቀጣይ ዓመታት ሥራው መካሄድ እንዳለበት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የኢንቨስትመንት የምስክር ወረቀት (ከሜሬት አጠቃቀም ስምምነት ወይም ከሜሬት ፈቃድ በተጻጻሪ ሚለኩ) በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡ በቤንሻንጉል ክልል ግን በሜሬት ይዞታው ላይ በየስድስት ወሩ የተወሰነ ሥራ መከናወን እንዳለበት ቢጠየቅም የኢንቨስትመንት ቢሮው እንደሚለው ከሆነ ይህ ተግባራዊ ስለመሆኑ ቁጥጥር ተደርጎ አያውቅም ማለት ይቻላል፡፡

በዚህ የጥናት ቡድን የተገመገሙት ስምምነቶች በሙሉ በግልጽ እንደሚያሳዩት ስምምነቱ በተባለው መሠረት የሚፈጸም ከሆነ እንደሚስረዝ ይናገራል፡፡ ሆኖም በተግባር የሚታየው ግን ከዚህ የተለየና ሕጉን በተግባር ማዋልን በተመለከተ ያለው አሠራር እንዳለ የሚቆጠር በጣም ደካማ የሆነ ነው፡፡ በስምምነቶቹ ላይ የሰፈረው የውል አንቀጽ ግልጽ ቢሆንም በዚህ የጥናት ቡድን በተጎበኙት የኢንቨስትመንት ቦታዎች ላይ ተፈጻሚ ሲሆን አይታይም፤ በተቃራኒው በሊዙ ስምምነት ላይ በግልጽ የሰፈረው ሥራ የመጀመር ውል በግልጽ ሲጣስ ተስተውሏል፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ስምምነቶች አንዱ ብቻ በመንግሥት ምርመራ እየተደረገበት ይገኛል፡፡

ይህ የጥናት ቡድን ያነጋገራቸው የክልል ማስተዳደር ባለሥልጣናት በሙሉ ጥቅማጥቅምን፣ ምርትን፣ የውሃና የሜሬት አጠቃቀምን በተመለከተ ምንም ዓይነት ክትትል
እንደሚካሄድ ገልጸዋል፡፡ በተግባር ላይ የዋለው ክትትል የሜሬት ይዞታው ቢያንስ በከፊል በሥራ ላይ ስለመዋሉ እንዲሁም ተገቢው ዓመታዊ ክፍያ ስለሚፈጸሙ የሚደረግ ብቻ ነው፡፡ ወደፊት በርካታ የእርሻ ሜሬቶች እየለሙ ሲሄድ በቂ በጀትና ጊዜ ስለሚኖር አሁን ያለው ሁኔታ እየተሻሻ እንደሚሄድና በስምምነት ወሉ መሠረት ክትትልና ቁጥጥር እንደሚካሄድ አብዛኛዎቹ የክልል ማስተዳደር ባለሥልጣናት ተስፋ ያደርጋሉ፡፡

በተመሳሳይ ሚለኩ ባለሃብቶች በስምምነቱ መሠረት ሥራቸውን በተመለከተ ተገቢውን ሪፖርት እያቀረቡ ስለመሆኑ ይህ የጥናት ቡድን ያገኘው ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም፡፡ ባለሃብቶች በየጊዜው የሚያቀርቡት ሪፖርት በተከራዩት የሜሬት ይዞታ ላይ እያከናወኑ ያሉትን የልማት ተግባር የሚገልጽ በመሆኑ የመንግሥት መ/ቤቶች ለቁጥጥር ተጨማሪ ወጪ ሳያወጡ በሜሬት ይዞታዎቹ ላይ በተጨባጭ እየተካሄደ ያለውን እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል፡፡ ሆኖም በተግባር እየታየ ያለው ይህ ሳይሆን ባለሃብቱ የሜሬት ይዞታውን ከተረከበና አስፈላጊውን ፈቃድ ካገኘ በኋላ ሕጉን በማክበርም ሆነ የክትትልና የሪፖርት አደራረግ ተግባራት ክንዋኔው እጅግ ያነሰ መሆኑ ነው፡፡

# 3. ጥቅማጥቅምና ተጽዕኖ

አሁን ካለው የሕዝብ ቁጥርና የሃብት አጠቃቀም ተጽዕኖ አኳያ እየተፈጸመ ያለው የሜሬት ውል ዋንኛ ተጠቃሚ ሌሎች ሲሆኑ የጉዳቱ ገፈት ቀማሽ ግን የአካባቢው ነዋሪ ነው፡፡ የሜሬት አጠቃቀም ዕቅድና ወጤታማ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ መኖር በተወሰነ ሚለኩ በአካባቢው ነዋሪ ላይ ሊደርስ የሚችለውን አስከፊ ተጽዕኖ ሊከላከል ይችላል፤ ሆኖም የእነዚህ አለመኖር ቁጥጥር በተገቢው ሁኔታ እንዳይካሄድ ከማድረጉ በላይ ለአካባቢው ሕዝብ ስጋት የሚፈጥር ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ በሚካሄደው የሜቴት ይዞታ ኢንቨስትመንት በርካታ ወገኖች ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ እነዚህም፦ –

- የፌደራሉ መንግሥት፡ ከውጪ የሚመጣው ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መሠረተልማቶችን በማሻሻል፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የግብር ገቢ ሜጨመር፣ ከውጪ መንግሥታት ጋር ያለው ግንኙነት ማሻሻል ዋንኞቹ ተጠቃሾች ናቸው፡፡
- የክልል ማስተዳድሮች፡ የሜቴት ኢንቨስትመንት ከፌደራል መንግሥት የሚመጣውን እርዳታ በማጠናከር፣ የሥራ ዕድልን በሜጨመር፣ እንዲሁም የመሠረተልማት ማሻሻልን በመደገፍ የራሱን ሚና ይጫወታል፡፡
- የወረዳ አስተዳደሮች፡ ከሜቴት ይዞታው በሚገኘው የኪራይ ገቢ ይጠቀማሉ፡፡
- ደገኞች፡ በተለይም ወንዶች በቀን ሠራተኛነት በመቀጠር ወይም የራሳቸውን የሥራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡
- ባለሃብቶች፡ ከምርታቸው ትርፍ ይጠቀማሉ፡፡ ትግሬዎችና የከተማው ምርጦች እጅግ ርካሽ በሆነ ዋጋ እንዲሁም የሕግ ተጽዕኖ በሌለበት ሁኔታ የሜቴት ይዞታዎችን ይረከባሉ፡፡ ወደፊት ገበያው ሥርዓት እየያዘና የሜቴት ዋጋው እየጨመረ ሲሄድ እነዚህን የሜቴት ይዞታዎች ወደሌላ በማስተላለፍ ወይም በመሸጥ እንዲሁም ወደፊት መንግሥት በሜቴት ላይ ያለውን የባለቤትነት ሥልጣን በሚያላላበት ጊዜ እነዚህ ባለሃብቶች ከፍተኛ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡
- ሌሎች የንግድ ተቋማት፡ በሌሎች ክፍለ ኢኮኖሚዎች የሚገኙ የንግድ ተቋማት በተለይም ግብርና ተኮር የሆኑት፣ የግብርና ግብዓት አቅራቢዎችና በማናኛና ንግድ አስተላላፊነት የተሰማሩ ከዚህ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ እነዚህ አብዛኛዎቹ የንግድ ተቋማት የሚገኙት በከተሞች አካባቢ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ማለት ይቻላል የሜቴት ኢንቨስትመንት ከተጧጧፈበት አካባቢ የራቁ ናቸው፡፡

## በሚፈጠረው ችግር ገፈት ቀማሽ ማነው?

- **የአካባቢው ነዋሪዎች፡** የሜቴት ኢንቨስትመንት በርካታ ባዕዳንን የሚስብ ሲሆን ይህም በአካባቢው ላይ አሉታዊ የማኀበራዊ ተጽዕኖን፣ ራስን የመቻል ብቃትን የሚዳከም፣ በኅብረት የመኖሪያ ሥፍራዎችንና የትውልድ ቀዬዎችን የሚወደም፣ የውሃ አቅርቦት የሚነስ እና አካባቢ የመበከል ተጽዕኖዎችን ያስከትላል፡፡
- **የወራጅ ውሃ ተጠቃሚዎች፡** የሜቴት ልማት የውሃ ሃብትን በመበከል በወራጁ ተጠቃሚዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡
- **የዱር አራዊት፡** በሜቴት ይዞታ ልማት ምክንያት የዱር አራዊት መኖሪያ ስለሚያጡ፣ አካባቢያቸው ስለሚበከልና ስለሚበታተኑ እነርሱም የአሉታዊ ተጽዕኖ ተጠቂዎች ናቸው፡፡

አሁን እየተካሄደ ያለው ኢንቨስትመንት የሚያስከትለው ጥቅምም ሆነ ተጽዕኖ በበርካታ ሁኔታዎች ላይ የተመረኮዘ ሲሆን ግብርናን አስመልክቶ የሚካሄደው የንግድ ተግባር ገና በእንጭጩ ከመሆኑ አንጻር አብዛኛዎቹ ተጽዕኖዎች ገና ወደፊት የሚታወቁ ናቸው፡፡ ከዚህ በታች የተሰጠው ትንተና ሁሉንም ያጠቃለለ ባይሆንም በተወሰነ ሚልኩ ገና ከጅምሩ እየተከሰተ ያለውን ሁኔታ የሚዳስስና ከእንደዚህ ዓይነት የኢንቨስትመንት ሥራ ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን በጥቅሉ የሚያስረዳ ነው፡፡

## 3.1 ጥቅማጥቅም

በታሳቢነት ከሚገኙት ጥቅማጥቅሞች መካከል አንዱ የኢኮኖሚ ወጠት ሜጨመር (በቀጥተኛ የውጪ ኢንቨስትመንትና በተያያዥ የሚመጡ ወጠቶች)፣ ተቀማጭ የውጭ ምንዛሪ ሜጨመር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የመሠረተልማት ግንባታ፣ የሥራ ዕድልና ሌሎች የልዕለምጣኔሃብት ጥቅሞችን ያካተተ ነው፡፡

### የቴክኖሎጂ ሽግግር

የግብርና ልማት መር ኢንዱስትራላይዜሽንን (ADLI) የልማት ስትራቴጂ አድርገው በተገበሩ አገራት ወስጥ የተማዘገበው ስኬት አንድ ወጥ ያልሆነ ነገር ግን የተደባለቀ ነው፡፡ ከእነዚህ ተሞክሮዎች በማሳት የADLI

ደጋፊዎች ስትራቴጂው ቴክኖሎጂን በማሸጋገር ድህነትን ለማስወገድ፣ የመሠረተልማት አወታሮችን ለማሻሻል እንዲሁም በአነስተኛ ግብርና ላይ የተሰማሩ ገበሬዎች ወደ ገበያው እንዲገቡ ለማድረግ ይረዳል በማለት ይከራከራሉ፡፡ እንዲሁም የሥራ ዕድል በማከፈት የሰዎችን የመግዛት አቅም እንዲጎለብት በማድረግ በካፒታል ማሻሻያዎች ላይ ገንዘባቸውን እንዲያወሉ ያስችላቸዋል የሚል አማካከትም አለ፡፡

እነዚህ ጠንካራ ጎኖች በኢትዮጵያም ተግባራዊ ይሆናሉ ለማለት አሁን ወቅቱ አይደለም፤ ምክንያቱም አሁን እየታየ ያለው ሁኔታ ተስፋ የሚሰጥ አይደለም፡፡ አብዛኛዎቹ በአነስተኛ የግብርና ተግባር ላይ የተሰማሩ ገበሬዎች አሁንም ዝቅተኛ የቴክኖሎጂ ግብዓት በማጠቀም በእርሻ በሬ የሚጠቀሙ ሲሆን የተቀረውን ሥራ ደግሞ በእጃቸው ያከናወናሉ፡፡ በመሆኑም በትልልቅ የእርሻ ተግባር ላይ የሚገኙት ማጠነሰፊ የካፒታል ኢንቨስትመንት የሚጠቀሙ በመሆናቸው በርካታ ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎችን፣ የመስኖ ተግባራትን፣ ብዛት ያለው የተባይ ማጥፊያዎችን ከማጠቀማቸው አኳያ የቴክኖሎጂ ሽግግሩም ሆነ ዕወቀቱ ወደ አንድ ኢትዮጵያዊ ገበሬ እንዴት ሊተላለፍ እንደሚችል ግልጽ አይደለም፡፡ እነዚህ የቴክኖሎጂ እሴቶች የፋይናንስ ብቃት እነርሱ አሁን ካላቸው ዕወቀትና አቅም እጅግ የላቁ ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ክፍተቶች ሊኖሩ በመቻላቸው ተገቢው የዕቅድና የፋይናንስ ቁርጠኝነት ሊስተካከሉ እንደሚችሉ እሙን ቢሆንም እስካሁን ይህንን የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራዊ የሚያደርግ ስትራቴጂ ስለመኖሩ ምንም ዓይነት መረጃ የለም፡፡

አነስተኛ የአገር ወስጥ የእርሻ ተግባር የሚካሄድባቸው የመሬት ኢንቨስትመንቶች ልክ በአነስተኛ የግብርና እርከን ላይ እንደሚገኙ በአብዛኛው ዝቅተኛ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን ነው የሚጠቀሙት፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች በሥራ ላይ የዋለ የመሬት ይዞታ የምስክር ወረቀት አሠራር ባለመኖሩ እንዲሁም ተፈላጊው የካፒታል ማጠን አናሳ በመሆኑ አዳዲስ የቴክኖሎጂ አሠራር በእነዚህ አነስተኛ የግብርና እርከን ላይ በሚገኙት ገበሬዎች መካከል ለማስፋፋት የሚከብድ ቢሆንም በአነስተኛ የኢንቨስትመንት ተግባር ላይ በተሰማሩት ዘንድ ይህንን የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ ከፍተኛ ዕድል አለው፡፡ በቤንሻንጉል በአንድ መንደር የሚገኙ የጉሙዝ ሽማግሌዎች እንዳሉት "በአንድ ወቅት ጥማድ በሬዎች ለአገልግሎት ሲወሉ ተመልክተን ቴክኖሎጂውን አደነቅን፡፡ አሁን ግን ከእኛ መካከል አንዳንዶች በጥማድ በሬዎች ያርሳሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት ትራክተሮችን እየተመለከትን ነው፤ አንድ ቀን ምናልባት እነዚህን ትራክተሮች እንጠቀምባቸው ይሆናል" ብለዋል፡፡

## የመሠረተ ልማቶች መሻሻል

ከዚህ በፊት ተደርጎ በማያውቅ መልኩ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ወስጥ ከፍተኛ የሆነ የመሠረተልማት ዕድገት በሁሉም እርከን እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ለሁሉም ዓይነት የአየር ንብረት የሚያገለግሉ መንገዶች በሁሉም ክልሎች ዋና ከተሞች ወስጥ እየተሠሩ በመሆናቸው በአገሪቷ ወስጥ የሚገኙትን ገበያዎች በበቂ ሁኔታ እያገናኙ ናቸው፡፡ በ1985 በአጠቃላይ የመንገዶች ርዝመት 19ሺህ ኪሜ ነበር፤ በ2000ዓም ግን ቁጥሩ ወደ 44,300ኪሜ አደጓል፡፡ በ1984 ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ሕዝብ ብዛት 400ሺህ የነበረ ሲሆን በ2000ዓም ወደ 1.7 ሚሊዮን አደጓል፡፡ በዚሁ በ2000ዓም 2,358 ከተሞች በኤሌክትሪክ መረብ ወስጥ ተካትተዋል፤ በ1984 ይህ ቁጥር 300 ብቻ ነበር፡፡ ከ1995 እስከ 1999ዓም ድረስ ባሉት ዓመታት የቴሌፎን ማስመር በእጥፍ የጨመረ ሲሆን የእጅ ስልክ ተጠቃሚው ቁጥር ከ98ሺህ ወደ 1.9ሚሊዮን አደጓል፡፡[110] እነዚህን ሁሉ ፕሮጀክቶች ለማካሄድ የሚያስችለው ገንዘብ የተገኘው ከአወሮፓ ኅብረት፣ ከቻይና፣ ከጃፓን እና ከነዳጅ ላኪዎች ድርጅት OPEC ከመሳሰሉ ለጋሾች ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በከፍተኛ ሁኔታ በአገሪቷ ወስጥ እየተካሄዱ ይገኛል፡፡ የኤሌክትሪክና የቴሌኮሚኬሽን መሠረተልማትም እንዲሁ እያደገ ነው፡፡

በዚህ የጥናት ቡድን በተቃኙት የመሬት ይዞታ ወሎች ወስጥ በአንደኛውም እንኳን የመሠረተልማት ለማሻሻል በባለሃብቱም ሆነ በመንግሥት የተደረገ ስምምነት የለም፡፡ የመሬት ይዞታ ለኢንቨስትመንት ጥቅም ላይ ሲወል ከዚህ በፊት በልማት ወደኋላ በቀሩ አካባቢዎች የሚደረግ የመሠረተልማት መሻሻል የነዋሪወን ሕይወት እንደሚቀይር ጥርጥር የለወም፡፡ ሆኖም ግን ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ባለሃብቶች በሙሉ ግን አሁን ያለው መሠረተልማት ለእነርሱ ሥራ በቂ እንደሆነ ነው የገለጹት፡፡

አብዛኛዎቹ በአነስተኛ ማጠን የግብርና ሥራ የሚያከናወኑት ባለሃብቶች በዝናብ ላይ ጥገኞች ላይ ናቸው፡፡ ማጠነሰፊ ሥራ እየሰሩ ካሉት

ባለሃብቶች መካከል ቢያንስ አንዱ (ሳውዲ ስታር በጋምቤላ) በአልዌሮ ወንዝ ላይ የግድብና ሰፋ ያለ የማስኖ ቦዮች ግንባታ ለማድረግ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ሌላው ታላቅ ባለሃብት ካሩቱሪ መደበኛ የመሠረተልማት ሥራዎችን (እንደ ኤሌክትሪክ፣ ውሃ አቅርቦት፣ ወዘተ የማሳሰሉትን) ለማከናወንና ምርቱን ለገበያ ለማቅረብ በአቅራቢያው የሚገኘውን የባሮ ወንዝን እንደሚጠቀም አስታውቋል፡፡[111] በርካታ በአነስተኛ ማጠን የግብርና ተግባር ላይ የተሰማሩ ወደፊት "ለስላሳ" የመሠረተልማት አውታሮች (ዘመናዊ የስርጭት ማስመር፣ የምርት ገበያ ልወውጥ፣ ወዘተ የማሳሰሉት) ዕድገት እየጨመረ ሲሄድ ምርታቸውን ለዓለምአቀፍ ገበያ የማቅረብ ዕድላቸው እንደሚጨምር ተስፋ ያደርጋሉ፡፡

የመሠረተልማት በበቂ ሁኔታ አለማስፋፋት በኢትዮጵያ የልማት ዕድገት ላይ ተጽዕኖ ሲያደርጉ ከነበሩት ችግሮች መካከል አንዱ ነው፡፡ አሁን እየተካሄደ ካለው የመሬት ኢንቨስትመንት አኳያ ባለሃብቶች የመሠረተልማት እንቅስቃሴውን የቀጥታ ድጋፍ በማስጠት፣ የገንዘብ መዋጮ በማድረግ፣ የተያየ ሽርክና በመፍጠር፣ ወይም በአገራት መካከል የሁለትዮሽ ስምምነት በማድረግ የራሳቸውን ድርሻ ሊወጡ ይችላሉ፡፡

ክፍለኢኮኖሚው ገና በመዳግ ላይ በመሆኑም ሊሆን ይችላል ይህ የጥናት ቡድን በባለሃብቶች የሚከናወን ምንም ዓይነት የመሠረተልማት ክንውን አልተመለከተም፡፡ ብዙዎቹ ባለሃብቶች ትምህርትቤት፣ ክሊኒክ፣ ወዘተ ለመክፈት እንዲሁም ሌሎች የማኅበራዊ ልማቶችን ለማከናወን ቃል የገቡ ቢሆንም ሕጉ በተግባር የመዋሉ ጉዳይ ክትትል እስካልተደረገበት ድረስ እነዚህ ተስፋዎች ሊፈጸሙ ይችላሉ ለማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ ሆኖም ግን በአገሪቷ የመሠረተልማት ዕድገትና በሕዝቡ የኑሮ መሻሻል ወስጥ ባለሃብቶች የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ ሊኖር እንደሚችል ጥርጥር የለውም፡፡

## ደመወዝ

ለግብርና ነክ የቀን ሥራ የሚከፈለው ደመወዝ ዝቅተኛ ነው፤ ምናልባትም በቀን ከ10ብር እስከ 20ብር ነው፡፡ ቆላማ ካልሆኑ ክልሎች የመጡ አብዛኛዎቹ የቀን ሠራተኞች ወንዶች ናቸው፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች ከሆኑት መካከል ወንዶችም ሆነ ሴቶች ተቀጥረው የመሥራት ሁኔታ ይታያል፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ሠራተኞች የአካባቢው ነዋሪዎች ቢሆኑም አብዛኛው ሠራተኞች ከደጋማው የአገሪቷ ክልሎች የመጡ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሥራው በሚጧጧፍበት ጊዜ (መኸር በማሳሰሉት ወቅቶች) የቀን ሠራተኞች በብዛት ስለሚያስፈልጉ በርካታ ወቅታዊ ሠራተኞች መቀጠራቸው የሚጠተዋል ጉዳይ ነው፡፡

ምንም እንኳን መንግሥት ጠቅለል ባለ መልኩ ዝቅተኛውን የቀን ደመወዝ ማጠንና የአከፋፈል ደረጃ ያሻሻለ ባለመሆኑ የደመወዝ ማጠን በቅርቡ ይስተካከላል ወይም ይጨምራል የሚል ተስፋ የለም፡፡ በየጊዜው ለሚከሰተው የሰራተኛ ፍላጎት በገበያው ላይ ያለው አቅርቦት ከፍተኛ በመሆኑ የደመወዙ ሁኔታ አሁን ባለበት ዝቅተኛ ደረጃ ይቀጥላል፡፡ ንግድ ተኮር የኢንቨስትመንት ሥራ እየተስፋፋ ሲሄድ በተለይም አብዛኛዎቹ የመሬት ይዞታዎች የማምረት ተግባራቸውን ማከናወን በሚጀምሩበት ጊዜ በፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለው ክፍተት እየጠበበ መሄዱ አይቀሬ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የደመወዝ ዋጋ መጨመሩ እንዲሁም የሠራተኛ ጥቅማጥቅሞች እየተሻሻሉ እንደሚሄዱ ማጣመት አያዳግትም፡፡

በብዙ መልኩ ሲታይ ደመወዙ አናሳ ቢሆንም ከደጋማ ክልሎች ለመጡ ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸው ይኸው የደመወዝ ማጠን ጠቃሚ የሆነ የገቢ ምንጭ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የቀን ሠራተኞች መሬት አልባ ወይም በጣም አነስተኛ የሆነ የመሬት ይዞታ ያላቸው በመሆኑ ወደፊት ባሉት ጥቂት ዓመታት ከድህነት የሚያመልጡበት ብቸኛው አማራጭ ከቀን ሥራ የሚያገኙት ደመወዝ እንደሆነ ብዙዎች ይናገራሉ፡፡

## የልዕለምጣኔሃብት (ማክሮኢኮኖሚክስ) ስታቲስቲክ

ከመሬት ኢንቨስትመንት የሚገኘውን የልዕለምጣኔሃብት ጥቅም በትክክል ለመግለጽ አስቸጋሪ ነው፡፡ በአብዛኛዎቹ የፌደራል መ/ቤቶች ከልማቱ ጋር በተያያዘ የሚገለጸው የካፒታል ወጪ ተመን አሳሳች ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ቁጥሮች ገና ወደፊት በወጪ የቀጥተኛ ኢንቨስትመንት (ባለሃብቱ ሞምልከቻውን ሲያስገባ) ቃል የተገባላቸው ናቸው እንጂ በትክክሉ የተከሰቱ የካፒታል መዋዕለንዋዮች አይደሉም፡፡ እነዚህ ከወጪ የሚመጡ የመዋዕለንዋይ ፍሰቶች እየተከሰቱ ለመሆናቸው እንዲሁም ባለሃብቶች አስፈላጊው ችሎታና ካፒታል እንዳላቸው የሚረጋገጫ መንገድ እስከሌለ ድረስ[112] የአገሪቷን ቀጥተኛ የወጪ ኢንቨስትመንት ፍሰት (ከልማት ጋር የተያያዘውን) ከማጠን በላይ የተጋነነ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ለምሳሌ፤

ተስፋ የተገባላቸውን ቀጥተኛ የውጪ ኢንቨስትመንቶችን እንደተከሰቱ አስመስሎ ቢያቀርቡት ከ1998 ጀምሮ ያለው የካፒታል ኢንቨስትመንት በስድስት ዕጥፍ አድጓል ሊያስብል ይችላል፡፡[113] ሆኖም በስፋት ተቀባይነት ያለውን የተባበሩት መንግሥታት የንግድና የልማት ኮንፈረንስ (UNCTAD) ዘዴ በማጠቀም ስሌቱ ከተሠራ ከ1998 ጀምሮ ከውጪ የሚመጣው ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እያሽቆለቆለ እንደሄደ የሚያሳይ ነው፤ ምክንያቱም የUNCTAD ዘዴ በባለሃብቶች ተስፋ የተገባውን የሚያካትት በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም እውነተኛው ከውጪ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣው የኢንቨስትመንት ፍሰትና ከዚያ ጋር ተዳምረው የሚሟጡት ጥቅማጥቅሞች በሙሉ በአሁኑ ወቅት ከመንግሥት ማምሪያዎች በይፋ እየተጠቀሰ ካለው በእጅጉ ያነሰ ነው፡፡

## 3.2 በምግብ ዋስትና ላይ ያለው ተፅዕኖ

የመሬት ኢንቨስትመንትን ከሚስቡ ቦታዎች መካከል በደቡብ ክልልና በጋምቤላ የሚገኙት ለምና ሽለቆማ የመሬት ይዞታዎች ዋንኞቹ ናቸው፤ ምክንያቱም አፈሩ ለምና አካባቢው በርካታ የውሃ ሃብት ስላለው ነው፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ አካባቢዎች በተደጋጋሚ በምግብ ዕጥረት እየተጠቁ ይገኛሉ፡፡ የተባበሩት መንግሥታት የዓለም የምግብ ፕሮግራም (WFP) እንደሚለው ከሆነ ባለፈው ዓመት በግምት 84ሺህ የሚሆኑ ግለሰቦች በጋምቤላ የምግብ ዕርዳታ መቀበላቸውን ዘግቧል፡፡ (በአሁኑ ወቅት የጋምቤላ ሕዝብ ብዛት 310ሺህ እንደሆነ ይገመታል)[114] በኢትዮጵያ የምግብ ዕጥረት በከፍተኛ ሁኔታ በሚታይበት የአፋር ክልል በፌደራል የመሬት ባንክ የተመዘገበና የአዋሽን ወንዝ አካልሎ የሚገኝ 409ሺህ ሔክታር መሬት ግብርናን ወደ ንግድ ለመቀየር በተያዘው አካሄድ ለኪራይ ተዘጋጅቷል፡፡[115]

የመሬት ይዞታን ለንግድ ማዋል በተለይ በምግብ ራሳቸውን ላልቻሉና ለረሃብ አደጋ ለተጋለጡት አንድ ተጨማሪ አስጨናቂ ነገር እንደሆነ ለዚህ የጥናት ቡድን ግልጽ ነው፡፡ በዚሁ ጥናታዊ ዘገባ (በክፍል 1.4) ላይ በምግብ ራስን ላለመቻል ዋንኛ ምክንያት የሆኑት ነጥቦች የመሬት ይዞታዎች በስፋት ለኢንቨስትመንት እየተሰጡ ባሉት የቤንሻንጉል ቆላማ ቦታዎች፣ የጋምቤላ እና የደቡብ ክልሎች በግልጽ ሲከሰቱ ይስተዋላል፡፡

ይህ የጥናት ቡድን ከተዘዋወረባቸው በርካታዎቹ ቦታዎች መካከል የሚገኙትንና ወደ መካራው ለመግባት ጠርዝ ላይ ያሉትን የየአካባቢውን ነዋሪዎች ይህ የጥናት ቡድን የጎበኛቸው ሲሆን ራሳቸውን ለመመገብ ያላቸው ብቃት በበርካታ ነገሮች (የአየር ንብረት ማዛባት፣ ጎርፍ፣ ግጭት ወዘተ) ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ ከእነዚህ አንዱ የተጓደለች እንደሆነ ራሳቸውን ለመመገብ ያላቸው ብቃት አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡

> "የእኛ ዓላማ ረሃብን መዋጋት አይደለም፡፡ እኔ ነጋዴ ነኝ፤ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ምግብ እንዲረከስ ማድረግ፣ አዎንታዊ እንጂ ምን ዓይነት አሉታዊ ችግር እንደሚያስከትል ፈጽሞ ሊገባኝ አይችልም፡፡"
>
> በጋምቤላ ክልል የተሰማሩ የውጪ ባለሃብት[116]

በአብዛኛው የምግብ ዕጥረት የትውልድ እውነታ እየሆነ በመምጣቱ ማኅበረሰቡ ይህንን የምግብ ዕጥረት የሚቋጋበትን የራሱን ብልሃት አዳብሯል፡፡ ለምሳሌ በበርካታ የጋምቤላ ቦታዎች (አቦቦ እና ኢታንግ ወረዳዎች) የሚገኙ ቤተሰቦች ወንዞን ተከትለውና በከፍታ ቦታዎች ላይ አሰባጥሮ በሚዘስ ድንገት ወንዞን ተከትሎ ከሚደረገው እርሻ የሚገኘው ምርት እንደታሰበው ካልሆነ ወይም ከበቂ በታች ከሆነ በችግር ወቅት እንደ መካላከያ ይጠቀሙባታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የምግብ ዕጥረት በሚከሰትበት ጊዜ በአቅራቢያ ከሚገኘው ደን ውስጥ (ፍራፍሬዎችን፣ የኦቾሎኒ ዓይነቶችን፣ ሥሬሥሮችን፣ ቅጥላቅጠልን፣ ወዘተ) ህይወትን ለማቆያ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡ (**ሣጥን** "በ" ላይ ደን ምን ያህል በጋምቤላ ለሚኖሩት የአገሪቷ ተወላጆች የሚሰጠው ጥቅም ተዘርዝሯል)

በዚህ የጥናት ዘገባ በክፍል 3.3 ላይ አሰባጥሮ የሚዘስ ተግባር የሚከናወንባቸው የመሬት ይዞታዎች በባለሃብቶች መጽዳታቸውን ይህ የጥናት ቡድን ተመልክቷል፡፡ የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) እነዚህን
"የተተዉ እርሻዎች" እያለ የሚጠራቸው ቢሆንም እነዚህ የመሬት ይዞታዎች ሆነ ተብለው ለድርቅ መካላከያነት ያገለግሉ ዘንድ በማኅበረሰቡ በዕዳሪ

ሜትነት የተተዉ ቦታዎች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሰፋፊ የደን ቦታዎች ለሜት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ይወሉ ዘንድ መመንጠራቸው ሌላ ለምግብ እጥረት መከላከያ ነዋሪው የሚጠቀምበት ዘዴ ከኅብረተሰቡ ዘንድ እየተወገደ ለመሆኑ ማስረጃ ነው፡፡

የንግድ ተኮር እርሻ ሌላው አሉታዊ ተጽዕኖ የዓሳ ሃብትን (በአንዳንድ አካባቢዎች ዋንኛ የምግብ ምንጭ ሲሆን) እንዲሁም የዱር አራዊትን (ረሃብ ሲጠና አንዳንዶቹ ይታደናሉ) ቁጥር በእጅጉ ማመንመኑ ነው፡፡ ከእነዚሁ እርሻዎች የሚፈሰው ወሃ ብክለት በማስከተል እንዲሁም የአካባቢውን የወሃ ሃብት በመቀነስ የሚፈጥረው ጉዳት ቀላል አይደለም፡፡ ለከብቶች ግጦሽ የሚሆን ሜት እያነሰ፣ እየቀነሰ እንዲሁም እየጠፉ ሜድ ለችግሩ መባባስ ሌላ ምክንያት ይሆናል፡፡ እነዚህ ሁሉ ችግሮች ደግሞ በአሁኑ ጊዜ እየተከሰተ ባለው የአየር ንብረት ለወጥ፣ የመንደር ምስረታ፣ ማቋረጫ በሌለው ግጭት እና በመሳሰሉ ምክንያቶች እየተባባሱ ይሄዳሉ፡፡

በ2001ዓም በጋምቤላ የአቦዶ Abodo woreda (አባንግን ጠይቅ) ወረዳ ካለው 17ሺህ ነዋሪ ሕዝብ መካከል 5ሺህ አንድ መቶ ያህሉ ከዓለምአቀፉ የምግብ ፕሮግራም የምግብ ዕርዳታ ተቀብለዋል፡፡[117] በርካታ የኢንቨስትመንት ተግባራት የሚካሄዱት በዚህ ወረዳ ሲሆን በተለይም ሳዉዲ ስታር 10ሺህ ሔክታር እንዲሁም ካሩቱሪ መቶ ሺህ ሔክር የሜት ይዞታዎችን የተረከቡት ከዚሁ ወረዳ ነው፡፡ (ሣጥን "መ" ይመልከቱ) ከእነዚህ ባለሃብቶች አንደኛው በአልዌሮ ወንዝ
ላይ ግድብ የመሥራት ዕቅድ ያለው ሲሆን ለዚሁ ሥራ ያመች ዘንድ ደኖች እየተመነጠሩ ነው፤ የእርሻ ሜቶችም እየወደሙ ነው፡፡ በአካባቢው የሚኖሩት ማኅበረሰቦች በሙሉ አስገዳጅ የመንደር ምስረታ ዒላማ ተደርጎባቸዋል፤ (ሣጥን "ቸ" ይመልከቱ) ነዋሪዎቹ ዕትብታቸው በተቀበረበት ሜት ላይ ምንም ዓይነት ዋስትና ያለው የሜት ይዞታ የላቸውም፤ ከደጋ ከመጡት የቀን ሠራተኞችና ገበሬዎች ጋር ያለውን ሜት ለመጠቀም ትንቅንቅ ወስጥ ይገኛሉ፡፡ በጣም ጥቂት የሆኑቱ በእነዚህ ማጠነ ሰፊ እርሻዎች ላይ ተቀጥሮው እየሠሩ ይገኛል፡፡

ሌላው በባሮ ወንዝ ዳርቻ የሚኙና 400 ሰዎች የሚኖሩበት ትንሽ መንደር ወስጥ ያሉት ነዋሪዎች እየረደሰባቸው ያለውን ነገር መመልከት በእንደነዚህ ዓይነት አካባቢዎች የሚኖሩ በተለይም ከምግብ ዕጥረት አኳያ የሚደርስባቸውን ለማሳየት በአስረጅነት ሊቀርብ የሚችል ነው፡፡ ነዋሪዎቹ በወንዙ ዙሪያና በአካባቢው በቆሎና ማሽላ የሚያመርቱባቸው የሜት ይዞታዎች ይገኛሉ፡፡ ሆኖም በሰኔ ወር 2002 ዓም ከወጪ የመጣ ባለሃብት ወደ አካባቢው ትራክተር ይዞ በሜድ ነዋሪዎቹ ያበቀሉትን ማሽላ በማነብሰብ እና አካባቢውን በመመንጠር ሩዝ ለማምረት ይዞታውን ማዘጋጀት ጀመረ፡፡[118] 1ሺህ 500 ሔክታር ወደሚገመተው የሜት ይዞታ ላይ ይኸው ባለሃብት ይዞ የመጣው የጥበቃ ጓድ ቡድን ቦታውን በመቆጣጠር ነዋሪ ገበሬዎቹ ቦታውን አቋርጠው በወንዙ ዙሪያ ወደሚገኘው የሜት ይዞታቸው እንዳይሄዱ ከልክሏቸዋል፡፡ በመቀጠልም በቦታው ላይ የሚገኘውን ደን የማጠሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ይኸው ድርጊት በወንዙ ዙሪያ የሚገኙት የሜት ይዞታዎችን ይወሰዳሉ የሚል ስጋትም እንዲኖር አድርጓል፡፡

> "ምን ማድረግ እንዳለብን አናወቅም፡፡ እነዚህ ሰብሎች በሕይወት ለመኖር በጣም አስፈላጊያችን ናቸው፡፡ የወደፊቱ ሁኔታ እንዲሁም ራሳችንን እንዴት ልንመግብ እንደምንችል ስናስብ እንጨነቃለን፡፡"
>
> በጋምቤላ የአንድ መንደር ሽማግሌ[119]

የትውልድ ቦታ ወይም እትብት የተቀበረበት በሚል ተለይተው የሚከለሉ ቦታዎችም ሆኑ ለእንደነዚህ ዓይነት ቦታዎች ዕውቅና የሚሰጥ አሰራር የለም፡፡ ነዋሪዎች ከመኖሪያቸው ሲፈናቀሉ ማንም አማክሯቸው አይደለም፤ ካሣ (የገንዘብም ሆነ የዓይነት) ፈጽሞ አይታሰብላቸውም፡፡ ከመኖሪያቸው አቅራቢያ ለእርሻ የሚሆን ሜት የለም፡፡ በሜጨረሻም ከወረዳው ባለሥልጣናት የሚነገራቸው ነገር ቢኖር ተበታትነው የሚኖሩ በመሆናቸው በአዲሱ የመንደር ምስረታ መርሃግብር መሠረት መሰሰው እንደሚሰፍሩ ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዝናቡ ሁኔታ እየተዘበራረቀ ከሜዱና ጎርፍ አካባቢውን እያጠቃው ባለበት ባሁኑ ሁኔታ የእነዚህ ነዋሪዎች በምግብ ራሳቸውን የመመገባቸው ሁኔታ ችግር ላይ ወድቋል፡፡ እንደ አሜራጭ

የሚጠቀሙባቸው መንገዶችም (እንደ አሣ ማጥመድ፣ የደን ሃብት፣ የበቆሎና የማሽላ ምርት) ካለው ነባራዊ ችግር ጋር ተዳምረው በምግብ ራሳቸውን የመቻላቸውን ሁኔታ አደጋ ላይ መጣል ብቻ ሳይሆን እንዳይኖር እያደረገ ነው፡፡ በተለይም ከመኖሪያቸው ጋር ተያይዞ የእርሻ መሬት በሌለበት ሁኔታ ተጨማሪ አዳዲስ ሰፋሪዎች ማምጣታቸው ችግሩ እጅግ የከፋ አድርጎታል ወደፊትም እያደረገው ይሄዳል፡፡

የመሬት ይዞታን ለንግድ ተግባር ማዋል በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረገው አሠራር ላይ ሁኔታው በተለይ በምግብ ራሳቸውን ባልቻሉ ማኅበረሰቦች ዘንድ መካከል አስከፊ ተጽዕኖ እንደሚያደርስ ይታወቃል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን ከተመለከታቸው የሊዝ ስምምነቶች መካከል በአንዱ እንኳን ባለሃብቱ ምርቱን በማስደግ የነዋሪወን ሕዝብ የምግብ ዋስትና ያሻሻል የሚል አንቀጽ አለመኖሩን ለመታዘብ ችሏል፡፡ እንዲያውም የፌደራሉ መንግሥት የወጪ ምንዛሪ ከሚፈለጉ የተነሣ ባለሃብቶች የገንዘብ ሰብል የተባሉትን ወደወጪ ተልከው የወጪ ምንዛሪ ሊያስገኙ የሚችሉትን ዓይነት ሰብሎች እንዲያመርቱ ነው ማበረታቻ የሚሰጠው፡፡ የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) ቃልአቀባይ ለዚህ የጥናት ቡድን ሲናገሩ "ከበቂ በላይ በቆሎ በአገሪቷ ወስጥ አለን፤ ከዚህ ተጨማሪ አንፈልግም" ብለዋል፡፡

የግብርና ሚኒስትር የሆኑት አቶ አበራ ደረሰ ከመንግሥት ተወካዮች በአብዛኛው የሚሰማውን አስተያየት በዚህ መልኩ ያስቀምጡታል፡- "ገንዘብ ካለን ምግብ ከየትም መግዛት እንችላለን፡፡ ከዚያም ችግራችንን መፍትሔ አገኘ ማለት ነው"[120] ብለዋል፡፡ ከዚህ በፊት በዕርዳታ የሚመጣውን ገንዘብ መንግሥት በኅብረተሰቡ መካከል በማከፋፈል ሥርዓቱን የሚደግፉ ግለሰቦችን በእጁ ሥር ለማስገባት ይጠቀምበታል (ሰው ይገዛበታል) እየተባለ ሲነገር የቆየ አስተሳሰብ አለ፡፡[121] እህል ከዓለምአቀፍ ገበያ በመግዛት መሬት ለሌላቸው ደሃ ገበሬዎች ማከፋፈል የትናንሽ እርሻ ገበሬዎች ራሳቸውን ለመቻል ከሚያደርጉት ጥረት ጋር ሲነጻጸር የምግብ ዋስትናን በምንም መልኩ አያሻሽልም፡፡ የግብርና ልማት ሞ

**ደመወዝ እና የቀን ሠራተኛ ፍልሰት**

የማጠነ-ሰፊ ንግድ ተኮር የግብርና ተግባር ዋንኛው ጥቅም ለበርካታ ሰዎች በሥራ የመሠማራት ዕድል ማከፈቱ ነው፡፡ ለምሳሌ ካሩቱሪ ከ20ሺህ እስከ 30ሺህ ሠራተኞችን፣[122] ሳውዲ ስታር ደግሞ ከ4ሺህ እስከ 5ሺህ ኢንዱስትራላይዜሽን (ADLI) በረጅም ዕቅድ የምግብ ዋስትናን በሚጨምር ደህነትን እቀንሳለሁ ቢልም አሁኑ የመሬት ይዞታ ኢንቨስትመንት በሚከሄድባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ነዋሪዎች በተለይም ከመሬት ሽያጩ ጋር በተያያዘ በሌሎች የአካባቢው ግፊቶች ተጽዕኖ ሲደርስባቸው በአጭርና መካከለኛ ጊዜያት ወስጥ በከፍተኛ ሁኔታ በምግብ እጥረት እንደሚጠቁ የታመነ ነው፡፡

## 3.3 የማኅበራዊ፣ ምጣኔሃብታዊ እና ባሕላዊ ተጽኖዎች

በአሁኑ ጊዜ ባለሃብቶች በተረከቧቸው የመሬት ይዞታዎች ላይ ማጠነሰፊ እንቅስቃሴ ባለመጀመራቸው አሁን እየተካሄደ ያለው የመሬት ኢንቨስትመንት የሚያስከትለው ማኅበራዊ ተጽዕኖ ወደፊት ግልጽ እየሆነ የሚሄድ ነው፡፡ እነዚህ ተጽዕኖዎች በነዋሪዎች ላይ የሚያስከትሉት ውጤትና ጥልቀት የሚከተሉት ነጥቦች በሚታወቃቸው ሁኔታ ላይ ጥገኛ ነው፡፡ እነዚህም፡- ተገቢ የሆነና ከሊዙ ስምምነት በፊት በሚደረግ የማኅበራዊ እና አካባቢያዊ ተጽዕኖ ግምገማ (SIA, EIA) እና ይህንንም ተከትሎ በሚከናወኑ ተከታታይ የልማትና ትግበራ ክንወኖች፣ በአሁኑ ጊዜ ያሉት ሕጎች በሥራ ላይ በመዋላቸውና በመከበራቸው፣ በባለሃብቶች፣ መንግሥት እንዲሁም የአካባቢው ማኅበረሰብ ለመተባበር ባላቸው ፍላጎትና ስለ ጉዳዩ ባያላቸው ዕወቀት ላይ ጥገኛ ነው፡፡

የሚያሳዝነው ነገር የተጽዕኖው ግምገማ ደካማ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የወጡ ሕጎችን የማስከበሩ ተግባር በጣም የላላ ከመሆን አልፎ ከመኖርም የሚቆጠር አይደለም፡፡ በአብዛኛው የማኅበራዊ ተጽዕኖ ወዲያውኑ የሚታይ ነው (መሬት ሲነጠቅ የሚሰማ ስሜት በመሆኑ)፡፡ ይህም ተጽዕኖ የሚይጠበንና ረጅም ጊዜ የሚወስድ ከመሆኑ አኳያ የኅብረተሰቡን ባሕልና መተዳደሪያ የሚያወድም ነው፡፡

ሠራተኞች እንደሚያስፈልጋቸው ጠቁመዋል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን የተመለከታቸው 500ሔክታር ስፋት ያላቸው ትናንሽ የሰሊጥ እርሻዎች እስከ 900 ሠራተኞችን ቀጥረው ያሠራሉ፡፡ (አብዛኞዎቹ ግን ጊዜ ወቅቱን ጠብቀው የሚከሰቱ የሥራ ዕድሎች ናቸው) ከእነዚህ ሥራዎች

በርካታዎቹ የቀንበላ ሥራ ሲሆኑ የደመወዙ ሁኔታም ዝቅተኛና ለአጭር ጊዜ የሚቆይ እንዲሁም ወቅቱን ጠብቆ የሚከሰት ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ቁጥሮች ልክ ሠራተኞች ቢቀጠሩም ተጨባጭ የሥራ ፈጠራን እና የአካባቢ ልማትን በተማለከተ እነዚህ አኻዞች የተዛባ ሚዛንን ነው የሚሰጡት፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በርካታ ሠራተኞች በተለይም ወንዶች ከሌሎች የአገሪቷ ክፍል በሚፈልሱበት ወቅት ከዚያው ጋር ተያይዞ በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ የሚያስከትለው የከፋ ተጽዕኖ አለ፡፡ በጋምቤላም ሆነ በቤንሻንጉል ነዋሪዎች ዘንድ ያለው ስጋት እነዚህ ሰፋሪዎች የሚከናወኑት ሥራ ወቅቱን ጠብቆ ከተጠናቀቀ በኋላ ወደማጡበት ከመመለስ ይልቅ እዚያው በመቆየት መሬት በመውሰድ፣ ልጆቻቸውን እና ቤተባቸውን በማምጣት በመሬት ኃብት አጠቃቀም ላይ የሚከሰተውን ተጽዕኖ ይበልጥ የከፋ ያደርጉታል የሚል ነው፡፡ እንዲሁም ሌላው ስጋት ማጠዎቹ በአካባቢው ስላለው የኑሮ ዘይቤ እምብዛም ደንታ ስለማይኖራቸው ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ (ለቤት ማሥሪያ፣ ለማገዶ እና ለከሰል) አካባቢውን ስለሚመነጥሩ የአገሬውም ነዋሪ ይህንኑ ተግባር በማከተል የምንጣሮ ተግባሩን ይቀጥልበታል የሚል ነው፡፡ እነዚህን ተቀጣጣይነት ያላቸውን ክስተቶች በአሁኑ ጊዜ የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ በግልጽ ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ቢሆንም ባለፉት ጊዜያት በዚህ ዙሪያ በኢትዮጵያ የተደረጉት የልማት ክንውኖች እንደዚህ ዓይነቱን ጽንሰሃሳብ ትክክለኛነት የሚያጎላና የነዋሪውንም ስጋት የሚያጠናክር ነው፡፡ (የሚጃንጀር ታሪክ የሚለውን ሣጥን "ሸ" ይመልከቱ)

በርካታ ሠራተኞች ወደ አካባቢው በመፍለሳቸው ምክንያት ስለሚከሰተው የማኅበራዊ ተጽዕኖ በበቂ ማስረጃ መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህም፦ የደን ጭፍጨፋ መጨመር፣ የዓሣ ኃብት መቀነስ፣ የዱር አራዊት እና ሌሎች የአካባቢው ኃብቶች ማሽቆልቆል፣ ከአካባቢው ነዋሪ ጋር የሚከሰት ግጭት፣ ከወሲብ ጋር የተያያዙ ጥቃቶች ማሻቀብ፣ በመሠረተልማቶች ላይ የሚከሰት ጫና፣ የሴተኛአዳሪነት መስፋፋት (በተያያዥም የአባላዘርና የኤይድስ በሽታ መስራጨት) እና የስነምህዳሩ ሥርዓት (የውሃ ኃብትንም ጨምሮ) መጨናነቅ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህን ተጽዕኖዎችን ለመቆጣጠር ከግሉም ሆነ ከመንግሥት በኩል የሚደረግ በማስረጃ የተረጋገጠ አንዳችም ጥረት እንደሌለ ይህ የጥናት ቡድን ተገንዝቧል፡፡



ደኑ በካሩቱሪ ቡልዶዘር ተጨፍጭፎና የሚቃጠለውም ተቃጥሎ“ለልማት” የዋለ ሜዴት በአሊያ፤ ኢታንግ አካባቢ

## ሣጥን ሸ፡ - የሜጀንጀር ታሪክ (አባንግ)

ቁጥራቸው ጥቂት የሆኑና የተገለሉ ሕዝቦች አካባቢ ስለ ማጠነ ሰፊ ንግድ ተኮር እርሻና የሠራተኛ ፍልሰት ሲከሰት የሚሆነውን ለማወቅ የሜጀንጀርን ታሪክ መሜልከቱ ጠቃሚ ማገለጫ ይሰጣል፡፡ የሜጀንግ ሕዝቦች ቁጥራቸው ከ15ሺህ እስከ 24ሺህ የሚደርስ ሲሆን የሚኖሩትም በገላጣው የአኙዋኮች ምድርና በደጋማው ክልል ጣካከል ጥቅጥቅ ባለው ደቡብ ምዕራብ የኢትዮጵያ አምባ ጦርዝ ላይ ነው፡፡ በአኗኗር ሁኔታቸው ከአካባቢያቸው ጋር በእጅጉ የተላመዱ ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው ለየት ያለም ነው፡፡ የሜጀንግ ሕዝቦች አራሽ ገበሬዎች ሲሆኑ የማኅበረሰባቸው አወቃቀር ያልተወሳሰበ እና ለቀቅ ያለ ነው፡፡ በአካባቢው ሥልጣን ያለው አካል ሥርዓትን የሚያስከብሩ ወሱን ሥልጣን ያላቸው ሽማግሌዎች ከመሆናቸው በስተቀር የፖለቲካ ሚዎች የሏቸውም፡፡ አሰባጥሮ ሚዚስ፣ የንብ ዕርባታ፣ እና ዓሣ ማጥመድ ዋንኞቹ መተዳደሪያቸው ናቸው፡፡

በደርግ ዘመን በአካባቢው ማጠነ ሰፊ የሆነ የመንግሥት እርሻ ላይ ቡና ይመረት ነበር፡፡ ይህንንም ለማከናወን ምንጣሮ ተካሂዶና ነዋሪው ተፈናቅሎ ነበር፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ የሜል አገር ሰዎችም በየእርሻው በቀን ሠራተኛነት ለማሥራት ከፈለሱ በኋላ በርካታ ለሜልማት የሚቻል የሜሬት ይዞታ በመኖሩ እንዲሁም ጥለውት ከማጠበት ቦታ የተሻለ አገልግሎት የሚኪጥ በመሆኑ ሥራቸው ቢጠናቀቅም እዚያው ኑሯቸውን ቀጥለዋል፡፡ አብዛኞዎቹ በእርሻዎቹ ጦርዝ ዙሪያ ሜሬት በመውሰድ ነበር የሰፈሩት፡፡ ከእነዚህ የሜሬት ይዞታዎች አንዳንዶቹ ማንም ያልሰፈረባቸው ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ከሌላ ቦታ ተፈናቅለው በማጡ የሜጀንጅ ሰዎች የሰፈሩባቸው ነበሩ፡፡ በአብዛኛው ግን የሜሬት ይዞታው ከሜጀንጂር ሰዎች የተገዛ ሊሆን የቻለበት ምክንያት እነዚህ ሕዝቦች ሜሬት ወሱንነት የሌለው ኃብት ነው የሚል አጣካከት ያላቸው በመሆኑና ሜሬት ለመሸጥ ደስተኞች በመሆናቸው ነበር፡፡ ይህም እየቀጠለ በሜዴዱ ሜጀንጂሮች ሜሬቱን እያጸዱ ሲሸጡና ራሳቸውንም ወደ ህዝብ ወደ አልሰፈረባቸው ቦታዎች ሲገፉ ደገኞችም እየተከተሉ ሲገዙ ቤተሰቦቻቸውም ይህንኑ ሲቀጥሉ ቆይቷል፡፡ በእያንዳንዱ ደረጃ፣ ት/ቤቶች፣ ክሊኒኮችና ሌሎች የአገልግሎት ተቋማት በመንግሥት እየተከፈቱ ሲሄድ ሜጀንጂሮችም አገልግሎት ወደሚደርስባቸው ቦታዎች እየተገፉ ሄደዋል፡፡ በዚህም በሃብታም ደገኞችና በደሃ የአገሬው ተወላጅ ጣካከል ያለው ክፍተት እየሰፋ ሄዷል፡፡

አሁን ግን ከ25ዓመታት በኋላ ሜጀንጂሮች በአደገኛ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡ በፊት እነርሱ ይኖሩባቸው የነበሩ ቦታዎች አሁንም በሜጀንጂር ስም የሚጠሩ ቢሆንም በቦታው ላይ ግን አንድም የሜጀንጂር ቤተሰብ የሚኖርባቸው ሆነዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ሕዝቦች በመንደር ምስረታና ቦታቸው ማጠነ ሰፊ ለሆኑ ንግድ ተኮር የእርሻ ኢንቨስትመንት እየዋለ በማምጣቱ ለተጨማሪ አደጋ ተጋልጠዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሜጀንጂሮች ሰፍረው የሚገኙት የጋምቤላን

ክልል አቋርጠው በሚያልፉ የአምስት ወንዞች ምንጭ አካባቢ በመሆኑ ይህንኑ አካባቢ ለሚልማት ከግብርና ባለሃብቶች ዘንድ እየቀረበ ያለው ተጽዕኖ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች እየተካሄደ ስላለው የሜሬት ኢንቨስትመንት እንዲሁም የምንጣሮው ሁኔታ በሜጃንጀር ሕዝብ ላይ ብቻ ሣይሆን በአጠቃላይ የጋምቤላ ክልል ሊያስከትል የሚችለውን አስከፊ ቀውስ እንዲሁም በክልሉ የእርሻ ተግባራዊነትን በተመለከተ የክልሉ ማስተዳድር ያለውን ስጋት እየገለጸ ይገኛል፡፡ በዚህም ምክንያት የተወሰኑትን አካባቢዎች የተከለሉ እንዲሆኑ (“የተጠበቀ የደን ኃብት” በሚል ስያሜ) ጥረት ሚድረግ የተጀመረ ሲሆን ይህም በምንጮች የተከበበውን ደን በመሸፈን የጋምቤላን ታላላቅ ወንዞች ለመከላከልና ፍሰታቸው እንዳያቋርጥ በሚድረግ የክልሉን ሕይወት ለበርካታ ሺህ ዓመታት በማቆየት ረገድ የወሃ ኃብትን በማለገስ የሚያከናወኑትን ተግባር እንዲቀጥሉ ለሚድረግ ነው፡፡

ይህ እንግዲህ በኢትዮጵያ ወስጥ አገር በቀል ተወላጆች በሚኖሩበት በአንድ ትንሽ ቡድን ወስጥ እየተከሰተ ያለ እውነታ ሲሆን ልክ እንደነዚህ ነዋሪዎች ሁሉ ሌሎችም በሜሬት ይዞታቸው፣ በማንነታቸው ላይና በመኖር ኅልወናቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የደረሰባቸው አሁንም እየደረሰባቸው ያሉና ወደፊትም የሚደርስባቸው ሌሎች በርካታ ማኅበረሰቦች አሉ፡፡

## <u>ሣጥን ቀ፡ የሚልሶ ማስፈር ታሪክ</u>

በቅርብ ዓመታት በኢትዮጵያ ከተከሰቱት ሁኔታዎች ማካከል በጣም አጨቃጫቂ የሆነው የሚልሶ ማስፈር ሂደት ሲሆን ይህም ሰዎችን እጅግ ከተጨናነቀ፣ የምግብ እጥረት ካለባቸው የደጋ ቦታዎች ዘርዘር ያሉ ለም ቦታዎች በስፋት ወደሚገኙባቸው አካባቢዎች ማስፈር ማለት ነው፡፡

በዘመነ ደርግ ማጠነሰፊ የሆነ የሚልሶ ማስፈር ተግባር የተፈጸመ ሲሆን በወቅቱም 38ሺህ አባወራዎችን ሚልሶ የማስፈሩ ሁኔታ በ1967 እና 1968 ተከናወኗል፡፡ በመቀጠልም በ1976ዓም ድርቅ ከሚያጠቃቸው የሰሜን ክልሎች 1.5 ሚሊዮን ሰዎችን ወደ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ የማስፈር ማጠነሰፊ ዕቅድ ማያዙን መንግሥት አስታወቀ፡፡ 250ሺህዎቹ ወደ ወለጋ፣ 150ሺህዎቹ ወደ ጋምቤላ እንዲሁም 100ሺህዎቹ ወደ ጎጃም ክፍላተ ሃገራት ሄዱ፡፡

እንዲህ ያለውን ምኞታዊ ዕቅድ ተግባራዊ ለሚድረግ የገንዘብ ዓቅም የለውም የሚል ዓለምአቀፍ ወቀሳ ትችት በመንግሥት ላይ ማነንዘር ጀመረ፡፡ ሌሎች ደግሞ ከሚልሶ ማስፈሩ በስተጀርባ ድብቅ የፖለቲካ ዓላማ የማካካት ዕቅድ አለ ሲሉ በርካታዎች ደግሞ ቤተሰቦችን በማያየት የሚፈጸመው ድርጊት የሰብዓዊ መብትን የሚጥስ ነው በማለት ያላቸውን ስጋት ማሰማት ጀመሩ፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ከሰፋሪዎቹም ሆነ ሰፈራው በሚካሄደበት ከሚኖሩ ጋር የተደረገ ምንም ዓይነት ምክክር አልነበረም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የሚልሶ ማስፈሩ ዕቅድ የተሳካ አልነበረም፤ ብዙዎች በወባና ሌሎች በሽታዎች ሲሞቱ ሌሎች ደግሞ ወደ ቀያቸው ተሚለሰው ሄደዋል፡፡ የተቀሩት በርካታዎች ግን አዲሱን ኑሯቸውን ገፍተወበታል፡፡ በሚልሶ ማስፈሩ ሂደት ወስጥ በአዲሶቹ ሰፋሪዎችና በቀደምት ነዋሪዎቹ ማካከል ያላቋረጠ ግጭት ሲከሰት ቆይቷል፡፡

በ1970ዎቹ አጋማሽ መንግሥት “የመንደር ምስረታ” በሚል አዲስ የሚልሶ ማስፈር ሮሃግብር የጀመረ ሲሆን ይህም ተበታትነወና በእርሻ ተግባር ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ማኅበረሰቦችን ቋሚ ወደሆኑ መንደሮች ማስባሰብ ነበር፡፡ የዚህም ዋና ጥቅም ፈጣን አገልግሎት ለማቅረብ፣ የሜሬት ይዞታ አጠቃቀምን ለማሻሻልና የተፈጥሮ ኃብት ጥበቃ ለሚድረግ ነበር፡፡ በመጋቢት ወር 1978ዓም 4.6 ሚሊዮን ሰዎች ከ4,500 በሚበልጡ መንደሮች ሚልሰው እንዲቋቋሙ ተደረገ፡፡ ዓለምአቀፉ ትችትና ወቀሳም የዚያኑ ያክል ጠንክሮ በተለይም ሚልሶ ሚቋቋሙ የተካሄደበትን ጊዜ (የእርሻ ምርት ሚቋረጡ)፣ የመንግሥት ዓቅም፣ የበሽታና ተባይ ማስራጨት እንዲሁም የደኅንነት ዋስትናው ማሽቆልቆሉ ከትችቶቹ ጋር አብረው የተጠቀሱ ናቸው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች አንጻር ዓቅም ሳይኖርና ዕቅድ ሳይደረግ በፖለቲካ ዓላማ ብቻ በማሳሳት የሚልሶ ሚቋቋም ሆነ የመንደር ምስረታ ጥረትና ተግባራዊነት በአካባቢው ነዋሪ ላይ ዘላቂና አስከፊ ተጽዕኖ ሚድረጉ አይቀሬ ነው፡፡ የአገሬው ነዋሪ ወደ ክልሉ እየፈለሱ የማጡ ሰፋሪዎች ያደረሱትን

ተጽዕኖ እና የኑሮ ቀውስ እስካሁን እያነሱ ያወሳሉ፡፡ ስለሆነም ወደፊት ንግድ ተኮር እርሻዎች ላይ ለሙምሬት ከማል አገር የሚፈልሰው ሕዝብ ልክ እንደበፊቱ ተመሳሳይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል የሚል ፍርሃት ይኖራል፡፡ የማንደር ምስረታው ጽንሰሃሳብ በአሁኑ ጊዜ እንደገና እያንሰራራ ሲሆን ዕቅዱም ተግባራዊ እየሆነ ያለው ማጠነሰፊ የሜሬት ኢንቨስትመንት በሚኪሄደበት ተመሳሳይ ቦታዎች ላይ ነው፡፡

## የግጭት መባባስ

**"እኛ ከማጡዎቹ ጋር ላሁኑ ምንም ግጭት የለንም፡፡ ሆኖም ግን ግጭቱ እየመጣ ነው ማለት ይቻላል፤ ይህም ግጭት ደግሞ ከሜሬት ይዞታ ጉዳይና ተገቢውን ክብር ከማጣት ጋር የተያያዘ ይሆናል፡፡"**

በቤንሻንጉል ከሚኙ የአገር ሽማግሌዎች አንዱ ከደጋማው የማል አገር እየፈለሱ ስለሚጣጡ ሠራተኞች ከተናገሩት[123]

የሕዝብ ብዛት እየጨመረ ሲመጣ የሜሬት ኃብት ስለሚቀንስ ግጭቶች የሚከሰታቸው ሁኔታ እጅግ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ የተደረገ ጥናት እንደሚያመለከተው ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ሲኖር የሕዝብ ዝወውር፣ የተፈጥሮ ኃብት መሟጠጥ፣ በየማኀበረሰቡ ወስጥ ያለው ልዩነት ማለትም በሃብትና በዘር ማስፋት፣ የኢኮኖሚ ድቀትና ለወድቀት መጋለጥ፣ በተፈጥሮ ኃብት ዙሪያ እንዲሁም የሚነሱ ግጭቶችን ለማስተዳደር የሚችሉ ተቋማት ማነስ፣ ደካማ የአስተዳደርና የሕግ አሰራር፣ በክልሎች አካባቢ የፖለቲካ አለሚረጋጋትና ጸጥታ ማነስ እንደሚከሰት አንድ ጥናት ጠቁሟል፡፡[124] አሁን በሊዝ እየተሸጡ በሚገኙት ቦታዎች እነዚህ ሁሉ እየተከሰቱ ይገኛል፡፡ በዚህ ከሜሬት ጋር በተያያዘ በሚደረግ ኢንቨስትመንት በተለያዩ ቦታዎች በርካታ ግጭቶች፣ ወከባ እና እስራት በኢትዮጵያ እየተከሰተና የዜና አወታሮችም እየዘገቡ ይገኛል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን እነዚህን ክስተቶች በቀጥታ የተመለከተበት ሁኔታ ባይኖርም በርካታ ማኀበረሰቦች "የመታሰር ማስፈራሪያ" እየደረሰባቸው በመሆኑ ከሜሬት ጋር በተያያዘ የሚገጥማቸውን ችግር ወደ በላይ አካል ከማሰማት የሚቆጠቡት በዚህ ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከመንግሥት በኩል በሚደርስባቸው ተጽዕኖ እና ማስፈራሪያ ምክንያት በተለያየ አካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎች ከዚህ የጥናት ቡድን ጋር ለመነጋገር እንደሚፈሩ ያሳወቁ ጥቂቶች አይደሉም፡፡



የአልዌሮ ወንዝ በ1980ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ተገድቦ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ሳወዲ ስታር ለእርሻው ሊገድበው አቅዷል

## የባሕላዊ ማንነት መጥፋት

ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የመሬት ይዞታ ማለት ሸቀጥ ሳይሆን የማንነታቸው ማለያ በመሆኑ በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ አይደለም፡፡ (ለዝርዝር ማብራሪያ ሣጥን "በ"ን ይመልከቱ) ስለዚህ የመሬት ይዞታን ወይም የእርሻ፣ በጎብረት የመኖሪያ፣ የግጦሽ፣ ወይም የሃይማኖትና የባሕል ቦታዎችን ማጣት በነዋሪው ሕዝብ ላይ የምግብ ዋስትናን፣ የማንነትን ማለያ፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን በከፍተኛ ሁኔታ ይጎዳል፡፡

### ሣጥን በ፡ የመሬት ይዞታ በጋምቤላ ለሚኙት አኙዋኮች ያለው ትርጉም

በኢትዮጵያ በተለያየ ቦታ ለሚኙ ቀደምት ነዋሪዎች የመሬት ይዞታ ያለውን ትርጉም ማንም ከውጪ የመጣ ሰው ሊረዳው የሚችል አይደለም፡፡ ምክንያቱም መሬት ማለት የኢኮኖሚ ኃብት ወይም የምግብ ማምረቻ ቦታ ማለት ብቻ አይደለም፡፡ ከነዋሪዎቹና በአጠቃላይ ከማኅበረሰቡ ያለፈ፣ ከአሁንና ከወደፊት ማንነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ስለ መሬት አስፈላጊነት አንድ የአኙዋክ አዛውንት የሚከተለውን ብለዋል፡ –

"በየመንደሩ የሚኖር ሁሉ የራሱን ድንበር በተለምዶ የት ድረስ እንደተሰመረ ያውቃል፡፡ የሁሉም ሰው ድንበር የተከበረ ነው ምክንያቱም ሰዎች የአያት ቅድመ አያታቸውን መናፍስት ይፈራሉና፡፡ በርካታ አኙዋኮች ከመኖሪያ ቦታቸው ወጪ ሲሞቱ ሬሳቸው ወደ ትውልድ ቦታቸው መጥቶ እንዲቀበር ይፈልጋሉ፡፡ መሬት ታሪካዊ፣ ስሜታዊ፣ መንፈሳዊና ፖለቲካዊ እሴቶችን ያዘለ በመሆኑ እንደዚህ ዓይነት የመሬት ይዞታዎች ሲወሰዱ ወይም ሲወረሩ ድርጊቱ የተፈጸመው በሌሎች አኙዋኮች እንኳን ቢሆን ጦርነት መጫሩ አይቀርም፡፡ ምክንያቱም በቦታው ላይ የሚኖሩት ሰዎች ራሳቸውን የተናቁና የተዋረዱ አድርገው ስለሚቆጥሩ ስለ መሬት ይዞታቸው ሲሉ ለመሞት ቆርጠው ይነሳሉ፡፡ የየትኛውም መንደር ነዋሪ አሰባጥሮ የሚዋርስ እንኳን ቢሆን ወደ ሌላ የመሬት ይዞታ ሄዶ ከዚያ ካሉት መንደረተኞች ጋር ተገቢውን ምክክር ሳያደርግ በሰው መሬት ላይ ምንም ሚድረግ አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ ደን ብቻ ማለት አይደለም፤ የድንበር ማካለያው በታሪክ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በመሆኑ የማን ድንበር የት ድረስ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ለዚህም ነው መሬት ማለት የኢኮኖሚ ጥቅም ማግኛ ብቻ ሳይሆን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ መንፈሳዊና ስሜታዊ እሴቶችን ያዘለ ነው የተባለው፡፡"

" . . . እንደየመንደሩ ሁኔታ መሬት ለእርሻ (በራስ ክልል ወስጥ አሰባጥሮ ለሚዘስ በሌሎች መንደሮች ግን ምክክር ሳያደርጉና ፈቃድ ሳያገኙ ምንም አለሚድረግ)፣ ዓሣ ለማጥመድ (ወንዞችንና ኩሬዎችን በመጠቀም)፣ ለም አፈሩ ቋሚ ግብርና ለማከናወኛ፣ ለአደን (ደዋር ተብለው ይጠራሉ) እንዲሁም ግጭት በሚከሰትበት ጊዜ ለደኅንነትና ከጠላት ለማሸሽ (ጥቅጥቅ ያለው ደን) የማስሉ አገልግሎቶች ላይ መዋል ይችላል፡፡ እነዚህ ቦታዎች ሁሉ የተከበሩ ናቸው፡፡ እንዲያውም አንዳንድ አካባቢዎች የአምልኮ ዛፎችም አሏቸው፡፡"

በፊት በደን ተሸፍኖ የነበረ ቦታ በኋላ ግን በአንድ የአገር ወስጥ ባለሃብት ተመንጥሮ የጸዳ ቦታን ይህ የጥናት ቡድን ተመልክቷል፡፡ መንደረተኞቹ ዶዘር መጥቶ እሲኪያጓራባቸው ድረስ እየሆነ ስለነበረው ጉዳይ ምንም የሚያውቁት አልነበረም፡፡ የመንደሩ ሽማግሌዎችም እየተገነደሱ የወደቁት ዛፎች የነበራቸውን የተለያየ ጥቅም ለዚህ ቡድን አስረድተዋል፡፡ በአጠቃላይ የበርካታ ዛፎችና ተክሎች ጥቅም ለቡድኑ የተብራራለት ሲሆን ይህም ጥቅም

ለምግብነት ከማገልገል ጀምሮ እስከ መድሃኒትነት እንዲሁም ለቤት ማሪያነትና ለማኅፈሳዊና አምልኳዊ አገልግሎታቸው በዝርዝር ለዚህ የጥናት ቡድን ተነግሮታል፡፡ እንዲሁም ጃርዲያ ተቅማጥ፣ ቢጫ ወባ፣ በሊሃርዚያ፣ ሾር የሰደደ ተቅማጥ እና የመሳሰሉ በአካባቢው የተለመዱ የበሽታ ዓይነቶችን የሚያድኑ ተክሎችና የዛፍ ዓይነቶች ይህ የጥናት ቡድን እንዲያወቅ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ድርቅና የምግብ እጥረት ሲኖር

ለምግብነት የሚውሉ የተለያዩ የፍራፍሬ፣ የለውዝ፣ የተክል እንዲሁም የጅብጥላ ዓይነቶች ለዚህ ቡድን የተገለጸለት ሲሆን በተጨማሪም ከደን ወስጥ የተለያዩ ዛፍ ዓይነቶች፣ ለማገዶነት የሚውሉ እንዲሁም ለጎጆና ለጀልባ መሥሪያነት የሚያገለግሉትን ሁሉ ተመልክቷል፡፡ ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ የደን መኖር ያለው ጥቅምም ለቡድኑ ተነግሮታል፡-

"ጦርነት በሚከሰትበት ጊዜ ልጆቻችንን ለመደበቅ ጫካውንና ደኑን እንጠቀምበታል፡፡ ሆኖም ይህ ጫካ ከተመነጠረ በኋላ ስለ ወደፊታችን በማሰብ እንጨነቃለን" በማለት ከመንደሮቹ በአንዱ የሚኖሩና ሜዳቸው በቅርቡ በወጪ ባለሃብት የተመነጠረ አዛውንት ተናግረዋል፡፡

ይህ የጥናት ቡድን በጎበኛቸው የቤንሻንጉል፣ የኦሮሚያና የጋምቤላ ክልሎች የዛፎች ጥቅምና የሚሰጡት አገልግሎት በተለይም ባሕላዊውን እና መንፈሳዊውን እሴታቸው እንዲገነዘብ ተደርጓል፡፡ ሆኖም አሁን እየተካሄደ ካለው ንግድ ተኮር የግብርና ተግባራት አኳያ ለክስቱ የሚችሉትን ችግሮች አስቀድሞ ለመከላከል ምንም ዓይነት ጥረት ሲካሄድ አልተመለከተም፡

አንድ ሌላ አዛውንት እንዳሉት፡-

"አንድ ትግሬ ባለሃብት ወደ አካባቢያችን መጥቶ አሁን ቦታው የእርሱ ስለሆነ አካባቢያችንን እንድንለቅ ነገረን፡፡ እኛም 'ይህ ሜዳችን ስለሆነ በጭራሽ አይሆንም' አልን፡፡ እርሱም መልሶ ፈጽሞ አሁን ይህ የኔ ሜዳ ሆኗል ለቅቃችሁ የማትሄዱ ከሆነ ትታሰራላችሁ አለን፡፡ እኛም 'ሂድና አሰረን፤ ይህ እንደሆነ የእኛ ሜዳ ነው' አልነው፡፡ ከዚያም እርሱ ትቶን ሄደ፡፡ ቀጥሎም የብሔራዊ ፓርክ ሰዎች መጥተው ደኑን ማለካትና ድንበር ማካለል ጀመሩ፡፡ ደኑን ማጠቀማችንን እንድንቀጥል ነገር ግን ተገቢውን እንክብካቤ እንድናደርግና የዱር እንስሳትን እንዳንገድል ነገሩን፡፡ ታዲያ እኛ ምን እናድርግ? ከተለያዩ ሰዎች የሚነገረን የተለያየ ነገር ነው፡፡ እኛ እንደሆነ ደኑን ለምግብነት (ፍራፍሬና የለውዝ ዓይነቶችን ለማግኘት)፣ ለመድሃኒትነት እንዲሁም ለጎጆ ቤታችን ሣር የምናገኝበት ምንጫችን ነው፤ ሕይወታችን ነው፤ ይህንን ካወደሙት የት ሄደን ነው የምንኖረው?

እኒህ አዛውንት ይህንን ታሪክ ሲነግሩን ይኸው ደን ሲመነጠር ባሻገር እየተመለከትን በተለይም ግማሽ ያህሉ በሕንዱ የካሩቱሪ ኩባንያ የተቀረው ግማሽ ደግሞ በአገር ወስጥ ባለሃብተ ሲመነጠር ይህ የጥናት ቡድን እየተመለከተ ነበር፡፡

ይህ የጥናት ቡድን በግልጽ ለሚረዳት እንደቻለው በኢትዮጵያ የሚገኙ ቀደምት ነዋሪዎች ማንነታቸው እንዲሁም ባሕላቸው ከሜዳት፣ ከወንዝ እንዲሁም ከደን ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ዓይነቱ የደን ጭፍጨፋና እትብት የተቀበረበትን ቦታ የሚጽዳት ተግባር በእጅጉ ስሜቱን የሚጎዳ ብቻ ሳይሆን የእነዚህን ነዋሪዎች ማንነትና ሕልውና ከፉኛ አደጋ ላይ የሚጥል ነው፡፡

**የሠራተኞች አስተዳደር (አያያዝ)**

“ለሠራተኞቼ የጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ አደርጋለሁ፤ ይህንንም የሚደርገው ሚልካም ሰው ስለሆንኩ ብቻ ሳይሆን ጥሩ ነጋደም ስለሆንኩ ነው፡፡ የሠራተኞች በሚልካም ማያዝ ለድርጅት ሚልካምነት ወሳኝነት አለው፡፡ ለሠራተኞቼ ልጆች ት/ቤት ማከፈት ትክክለኛ ድርጊት ነው፡፡ እነዚህ ወጣቶች ናቸው የወደፊት ሥራ አስኪያጆች፤ ምናልባትም እኔን ሊተኩኝ ይችላሉ፡፡ እኛ ለወደፊት ጫምር ነው ማዋዕለንዋያችንን እያፈሰስን ያለነው፡፡”

ሳይ ራማክሪሽና ካሩቱሪ፤ የካሩቱሪ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ[125]

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት “ለእርሻ ኢንቨስትመንት የአካባቢ ጥበቃ ልምምድ ሕግ” እያረቀቀ ይገኛል፡፡ ይህ ረቂቅ የሠራተኛ መብትን፣ የትርፍ ሰዓት አከፋፈልን፣ የሳምንት የሥራ ሰዓትን፣ ከሥራ ፈቃድ ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን፣ ሚድልዖ ስላለሚጸም፥ ሴቶች ለተባይ ማጥፊያ ሚድሃኒት እንዳይጋለጡ ስለማከልከል፣ ለእርጉዝ ሴቶች የወሊድ ፈቃድ ስለማስጠት፣ ኤች አይ ቪን ለማከላከል ድጋፍ ስለማስጠት፣ በሥራ ላይ የሚደርስ በደልን ስለማከላከል፣ በሠራተኛ ማኀበር ስለሚደራጀት፣ ዕድሜያቸው ከ18 በታች የሆኑ ልጆች ማስራትን ስለማከልከል፣ እና ስለ ጤና እና ደኅንነት ጥበቃ የሚያጠቃልል ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የአዋጁ ሃሳቦች ከኢትዮጵያ የሠራተኛ አዋጅ 42/1985 ላይ በቀጥታ የተወሰዱ ናቸው፡፡ ሆኖም ሕጉ ገና አለመውጣቱ ብቻ ሳይሆን በሥራ ላይ መዋሉና መተግበሩ ገና የሚይታሰብ ነገር ነው፡፡

በርካታ የየአካባቢው ነዋሪዎች ሚሬት በሊዝ የተረከቡ ባለሃብቶች በአካባቢው ለሚገኙ ተሜሪዎች የትምህርት ቤት ማለዮ አልባሳትን (ዩኒፎርም) እንዲሁም ለየማንደሩ ወሃ እንደሚያቀርቡ ይናገራሉ፡፡ አንድ የአገር ወስጥ ባለሃብት “ወባ ከተነሳ” ወይም በሥራ ላይ አደጋ ከደረሰባቸው ለሠራተኞቹ የጤና ሽፋን እንደሚሰጥ ተናግሯል፡፡ በጋምቤላ ክልል የሚደረገው የስምምነት ሰነድ ላይ ባለሃብቶች ለሠራተኞቻቸው የጤና እና የት/ቤት ፍላጎት ማሟላት እንዳለባቸው ያዛል፡፡ አብዛኛዎቹ ባለሃብቶች ደግሞ ሠራተኞቻቸውን እንደሚመገቡ ይናገራሉ፡፡

**ሣጥን ተ፡ የኢትዮጵያ የአበባ ኢንዱስትሪ**

ከሰኔ 2001ዓም ጀምሮ 251 የወጪ ድርጅቶች በአበባ ምርት ላይ ለማሰማራት ተመዝግበዋል፡፡ ከእነዚህም ወስጥ ስልሳ አንዱ ሥራ የጀመሩ፣ ሃያ አንዱ በትግበራ ሂደት ላይ ማሆናቸው፣ መቶ ሰላሣ አራቱ በቅድመ ትግበራ ሂደት ላይ ማሆናቸው፣ ሰላሣ ስድስቱ ደግሞ ምዝገባቸውን ማሰረዛቸው ሚረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከእነዚህ አበባ አምራቾች ማከከል 95በመቶ የሚሆኑት በ3500 ሔክታር ሚሬት ላይ በኦሮሚያ ክልል ስራቸውን እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ የአበባ ምርትን ወደ ወጪ በመላክ ከአፍሪካ ኢትዮጵያ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ስትገኝ በ2000ዓም ኢትዮጵያ ወደወጪ የላከችው አበባ 150 ሚሊዮን ዶላር ደርሶ ነበር፡፡

ከዚህ የአበባ ምርት ጋር በተያያዘ ለተባይ ማጥፊያና ለማዳበሪያ የሚውለው ንጥረነገር የአካባቢ ብክለት የማምጣቱ፣ የውሃ ጥራት የማባላሸቱ፣ የቆሻሻ ፍሳሽ ለማስወገድ የማስቸገሩ ጉዳዮች አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል፡፡ ንግድ ተኮር የግብርና ኢንቨስትመንትን "በአንድ ማዕከል ለማስተናገድ" እንደተደረገው ሁሉ በአበባ ንግድም የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (EIA) ሳይካሄድ ፈቃድ የማስጠት ሁኔታ ስላለ መንግሥት ይህንን ማስጦር ለማስያዝ ዕቅድ ይዟል፡፡ አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ያደረጉ የአበባ ድርጅቶች 10 ብቻ መሆናቸውን ጠቁሟል፡፡

የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ዋና ኃላፊ የሆኑት አቶ ሰሎሞን ከበደ እያደገ ያለው የአበባ ንግድ ጋር በተያያዘ ሕግና መመሪያ ያለመኖሩን ምክንያቶች ከዚህ እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፡ –

- አሁን እየተሠራባቸው ያሉት ሕግጋት በሚገባው አለመተግበራቸው፤
- መሠረተልማቱን በተመለከተ በቂ ሕግጋት አለመኖር፤
- የአበባ ንግድ የፖለቲካ ድጋፍ ያለው በመሆኑና በአብዛኛው የመንግሥትን አካላት መወስወስ በመቻሉ፤
- ለአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጽ/ቤት ከጉምሩክ፣ ከብድር ማኅበራት፣ ከመሳሰሉት መ/ቤቶች ምንም ዓይነት ጥያቄ አለመቅረቡ፤
- መመሪያና ደንቡን ለማስፈጸም ከመንግሥት አካላት በኩል ተነሳሽነት አለመኖር፤
- መንግሥት ቀጥተኛ የውጪ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት በሚል ሕጉ እንዲላላ ማድረጉ፤

ተጠቃሽ ሊሆኑ የሚችሉ ምክንያቶች ናቸው፡፡ የአበባ ክፍለ ኢኮኖሚውን የሚመራው የኢትዮጵያ የአበባ አምራቾችና ላኪዎች ማኅበር የራሱን ሕግ በ2000ዓም አካባቢ አውጥቷል፡፡ ይህ ሕግ በአብዛኛው የአካባቢና የሠራተኛ ጉዳዮችን፣ የኬሚካል አጠቃቀምና ልምዶችን፣ ቆሻሻ አወጋገድ፣ እንዲሁም የውሃ አጠቃቀምን በሚመለከት የሚያብራራ ነው፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ተገቢውን ተግባር ለሚከተሉና ለሚፈጽሙ የአበባ አምራች ድርጅቶች የወርቅ፣ የብርና የነሐስ የክብር ደረጃዎች ይሰጣል፡፡

ምንጭ Ethiopian floriculture and its impact on the Environment: Regulation, Supervision and Compliance. Mulugeta Getu

**ሣጥን ቸ፡ መንደር ምሥረታና ግዳጅ ሰፈራ**[126]

በኢትዮጵያ የመንደር ምሥረታና ሰፈራ የማስፈር ታሪክ አከራካሪና ከፖለቲካ ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ (ሣጥን ቀ ስለ ታሪካዊ የሚናገረው አለው) በአሁኑ ጊዜም ሂደቱ ንግድ ተኮር የሆኑ ኢንቨስትመንት በሚካሄድባቸው ቦታዎች ላይ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ከክልል ማስተዳድሮች የተገኘው ሚኒስ በጋምቤላና በቤንሻንጉል የሚገኙት ቀደምት ነዋሪዎች በሙሉ (በጋምቤላ ቁጥራቸው 45ሺህ ቤተሰቦች ሲሆን በቤንሻንጉል ደግሞ 90ሺህ ቤተሰብ ናቸው) ዕትብታቸው ከተቀበረበት ቀዬ እየተፈናቀሉ ከ400 እስከ 500 ቤተሰብ ሊኖርባቸው በሚችልባቸው ትናንሽ መንደሮች እያስፈሯቸው ይገኛል፡፡[127] ምንም እንኳን ሚኒስ የተረጋገጠ ባይሆንም የመንደር ምሥረታ ፕሮግራም በደቡብ ሕዝብ እና በአፋር ክልል እየተካሄደ ይገኛል፡፡

በጋምቤላ ክልላዊ ማስተዳደር የሚደረገው የሰፈራ ፕሮግራም በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ቢናገሩም በክልሉ የሚገኙ አንድ መንደረተኛ እንደተናገሩት ግን ማንኛውም የማኅበረሰቡ አባል ወደተባለው ቦታ የማይሄድ ከሆነ "የፌደራል ፖሊስ መጥቶ ወደ እስር ቤት ይወስደዋል" ብለዋል፡፡ በሁለቱም ክልሎች ያነጋገርናቸው መንደረተኞች አብዛኛዎቹ ወደሰፈራ ሜድ እንደማይፈልጉ የገለጹ ሲሆን "መንግሥት ሂዱ ካለ ግን ሜድ አለብን" ብለዋል፡፡

በርካታ ማንደረተኞች ወደ ሰፈራ ሜድ እንደሜዴፈልጉና እንዲያወም ስለዚህ ጉዳይ ሲያስቡ የወደፊት ዕጣ ፈንታቸው ምን እንደሚሆን እንደሚያስጨነቃቸው ተናግረዋል፡፡ በቤንሻንጉል የሚገኙ ማንደረተኞች ወደሰፈራ የሜዱበትን ቦታ የወሰኑ ሲሆን ይህም ለዋና ማንገድና ለውሃ ቅርበት ያለው፣ ከማንደሮቹም አማካይ የሆነ ና በቂ የእርሻና የግጦሽ ቦታ ያለው መሆን እንደሚገባ በወሳኔያቸው አሳወቀዋል፡፡

የግዳጅ ሰፈራውን ጉዳይ በተማለከተ ሌሎች ማነበረሰቦች ግን ጥርጣሬ እንዳላቸው ሲናገሩ ይህ የሚከሄደበት ዋንኛ ምክንያቶች ኅብረተሰቡ በማንግሥት ላይ ጥገኛ እንዲሆን፣ የአማፂያን ቡድኖች በክልሉ እንዳይንቀሳቀሱና ማንግሥትም "ሜሬቱን በቀላሉ ለባለሃብቶች ለማስጠት እንዲያመቻው" ነው ይላሉ፡፡ ይህንን በማስረጃ ለሚረጋገጥ የሚቻል ባይሆንም ወደ ሰፈራ እየተነሱ ባሉት ማንደሮች እና ለሰፋፊ ንግድ ተኮር እርሻ አገልግሎት እንዲወሉ ምልክት የተደረገባቸው የሜሬት ይዞታዎች ማካከል ቀጥተኛ ግንኙነት ይታያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለመጀሜሪያ እንዲነሱ የተወሰነባቸው ማንደሮች ለውጪ ባለሃብቶች በተሰጡት የሜሬት ይዞታዎች ላይ የሚኖሩና ሜሬቱንም እየተጠቀሙ የሚገኙ ማነበረሰቦች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ለሳውዲ ስታር በተሰጠው ሜሬት ላይ የሚኖሩት በማንደር ምስረታው ፕሮግራም መሠረት በአቅራቢያው ወደሚገኘው ፖኬዲ ቦታ እንዲሄዱ ተነግሯቸዋል፡፡ እነዚህ ማንደረተኞች ለትወልድ ሲገለገሉበት የነበረው ደን በአሁኑ ጊዜ በሳውዲ ስታር ተመንጥሯል፡፡

አንድ በአብዘኛው የሚነገር ጉዳይ ወደሰፈራ የሚኬደባቸው ቦታዎች የምግብ ዕጥረት ይኖራል የሚል ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በርካታ የአካባቢው ነዋሪዎች አሰባጥሮ የሚዘስን ልምድ የሚከተሉ ሲሆን በዚህም ምክንያት ሜሬታቸውን ከ 3 – 7 ዓመታት ካረሱ በኋላ ምርት ሲቀንስ በአቅራቢያው ወደሚገኝ ሌላ ሜሬት በሜድ እዚያም እንዲሁ ከ3 – 7 ዓመታት ሲያርሱ ይቆያሉ፡፡ አንዳንድ ሜደረተኞች ወዲያውኑ ወደመጀሜሪያው ሜሬት የሚማለሱ ሲሆን ሌሎች ግን ወደተለያዩ ቦታዎች ለዓመታት ሲያርሱ ከቆዩ በኋላ ነው ወደመጀሜሪያው ሜሬት የሚማለሱት፡፡ ሌሎቹ የአገሬው ነዋሪዎች በተለይም የጋምቤላ አኙዋኮች ቋሚ ለም የሜሬት ይዞታዎች በክልሉ ወንዞች አቅራቢ አሏቸው፡ በጋምቤላ የሚደረገው የማንደር ምስረታ እያንዳንዱን ቤተሰብ በአንድ ቋሚ ቦታ ላይ ከ3 – 4 ሐክታር ሜሬት በማስጠት የሚደረግ የአሰፋፈር ፖሊሲን የሚከተል ነው፡፡[128] በቤንሻንጉል ግን ለእያንዳንዱ ቤተሰብ 2.5 ሐክታር ሜሬት ለእርሻ ለማስጠትና ግማሽ ሐክታር በማስኖ የሚለማ ሜሬት ለምግብ ምርት እንዲሁም ለግጦሽ 1ሐክታር ሜሬት እንዲሰጥ የሚያደርግ ፖሊሲ ነው፡ እነዚህ የሜሬት ይዞታዎች ከዚህ በፊት በክልላዊ ማስተዳድሮች ሚረጋገጫ የሚሰጥባቸው ነበሩ፡፡[129] የእርሻ ዘዴዎችና ሌሎች ግብዓቶች ከአዲሱ የእርሻ አካሄድ ጋር እየተስማሙ ሜድ አለባቸው፡ ለዚህም ስልጠና እንደሚሰጥ የክልል ማስተዳድሮች ተስፋ በሰጡም ነዋሪዎች ግን እምነት የላቸውም፡

"እነርሱ እዚያ (የተመሠረተው ማንደር) ሜሬቱን አጽድተው ሊያዘጋጁ ይችላሉ፤ እኛ ግን ሚዘስ የምናወቀው እዚህ ነው፡ እዚያ እንዴት ሚዘስ እንደምንችል አናወቅበትም፡ ግራ ገብቶናል፤ ምን ሜድረግ እንዳለብን አናወቅም፡"

"አንዳንዶች ወደ ሰፈራው አይሄዱም፤ እዚሁ እየተራብን እንሞታለን እንጂ እዚያ በውሃ ብቻ መኖር አንችልም፡"

በአሁኑ ጊዜ ማንደረተኞቹ ሁሉ ለምግብ የሚሆናቸውን በወንዙ ዙሪያ በሚገኙ ቋሚ የሜሬት ቦታዎች ላይ የሚያመርቱ ሲሆን በከፍተኛ ቦታዎች ላይ ደግሞ አሰባጥሮ የሚዘስን ልምድ በማከተል በቆሎ ያመርታሉ፡፡ ይህ አሰባጥሮ የሚዘስ ልምድ አሣ ከማጥመድና ከደን ወስጥ ከሚያገኙት ምግብ ጋር በተቀናጀ ሜልኩ የምግብ እጥረት እንዳይኖር የሚከላከሉበት ዘዴ ነው፡ ወደሰፈራ ከሄዱ በኋላ ግን የምግብ እጥረት ቢከሰትባቸው ያላቸው ብቸኛ ማካላከያ ከማንግሥት የምግብ ዕርዳታ መቀበል ሲሆን ለአንዳንድ ማንደረተኞች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ ማንግሥት የምግብ ዕርዳታ እንደሚያደርግ ተናግሯቸዋል፡፡

"እነርሱ እንደሚሉት በርካታ ውሃ እንዲሁም ማጠነኛ ጎጆ ቤት እና ከጓሮ ደግሞ አትክልት ለማበቀያ ቦታ ይኖራል ነው የሚሉት፡፡ ሆኖም ግን ምንም ምግብ እንደሜይኖር ነው እኛ የምናወቀው፡ እነርሱ የምግብ ዕርዳታ እንደሚሰጡ ይናገራሉ ሆኖም እኛ ካለን ልምድ እነርሱ የተናገሩትን በጭራሽ የሜይጠበቁ መሆናቸውን ነው፡ እኛ ግን እዚህ የራሳችንን ምግብ ማምረት እንችላለን፡፡ ስለዚህ በፍጹም ከዚህ አንሄድም፤ ሊወስዱን የሜሬልጉ ከሆነ መጀሜሪያ እኛን መግደል አለባቸው፡"

"ማንግሥት ምግብ የሚያቀርብልን ከሆነ ሜልካም ነው፤ ካልሆነ ግን ጥሩ አይሆንም፡ እኛ ወይ ወደ ወንዙ እንሄዳለን ወይም ወደ እርሻችን እንማለሳለን፡፡"

በማደር ምስረታ እና በንግድ ተኮር የሜት ኢንቨስትመንት መካከል ያለዉ ግንኙነት ጊዜ ራሱ የሚፈታው ቢሆንም ተበታትኖ የሚገኘዉ ነዋሪ በአንድ ማሰባሰብ ሰፋፊ ቦታዎችን ለእርሻ ኢንቨስትመንት እንዲውሉ ዕድል ይከፍታል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሜት በፌደራሉ የሜት ባንክ ወስጥ የሚገኝ ሲሆን ከእነዚህም ወስጥ አብዛኛዎቹ በቤንሻንጉል፣ በደቡብ ሕዝቦች፣ እና በጋምቤላ ክልሎች ወስጥ የሚገኙ ናቸው፡ የማደር ምሥረታዉም እንዲሁ እየተከናወነ ያለው በእነዚህ ክልሎች ወስጥ በሚገኙ ቦታዎች ላይ ነው፡ ምንም እንኳን ማግሥት ጉዳዩን ሊያስተባብል ቢሞክርም ይህ የጥናት ቡድን ለሚረጋገጥ የቻለው ነገር ቢኖር ገበሬዎች አሁን እያረሱበትና እየኖሩበት የሚገኘው ሜት በፌደራሉ የሜት ባንክ ወስጥ ለኢንቨስትመንት እንዲወሉ ተዛወረዋል፡፡

"ኃይለሥላሴ ጥሩ አልነበሩም፤ ደርግም እንዲሁ የሜሉሶ ማስፈር ተግባር ሲያካሂድ ነበር፤ ሆኖም ግን እንዳሁኑ ሆኖ መቼም አያውቅም፡ ከዚህ በፊት መቼም ቢሆን አካባቢያችንን ለቅቀን እንድንሄድ አስገድደዉን አያውቁም፡ ይሄ ከእኛ በስተጀርባ የሚታየው ደን ይታሃል? ያኔ የጭፍጨፋው ጊዜ በርካታ ሰዎች እዚያ ተደብቀው ነበር፡፡ አሁን ይህንን ሁሉ ይመጥሩታል፤ ታዲያ ለልጆቻችን ያላቸው ተስፋ ምንድነው? በቃ አገልጋይ ባርያ ሆነው ነው የሚቀሩት፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ማንም መጥቶ ሳያነጋግረን

መቅረቱ ነው፤ ቢመጡና ቢያነጋግሩን እኮ ይህ ቦታ እንዴት የአያት ቅድመአያታችን ቦታ እንደሆነ እንነግራቸው ነበር፡፡"

### የመተዳደሪያ መጥፋት

የማደር ምስረታ፣ ሰፈራ፣ የእርሻ ሜት ማጠቅ፣ የተፈጥሮ ኃብት መወደም፣ የወሃ ኃብት መቀነስ፣ ወዘተ ማከሰት ለነዋሪው ሕዝብ መተዳደሪያ የሆነው ሁሉ እየጠፉ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡ በጋምቤላ 45ሺህ እንዲሁም በቤንሻንጉል 90ሺህ ቤተሰቦችን ወደ አዲስ ማደር በማስፈር እና ሜቱን ለኢንቨስትመንት ለማዋል ሲባል በሚደረገው የሚፈናቀል ተግባር የ650ሺህ ሰዎች መተዳደሪያ እንደሚጠፉ ይነገራል፡፡[130] በማደር ምስረታ ወይም በሜት ኢንቨስትመንት ምክንያት በደቡብ፣ በኦሮሚያ፣ በአፋርና በሌሎች ክልሎች የሚኖሩት ሰዎች አጠቃላይ ቁጥር ከአንድ ሚሊዮን እንደሚበልጥ ይገመታል፡፡[131]

ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚከሰተዉን የመተዳደሪያ መጥፋት በቀላሉ ሊታይ የሚገባው አይደለም፡ እነዚህ ቤተሰቦች ከሚፈናቀላቸው በፊት በተለይ በምግብ በኩል ራሳቸዉን ችለው ይኖሩ የነበረ ሲሆን አሁን ግን ከዚህ ደረጃ ዝቅ ብለው በማግሥት ድጎማ የሚኖሩ ጥገኞች እንዲሆኑ ተገድደዋል፡፡ ከዚህም አልፎ የአማገብ ሁኔታቸው ማለወጥ፣ ከአያት ቅድመአያታቸው የተረከቡትን ሜት ማጣት፣ የደመወዝና የዕርዳታ ጥገኛ መሆናቸዉና በማነበረሰቡ ወስጥ ያለው ቅርርብ መላላት በአጠቃላይ የመተዳደሪያና አብሮ የመኖርን ድርና ማግ እያጠፉ እንደሚሄድ ነው፡ ከማደር ምስረታው ሂደት ጋር በተያያዘ ማግሥት ለኅብረተሰቡ የሚሆን የእርሻ ሜት እንዲሁም አዳዲስ የእርሻ ዘዴዎችን እንዲማሩ ስልጠና እንደሚሰጣቸው ቃል የገባ ቢሆንም እስካሁን የተደረገ አንዳችም ነገር የለም፡ የምግብ ዋስትና እየቀነሰ ማጣት፣ ከተፈጥሮ ኃብት ጋር በተያያዘ የሚኖሱ ግጭቶች የሚጨምሩቸው ሁኔታ እየጎላ ማጣት፣ ሰዎች ለራሳቸው ያላቸው ክብር መቀነስ እና የባህላዊ ማንነት ማሸርሸር በአጠቃላይ የመተዳደሪያ መጥፋት ወጤት ሆነው ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡ ስለሆነም በሜት ኢንቨስትመንት ምክንያት የየአካባቢው ነዋሪዎች ላይ የሚደርሰው ተጽዕኖ የረጅም ጊዜ፣ ዘላቂና ወደነበረበት መመለስ የሚይቻል ነው፡

## 3.4 ንብረት ማስጣትና ሚፈናቀል

ይህ የጥናት ቡድን በጎበኛቸው ቦታዎችና አጎራባች ማደሮች በሜት ኢንቨስትመንት ወይም በሰፈራ ምክንያት የተከሰተ ምንም ዓይነት የሚፈናቀል ተግባር ማስረጃ አልተገኘም፡ ሆኖም የሜት ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ሁኔታ በጣም በሚከሄድባቸው ቆላማ ክልሎች (ጋምቤላ፣ ቤንሻንጉልና ደቡብ ሕዝብ) ማጠነ ሰፊ የማደር ምስረታ የሚከሄድ ሲሆን ይህም ተበታትነው የሚገኙ ማደሮችን ወደ አንድ ቦታ በማምጣት የአገልግሎት አቅርቦትን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማዳረስ እንዲያስችል በሚል ነው፡ (ሣጥን ቸ፡ ዝርዝር ማዘራሪያ ይሰጣል) የተበታተኑ ነዋሪዎች የሚገኙባቸው ቦታዎች ለሜት ኢንቨስትመንት ከታቀዱት ቦታዎች አብዛኛዎቹ ናቸው፡ በመሆኑም የማደር ምስረታው ተግባር ቦታዎቹን እያጸዱ ለእርሻ ንግድ ለባለሃብቶች ለማስጠት የታቀደ መሆኑ በሰፊው ይታመነበታል (በተለይ በአካባቢው ነዋሪ ዘንድ በዚህ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ አለ) በኢትዮጵያ ወስጥ ሰፋፊ ቦታዎች ከያዙት ቀዳሚ የሆነው የሕንዱ

ካሩቱሪ ኩባንያ ተጨማሪ ቦታ ከፈለገ የጋምቤላ ክልል ማስተዳድር የአላ ማንደርን ወደ ሌላ ቦታ በመውሰድ ለካሩቱሪ ቦታውን ሊያዘጋጅለት እንደሚችል የኩባንያው ሹማምንት በአደባባይ ይናገራሉ፡፡ ኩባንያው ግን አለሚፈለጉን አስታወቋል፡፡[132]



በርካታ አነስተኛ ባለሃብቶች የወሰዱትን ሜሬት በመማጠር በሕገ ወጥ የከሰል ንግድ በማስሜራት ዳጎስ ያለ ገንዘብ ያገኛሉ

ከሰፈራው ሞርሃግብር ጋር በተያያዘ ከማንደር ምክረታው በስተቀር ማጠነኛ የሚናቀል ሁኔታ እስካሁን ያለ ቢሆንም ማጠነ ሰፊ የሆነ የእርሻ ሜሬት እና የማነበረሰቡ የሞሪያ ስፍራ በእጅጉ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ እንዲያወም በአንዳንድ ቦታዎች ይህ የእርሻ ሜሬት ሰብል እያለበት የተማጠረ ሲሆን ይህ ዓይነቱ ድርጊት በአብዛኛው በእነዚህ ቦታዎች ሊከሰት የቻለው ሜሬቱ ወደፊት ለጥቅም እንዲወል በአሰባጥሮ እርሻ ልምድ ምክንያት የተተወ በመሆኑ ነበር፡፡ በዚህ የጥናት ቡድን የተጎበኙት አብዛኛዎቹ የአካባቢው ነዋሪዎች የተለያየ አሰባጥሮ የሚዞስ ልምድን የሚከተሉ ናቸው፡፡ የጋምቤላ ኑዌሮች ለምሳሌ ያህል በጋውን በወንዙ ዙሪያ በሚዞስና ለከብቶቻቸው ግጦሽ በሚፈልግ ያሳልፉና ክረምት ሲመጣ ወደ ወስጥ ገባ ብለው መኖር ይጀምራሉ፡፡ ይህም ሆኖ ግን በአሁኑ ወቅት በእርሻ አገልግሎት ላይ የነበረ እንዲሁም በአሰባጥሮ የሚዞስ ልምድ ምክንያት የተተወ ማጠነ ሰፊ ሜሬት ለኢንቨስትመንት ተሰጥቷል (የሜሬቱ ስፋት ከአንድ ሺህ ሔክታር በላይ ነው) ሆኖም የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) እና ሌሎች የመንግሥት መ/ቤቶች ይህንን የአሰራር ሁኔታ በአጽንዖት የሚቃወሙ ሲሆን በአሰባጥሮ የእርሻ ዘዴ ምክንያት በእዳሪ ሜሬትነት ባዶ የሆኑትን የሜሬት ይዞታዎች “የተተዉ/የሚፈለጉ” የሜሬት ይዞታዎች ብለው ነው የሚጠሯቸው፡፡

ኤላ በተባለው ማንደር ስለሆነው ካሩቱሪ ኩባንያ ሲናገር ምንም የጠፉ ሜሬት እንደሌለ ነዋሪዎቹም እንዳልተፈናቀሉ በተደጋጋሚ ያስረዳል፡፡[133] ሆኖም ነዋሪዎቹ እንደሚሉት ካሩቱሪ መጥቶ ቦታውን በማጠረው ጊዜ ማንደረተኛው ያበቀለውን በቆሎ፣ ማሽላ እና ሌሎች የኦቾሎኒ ዝርያ ያላቸው

ሰብሎችን በሙሉ እንደወደመባቸው ይናገራሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከአያት ቅድመአያታቸው ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ስርዓት መሠረት ሚዎቻቸው ይቀበሩበት የነበረውን ንጉሣዊ የመቃብር ቦታ አብሮ ወድሟል፡፡ አሁን የቀረው አንድ ብቻ ሲሆን ይህም ሊድን የቻለው ማኅደረተኛው ወጥቶ ከባንያው ያስሚራውን ዶዘር ፊት ለፊት በማፈጣቸው ነበር፡፡[134]

እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በባኮ 10ሺህ ሔክታር ሜሬት ለካሩቱሪ በማስጠቱ በርካታ ገበሬዎች ሜሬታቸውን አጥተዋል፡፡ በምላሹ የእርሻ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት (AISD) ቃልአቀባይ ሲናገሩ "ነዋሪዎቹ የባለቤትነት ማስረጃ ካላቸው ተገቢው ካሣ ይሰጣቸዋል፤ አለበለዚያ ሜሬቱን ይጠቀሙ የነበረው በሕገወጥነት ነበር ተብሎ ይያዛል" ብለዋል፡፡ ሆኖም የሜሬት ምዝገባ ሥራ በኦሮሚያ ክልል ገና አልተጠናቀቀም፤ እንዲሁም በክልሉ በየትኛውም ቦታ ቢሆን ኅብረተሰቡ ለሚኖርበትም ይሁን ከብቶች ለግጦሽ የሚጠቀሙበት ቦታ በተማከለ ሕጋዊ የባለቤትነት ደብተር ተሰጥቶ አያውቅም፡፡

በቤንሻንጉልም ለኢንቨስትመንት ስለተሰጠው 3ሺህ ሔክታር ሜሬት አንድ ባለሃብት ለዚህ የጥናት ቡድን ሲናገሩ በቦታው ላይ በርካታ ገበሬዎች (የአገሬው ተወላጅ ጉሙዞችና ደገኞች) የነበሩ መሆናቸውን ገልጸው እነዚህ ማኅደረተኞች ከቦታቸው ባለመነሳታቸው ምክንያት ከ300 ሔክታር ሜሬት በላይ ሊማጥር እንዳልቻለ ይናገራል፡፡ ሆኖም በባለሃብቱና በገበሬዎቹ መካከል የተፈጠረው ጥላቻ እያደገ በመምጣቱ የወረዳው ማስተዳደር የባለሃብቱን የሜሬት "ወሰን ለማከለል" ቃል ገብቷል፡፡

ገበሬ ይሁን ነዋሪ እንደሌለ በተዘዋወረበት ቦታ ሁሉ ለማታዘብ ችሏል፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች ሜሬታቸው የተወሰደባቸው ተቀጥረው ማሥራት እንዲችሉ ሜሬቱን በወሰደው ባለሃብት ጥያቄ የቀረበላቸው አሉ፡፡

ምንም እንኳን የሜሬት ባለቤትነት ደብተር ቢኖርም ባይኖርም እንዲሁም ለሜሬቱ ተገቢው ካሣ ተሰጥቶታል ቢባልም ሜሬት ግን ምትክ የሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ወስጥ ሜሬት አይሸጥም፤ አይለወጥም፡፡ በመሆኑም ካሣ እንኳን ተብሎ የሚከራው ገበሬዎችን ሜሬት አልባ ከሚያረግ

**ካሣ**

የማግሥት ባለሥልጣናት "ማንም ሰው ከእርሻ ሜሬቱ አልተፈናቀለም" የሚሉ በመሆናቸው የካሣ ጉዳይ በተማከለ ለመጠየት በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ የካሣ ጉዳይ አስፈላጊነት የለውም ለማለት ያስገድዳል፡፡ የካሣ አከፋፈልን በተማከለ ተፈላጊ ማስፈርቶች በኢትዮጵያ ሕግ ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በተለይ በአዋጅ ቁጥር 455/1997 ስለ ወርስ እንዲሁም ባለሜሬቱ በሜሬት ይዞታው ላይ ያፈሰሰውን የሥራተኛና የካፒታል ማጠን አስልቶ የቅድሚያ ካሣ ሊከፈለው እንደሚገባ በግልጽ ይናገራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሜሬቱ ላይ የሚፈናቀል ማንኛውም ሰው በሜሬት ይዞታው ላይ ያፈሰሰው የካፒታልና የሰው ኃይል እንዲሁም ያደረገው ማሻሻያ ታስቦ ካሣ እንዲሰጠው ህጉ ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም የተፈናቀሉ ሰዎች ባለፉት 5 ዓመታት ካገኙት አማካይ ዓመታዊ ገቢ 10 እጥፍ የሚሆን ገቢ ሊቀበሉ ይገባቸዋል በማለትም ያዝዛል፡፡

ሆኖም ግን ይህ ሁሉ ተግባራዊ የሚሆነው ገበሬው በሜሬቱ ላይ ህጋዊ የባለቤትነት ደብተር ሲኖረው ብቻ ነው፡፡የባለቤትነት ደብተር ለሌላቸው የካሳ አከፋፈልን በተማከለ ሊደረግላቸው ስለሚገባው አስተያየት ምንም ዓይነት ሕጋዊ አሠራር እስካሁን የለም፡፡ ለዚህ የጥናት ቡድን አስተያየታቸውን የሰጡ ምንጮች ሲናገሩ የካሣ ክፍያ በአብዛኛው የሚሰጠው በአዲስ አበባ ዙሪያ (አካባቢ) የሜሬት ይዞታ ላላቸው (በዚያ አካባቢ የሚገኝ የሜሬት ይዞታ ለከተማ ማስፋፋት፣ ለኢንዱስትሪ ግንባታ ወዘተ የሚውል ነው) እንዲሁም የአበባ ንግድ እየተጧጧፈ በመጣበት ከ1997-1999 ድረስ ባሉት ዓመታት እንደነበር ገልጸዋል፡፡ ይህ የጥናት ቡድን ሜሬቱ ለተወሰደበት በምትኩ ካሣ የተሰጠው አንድም

በስተቀር የኅብረተሰቡን አኗኗር ከመቀየር አኳያ ምንም የሚያመጣው ተጽዕኖ የለም፡፡

## 3.5 የአካባቢ ተጽዕኖ

በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ ኢትዮጵያ በርካታ ችግሮች አሉባት፡፡ እነዚህም የሜሬት ኃብት ሜራቆት (ዝቅጠት)፣ በአየር ንብረት ማለዋወጥ ምክንያት

ለሚከሰት የአካባቢ ብክለት ተጋላጭነት፣ የአየር ብክለት፣ የውሃ ብክለት፣ የብዝሃ ሕይወት መጥፋት፣ አካባቢውን በፍጥነት የመውረር ችሎታ ያላቸው ባዕዳን ዝርያዎች ማስፋፋት፣ የከተማ አየር ብክለት እና ከየቤቱ የሚወጣ መርዛማ የቆሻሻ ፍሳሽ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡[135]

## የደን ምንጠራና የሜሬት ኢንቨስትመንት

ኢትዮጵያን ከሚያሰጓት የአካባቢ ጥበቃ አደጋዎች ቀዳሚው የደን ምንጠራ ነው፡፡ በተለይ በደጋማው የአገሪቷ ክፍል ይህ የደን ምንጠራ በሰፊው የሚካሄድ ሲሆን በየዓመቱ ከ80ሺህ እስከ 200ሺህ ሔክታር ደን ይመነጠራል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የአፈር ኃብት መዘቀጥና የአፈር መሸርሸር እያደጉ ያሉ ችግሮች ሲሆኑ ይህም በየዓመቱ ለምርት መዋል የሚችል 30ሺህ ሔክታር ሜሬት እንዲወድም እያደረገ ይገኛል፡፡ (2ሚሊዮን ሔክታር ሜሬት ፈጽሞ ጥቅም ሊሰጥ በማይችልበት ሁኔታ ወድሟል፡፡)[136] ምንም እንኳን በቆላማ የአገሪቱ ክፍል የደን ምንጣሮው በምን ያህል ፍጥነት እያደገ እንደሆን ለማወቅ እርግጠኛ ሚረጃ ባይኖርም በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው ለባለሃብቶች እየተሰጠ ያለው ሜሬት (ለሽያጭ ዝግጁ ነው ስለሚባል) በእርሻ ሥራ ላይ ያልዋለ ሲሆን በአብዛኛው በተፈጥሮ ደንና በዛፎች የተሸፈነ ነው፡፡ የሚታረስ ሜሬት በተፈጥሮ ደን ወይም በዛፍ ካልተሸፈነ በአካባቢው ተወላጆች ተመንጥሮ የተወሰነ የእርሻ በኢትዮጵያ ወስጥ በተለያየ ቦታ በተለይም በቆላማ የአገሪቷ ክፍል ለሚገኙ በርካታ ተወላጅ ነዋሪዎች የተፈጥሮ ደን ከፍተኛ ደረጃ የሚሰጠው አገልግሎት አለ፡፡ (ሣጥን (በ) ይመልከቱ) ከእነዚህም ጥቅሞች መካከል ለመድኃኒትነት፣ ለማገዶነት፣ ለህንጻ መሣሪያነት፣ ለምግብነት ከመዋሉ በተጨማሪ አንዳንድ ዛፎች ባሕላዊና ታሪካዊ ትርጉም ያላቸው በመሆናቸው በጥቃት ጊዜ ከጠላት ለመከላከያነትም ያገለግላሉ፡፡ በተደጋጋሚ በየአካባቢው የሚኖሩ ተወላጅ ነዋሪዎች ለዚህ የጥናት ቡድን እንደተናገሩት በተለይ ድርቅ በሚከሰትበትና በአየር ንብረት ለውጥ፣ በተባይ መከሰት እንዲሁም በግጭት ምክንያት የምግብ ዕጥረት በሚኖርበት ጊዜ ከጫካው (ከደኑ) የሚገኘው ሁሉ ለችግር ቀን መውጫ በመሆን እንደሚያገለግል በተደጋጋሚ ገልጸዋል፡፡[137]

በተለይ በቤንሻንጉል ክልል በሚፈጸም የሜሬት ውል ስምምነት ላይ እንደሰፈረው አንድ ሔክታር ሜሬት በተመነጠረ ቁጥር በምትኩ ስድስት ዛፎች መተከል እንዳለባቸው የሚያዝ ቢሆንም በየአካባቢው ስምምነቱን ተግባር እየተከናወነበት ይገኛል ማለት ነው፡፡ ከዚህ ወጪ ደን የሚጨፈጨፍ ወይም ዛፎች እንዲሁ የሚቆረጡ ሲሆን ይህ የጥናት ቡድን የጎበኛቸው የኢንቨስትመንት ቦታዎች በሙሉ ማለት ይቻላል ቀድሞ በዛፍ የተሸፈኑ ስፍራዎች ወይም የተፈጥሮ ደንና ዛፎች የነበሩባቸው ሲሆን አሁን ግን በቡልዶዘር ዛፎቹ ተመንጥረውና ተጨፍጭፈው ሜሬቱ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት እንዲውል የተደረጉ ናቸው፡፡ እንዲያውም በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የምንጣሮውን ሥራ እያከናወኑ የነበሩ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች ዛፎቹን እየገነደሱ ለከሰልና ለማገዶነት በአካባቢው ለሽያጭ ለማቅረብ ሲሰሩ ይህ የጥናት ቡድን በእማኝነት ለመመልከት ችሏል፡፡

የከሰል ሽያጭ በኢትዮጵያ በሕግ የተከለከለ ቢሆንም በየቦታው እየተካሄደ ያለና የተለመደ ድርጊት እንደሆነ ይስተዋላል፡፡ ማጠነ ሰፊ ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ (በተለይ የውጭ) ባለሃብቶች ከባድ መሣሪያዎችንና ማሽኖችን በማጠቀም ምንጣሮና የደን ጭፍጨፋ ካካሄዱ በኋላ እንጨቱን፣ ቁርጥራጩን አንድ ላይ በማድረግ ሲያቃጥሉት ይህ የጥናት ቡድን በአካል ተገኝቶ የተመለከተ ሲሆን በየአካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎችም ይህንኑ ይመሰክራሉ፡፡

የሚያስፈጽመው የኢንቨስትመንት ቢሮ ይህንን በጭራሽ ተግባራዊ አድርጎ አያውቅም፡፡

## የአሃዳዊ ባህሎች ተጽዕኖ

አሃዳዊ ባህሎች እና የኢንዱስትሪን ዘዴ የሚከተል ግብርና በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚያማጡት ተጽዕኖዎች የሚከተሉት ናቸው፡-የአካባቢ በመርዛማ ኬሚካሎች መመረዝ (ይህ በተለይ የአፈርን ዘር የማበቀል ብቃት በመቀነስ በሁሉም የተመጋቢ ሠንሰለት የሚገኙትን ሊጎዳ ይችላል)፣ የተፈጥሮን ተባይ የመካላከል ዓቅም ማዛባት፣ አዳዲስ አረሞችና የዕጽዋት (የአዝርዕት) በሽታዎች መከሰት፣ የብዘሃ ሕይወት መጥፋት፣ አገር በቀል በሆኑት ዕጽዋት ወስጥ በሳይንስ የተዳቀሉ የዕጽዋት ዝርያዎች ማስፋፋት (ቴሳ ምንደሳ ወይም genetically-engineered) ወዘተ የተለመዱት ናቸው፡፡[138]

አሁን እየተሸጡ በሚገኙት ቦታዎች ላይ የሚከሄደው የእርሻ ልማት በጣም ውሱን በመሆኑ የማዳበሪያና የተባይ ማጥፊያ አጠቃቀም የዚያኑ ያህል የተወሰነ ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ በዚሁ አይቀጥልም፡፡ ምክንያቱም በርካታ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች እነዚህን ኬሚካሎች በሊዝ በወሰዷቸው ሜሬቶች ላይ በብዛት ለማጠቀም ማዘጋጀታቸውን የገለጹ ሲሆን ይህንን የሚከለክል (የሚገድብ) ሕግ ስለሜኖሩ ምንም የሚያወቁት ነገር እንደሌለ ገልጸዋል፡፡ ለግብርና ኢንቨስትመንት የተዘጋጀው የአካባቢ ጥበቃ ሕግ የተባይ ማጥፊያ አጠቃቀምን በተማለከተ እንዲሁም በሕግ የተፈቀዱ ኬሚከሎችን ዝርዝር፣ መሠረታዊ የአካባቢ አጠባበቅ ማስፈርቶችን (ማለኪያዎችን)፣ የሠራተኞችን የጤና አጠባበቅንና ደኅንነትን በተማለከተ ዝርዝር መመሪያዎችን ይሰጣል፡፡ የፌደራል የተባይ ማጥፊያ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 20፤1982 የተባይ ማጥፊያን በተማለከተ የጥንቃቄ አጠቃቀምን፣ ምዝገባን እንዲሁም ስለ ጤና አጠባበቅና ደኅንነት ዝርዝር መመሪያ የሚሰጥ ቢሆንም እስካሁን ግን ሕጉ በሥራ ላይ አልዋለም፡፡ ኢትዮጵያ ደግሞ ከተባይ ማጥፊያ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ አሳሳቢ ታሪክ አላት፡፡ ለምሳሌ በቅርቡ በተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ለተባይ ማጥፊያ ከውጭ ወደ አገር ወስጥ ከሚገቡት 96 መድኃኒቶች ወስጥ 18ቱ እንዲሁም ፈንጂሳይድስን (fungicides) ለማጥፋት እንዲሁ ከውጪ ከሚገቡት 105 መድኃኒቶች መካከል 19ኙ ብቻ በአበባ አምራቾ (አብቃዮች) ለጥቅም የዋሉ ቢሆኑም ፈቃድ ከተሰጣቸው መድኃኒቶች ዝርዝር መካከል ግን አይደሉም፡፡[139]

## ሌሎች የአካባቢ ጥበቃ ተጽዕኖዎች

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨሜሪ ሊከሰቱ የሚችሉ እጅግ አስከፊ የሆኑ የአካባቢ ጥበቃ ተጽዕኖዎች የእርጥብ ሜሬቶች ብክለት፣ የዱር አራዊት በዓይነትም ሆነ በብዛት መቀነስ፣ የወሃ ማበከል፣ ዝርያቸው በሚይታወቅ የአዝርዕት (የዕጽዋት) አረም መወረር እና የብዝሃ ህይወት መጥፋት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በየአካባቢው ለሚገኙ ነዋሪዎች የእርጥብ ሜሬት መኖር ለኑሯቸው ወሳኝ የሆነ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነቶቹ ሜሬቶች ማጠነ ሰፊ የሆነ የብዝሃ ህይወት የሚገኝባቸው በመሆናቸው ጎርፍን በመካላከል፣ የወንዞችን

### ሣጥን ጎ፡ የአየር ንብረት ለወጥ በኢትዮጵያ[140]

ኢትዮጵያ በአብዛኛው ሕዝቧን የመመገብ ብቃቷ ጥገኛ የሆነው በአየር ንብረት ላይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የምግብ ዋስትና በአገሪቷ ወስጥ ተግባራዊ እንዳይሆን ካደረጉት መካከል ቀዳሚዎቹ ድርቅና የጎርፍ አደጋዎች ናቸው፡፡ አሁን እየተካሄደ ያለው የሜሬት ሽያጭ ይህም በአየር ንብረት ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት አንጻር በኢትዮጵያ የሜሬት ኢንቨስትመንት ፖሊሲ ላይም ሆነ በአጠቃላይ ተለዋዋጭ በሆነው የአየር ንብረት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ትኩረት የተሰጠው አይመስልም፡፡ በወሃ ኃብት አጠቃቀም ላይ ያለው ልቅነት እንዲሁም የምርቱን አላላክና የገበያወን ሁኔታ በተማለከተ ያለው የላላ ቁጥጥር ሁኔታወን የበለጠ እንዲባባስ ያደርገዋል፡፡

በቅርቡ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት እንዳማለከተው በአየር ንብረት ለወጥ ምክንያት ለሚደርሰው አስከፊ ወጤት በከፍተኛ ሁኔታ ከተጋለጡት አገሮች መካከል ኢትዮጵያ በቀዳሚነት እንደምትገኝ ዘግቧል፡፡ ለሚከሰተወም ለወጥ ኢትዮጵያ ምላሽ ለመስጠት ያላት የአቅም ብቃት ዝቅተኛ መሆኑን ጥናቱ ጨምሮ አስታወቋል፡፡ የአየር ንብረት ለወጥን በተማለከተ የሚከናወኑ የሞዴል ጥናቶች እርግጠኛ ያለመሆን ችግር ቢኖራቸውም አሁን ካለው ሁኔታ በመነሳት በኢትዮጵያ የዝናብ ሁኔታ መለዋወጥ፣ አስከፊ የአየር ጠባይ ክስተቶች፣ የወሃ እጥረትና የሙቀት ሜጨመር (የዓለምአቀፉ የጥናት ሞዴል እንደሚያነብየው የዛሬ 40ዓመት በኢትዮጵያ የሙቀቱ ማጠን በአማካይ ከ1.7 እስከ 2.1 ዲግሪ በሴንቲግሬድ ይጨምራል) እንደሚከሰት ብዙዎች የሚጋሩት ሃሳብ ነው፡፡ ከዚህ ጋር የተያያዙ ተጽዕኖዎች ደግሞ በሽታ (ወባ፣ ኮሌራ፣ የአከርካሪ አጥንት ትኩሳት ተብሎ የሚጠራው (dengue fever)፣ …) እንዲስፋፉ፣ የምግብ ዕጥረት፣ የሜሬት

ኃብት ማሽቆ፣ የሠረተ ልማት ወድመት እንዲከሰት እንዲሁም አላቂ በሆኑ የተፈጥሮ ኃብቶች ላይ ያለው እሽቅድምድም ሁኔታው እንዲባባስ ያደርጉታል፡፡ በቤንሻንጉልና በጋምቤላ የሚኖሩ ገበሬዎች ለዚህ የጥናት ቡድን ሲናገሩ፡- ባለፉት አምስት ዓመታት በክልላቸው የተከሰተው የአየር ጠባይ (የዝናብና የሙቀት ማጠን ማለያየት፣ በወንዞች ውስጥ ያለው የውሃ ማጠን መቀነስ፣ ወዘተ) ፈጽሞ ሊተነበይ የሚቻል እና ፈጽሞ ተለዋዋጭ እየሆነ እንደመጣ ገልጸዋል፡፡ ይህም በምግብ ምርታቸው ላይ ተጽዕኖ ማስደሩን አክለው ተናግረዋል፡፡

አፈሳሰስ በመቆጣጠር የአካባቢውን የውሃ አቅርቦት የሚቆጣጠሩ የተፈጥሮ ስጦታዎች ናቸው፡፡ አሁን ባለው የሜሬት ኢንቨስትመንትና አሽናሽን እጅግ በርካታ እርጥብ (ወሃማ) ሜሬቶች ለባለሃብቶች ተሰጥተዋል፡፡ በጋምቤላ ክልል ሥሬውን እያከናወነ የሚገኘው የሕንዱ ካሩቱሪ ኩባንያ ወሳኝ የሆኑ እርጥብ (ረግረግ) ሜሬቶችን በከፊል እያስማጠጠ ለሚያከናውነው የእርሻ ተግባር ሲጠቀም ይህ የጥናት ቡድን ቦታዎቹ ላይ በተገኘበት ወቅት ለመጫለከት ችሏል፡፡

## የአካባቢ ጥበቃና የማነበራዊ ተጽዕኖ ክትትል በኢትዮጵያ

የልማት እንቅስቃሴዎችን ለመጠን እና ለማቃለል የአካባቢ ጥበቃ ተጽዕኖ ግምገማ (ብዙውን ጊዜ ከማነበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጋር በማጣመር) በዓለምአቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ የዚህ ግምገማ ብቃት እንደየአገሩ በለያይም በአሁኑ ጊዜ በሥሬ ላይ ከዋሉት ዘደዎች መካከል የልማት ፕሮጀክቶችን ቀጣይነትን ለሚጋገጥ የሚገለግል ተስማሚ ማልገያ ነው፡፡ ይህ ግምገማ የአንድን ፕሮጀክት የአካባቢያዊና የማነበራዊ ተጽዕኖዎች አስቀድሞ ለሚደትና የእርምት እርምጃ ለመውሰድ፣ እንዲሁም አጠቃላይ ምክክር ለሚደረግና ትንተና ለማስጠት በብቃት የሚረዳ ነው፡፡

በ1990ዓም የወጣው የኢፌዲሪ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ ሕዝባዊ የምክክር ሂደት፣ የቀጣይነት ጽንሰ ሃሳቦች እና ሙሉ የአካባቢያዊና የማነበራዊ ተጽዕኖ ግምገሞች እንዲደረጉ ይጠይቃል፡፡ በ1994 ደግሞ የተሻሻለው ሕግ ፕሮጀክቶች በተግባር ላይ ከሙላቸው በፊት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (EIA) መደረግ እንዳለበት ደንግጓል፡፡[141] ነገር ግን በግንዛቤ መታጣት፣ በአቅም ማነስ፣ በአስፈጻሚው አካል ስልት ማጣት፣ በሚበረታቻ መታጣት፣ እና በደካማ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ምክንያት ይህ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አፈጻጸም ደካማ ሆኖ ቆይቷል፡፡[142] በ1997ዓም 300 የሚሆኑ የፕሮጀክት ባለቤቶች በአዲስ አበባ አካባቢ ለኢንቨስትመንት የሚውል ሜሬት ተሰጥቷቸው ነበር፡፡ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣንም ከመካከላቸው ሰሚያ የሚሆኑትን ባለሃብቶች መርጦ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (EIA) የሚደረግን አስፈላጊነትን በመግለጽ ቢነገራቸውም ሁለቱ ብቻ የባለሥልጣኑን መ/ቤት አሠራር በመከተል ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሞከሩ በሆንም እነርሱም ግን ምንም ዓይነት መረጃ ሚልሰው አላስረከቡም፡[143]

## 3.6 የውሃ አጠቃቀምና አስተዳደር

ኢትዮጵያ 122 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ የሚፈሱ 12 ወደ ሸለቆ የሚወርዱ ወንዞች ያሏት ሲሆን በሜሬት ውስጥ ደግሞ ከ2.6 እስከ 6.5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ የሚደርስ የውሃ ክምችት አላት፡፡ ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ካላት ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት አኳያ አንድ ሰው በዓመት 1ሺህ 575 ሜትር ኩብ ውሃ እንደልቡ ማግኘት ይችላል ማለት ነው፡፡ በአገሪቷ ውስጥ ያለው የውሃ ተፋሰስ በአራት ይከፈላል፤ (ከአባይ፣ ከስምጥ ሸለቆ፣ ከሸበሌ-ጁባ እና ከሰሜኑ ምስራቅ) 69በመቶ የሚሆነው የሚመጣው ከአባይ ወንዝ ነው (የአባይ ወንዝን በተመለከተ ሳጥን ኘ ላይ የቀረበውን ወይይት ይመልከቱ) አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ወንዞች ሁኔታ ወቅታዊነት የሚታይባቸው በመሆናቸው 70በመቶ የሚሆነው የሚፍሰት በሐምሌና ነሐሴ ወራት ነው፡፡ ሕዝቡ ከሚጠቀመው 3በመቶ ከሚሆነው የውሃ ኃብት 86በመቶ የሚሆነው ለእርሻ የሚውል ሲሆን 11በመቶ የሚሆነው

